


ክላሲ ጹሁፍ

ጀምበሩ ደሲ መንግስቱ
Jemberu Dessie Mengistu

፪ኛ ዕትም

አዘጋጅ፦ ዳዊት ደስታ

አሳታሚና አከፋፋይ
በኢ/ኦ/ተ/ቢ/ክ/በሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
፳፻፷ ዓ.ም

© ማኅበረ ቅዱሳን ፳፻፫ ዓ.ም
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

የመጀመሪያ ዕትም 2005 ዓ.ም.
ሁለተኛ ዕትም 2008 ዓ.ም.

ይህ መጽሐፍ
በሕ/አ/ተ/ቤ/ክ/በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ኤዲቶሪያል ቦርድ ታይቶ፣ ታርሞና ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው።

አድራሻ፡-
በሕ/አ/ተ/ቤ/ክ/በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ፖ.ሳ.ቁ 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ስልክ ፡- +251 11 124 61 82//83/84

Email:- mk.devt@yahoo.com
Website:- www.eotc-mkidusan.org

መግቢያ

አለቃ ኪዳን ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ "ብሂል" የሚለው ቃል ትርጉም ብሀለ "አለ" ብሂል "ማለት" ሲሆን ፤ አበው የአብን ብፁር አባቶች ማለት ነው /1948፡/ The sayings of fathers ብሂለ አበው፡- የአባቶች አባባል፡ምክር፡ትምህርት ማለት ነው። ይሁ መጽሐፍ የቀደሙ አባቶችን ብሂል ይዟልል። እነዚህ የአበው ብሂሎች መንፈሳዊ ሕይወትን የሚያንጹ፣ በሕይወ ታችን ለሚያጋጥሙን የእንንንት ፈተናዎች ምንነትና የአበውን ተጋድሎ የሚያስተምሩን ናቸው።

ዲ/ን ዳንኤል ክብረት "ብበረሓው ጉያ ውስጥ" በሚለው መጽሐፉ የአበው ብሂሎች ዘመናችን ተሻግረው እዚህ እንዴት ሊደርሱ እንደቻሉ ሲገልጽ "ከገዳማውያን አበው የተገኙት ብሂሎች በተሰያዩ ደረጃዎች አልፈው በዚህ ዘመን መድረሳቸው ይታመናል።

የመጀመሪያው ደረጃ እነዚያን መንፈሳውያን አርበኞች የሆኑ ገዳማውያን አበው ለሚቀርቡ ፣ ለሚጠይቁና በረድእነት ለሚያገለግሉ በየዘመኑ በቃል የተነገሩበት ደረጃ ነው። ወደ ግብጽና ፍልስዮኤም በረሓዎች እነዚህን አበው ለማየት በመጡ ክርስቲያኖች አማካኝንት ለይየ ዘመናት ቃል በቃል ሊተላለፍ ቅደተዋል።

ሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እነዚህ በቃል የተላለፉ የአበው ብሂሎች ወደ ጽሑፍ የተሸጋገሩበት ዘመን ነው። ይህም በኖሎው መቶዘዘ መጨረሻ እና በአምስተኛው መቶዘዘ መጀመሪያ

ጽናት

፩. አሁን እያለፍክ ያለህበት ሰዓት፣ ባለህበት ቦታ ያገኘኸው ሁሉ ሰው፣ ባለህበት አፍታ የምትሠራው ሥራ እነዚህ ሁልጊዜ በሕይወትህ ሁሉ እጅግ ጠቃሚ ናቸው።

/ ጸውሎስ ኤፒፎኒዎስ /

፪. የጋብቻ ታላቅነት የሚረጋገጥበት ቤተክርስቲያን ደስታዋን የምትገልጥበት፣ በረከት የሚታተምበት፣ መላእክት ለምስክርነት የሚገኙበት፣ እግዚአብሔር የሚያጸናው ጋብቻ ነው።

/ሊቁ ተርቱልያን/

፫. ለምናስተምረው ትምህርት እውነተኛነት ማስረጃው ከቅዱሳን ሐዋርያት በደቀ መዛሙርቶቻቸውና አሥረኍኛታቸውን በተከተሉ ቅዱሳን አበው በኩል ያገኘነውና የወረስ ነው ትውፊት ከኛ ጋር መኖሩ ነው።

/ቅዱስ ዮሐንስ ክሪሶስቶም/

፬. ሐዋርያት ሁሉንም ነገር አልጻፉልንም። እንዲያውም የበለጠውን ያስተማሩን በቃልና በማሳየት ነው። ለኛ ከጽሑፎቻቸው ጋር ያወረሱን ትልቅ ሀብት ቢኖር ትውፊታቸው ነው።

/ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፭. ወይንን ውሰድ መጀመሪያ ቅጠል ያወጣል ከዚያም እንበጥ ተጥሎም መራራ ፍሬ በመጨረሻም ጣፋጭ ዘለላ በእጅት ይገኛል። ዘወትር እኛም እንደዚሁ ከብዙ ፈተና፣ ሁከት፣ መረበሽ፣ ችግር በኃላ እርሱን አምነናልና ሰላምን እን ቀበላለን።

/ቅዱስ ቀሌምንጦስ/

፮. ለክርስቶስ ሥጋ ክብር ማንም ሰው በድንግልና መኖር ከቻለ ያለሃኝ ሕይወት እጥፋቱ ያለምንም መመኳት ያድርግ።

/ቅዱስ አትናቴዎስ/

፯. ክርስቲያን የራሱን ሕይወት አይቆጣጠርም ጊዜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሰጣል እንጂ።

/ቅዱስ አትናቴዎስ/

፰. ከልባቸው የእግዚአብሔር አገልጋዮች በሆኑ ሰዎችና ተስ ፋቸውን በእግዚአብሔር ላይ በጣሉት ሰዎች ላይ ዲያብሎስ ጊታ ሊሆን አይችልም ጊታ የሆነው እግዚአብሔር እንጂ።

/አረኖው ሄርማን/

፱. በልቡ እግዚአብሔርን የያዘ ሰው ሕግጋቱን መፈጸም ይችላል። ነገር ግን በክንፈሩ ብቻ ጊታ ሆይ ጊታ ሆይ የሚል ልቦናው ተጠራጣሪ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ሕግ መፈጸም አይችልም።

/አረኖው ሄርማን/

፲. ትግል፡ ፈተናና መከራ ከሌለ የድል አክሊል፡ ጠላት ከሌለ ድል ማድረግ አይኖርም።

/ታላቁ ባሲልዮስ/

፲፩. አንድ ሰው ለቤተ ክርስቲያን መሰረታዊ ሥራ ሲያከ ናውን የሚችለው ታሪክን የሚሠራ ወዲያ ወዲህ ከማለት ይልቅ በአንድ ቦታ ረግቶ ሲኖር ነው።

/አባ እንጦንስ/

፲፪. ሰው በህይወት ዘመኑ የተቀደሰ ሥራ እንዲሠራ እንጂ ዝም ብሎ እየበላ እየጠጣ ዘመኑን እንዲገፋ እግዚአብሔር አልፈጠረውም።

፲፫. በስም ብቻ መኖር በታሪክ ብቻ መክበር ስለማይቻል ሁሉም በተሰለፈበት የሥራ መስክ ቅኑት እንደ ገበሬ ፅሙድ እንደ በሬ ሆኖ መሥራት ይጠበቅበታል

/ብፁዕ አቡነ አስጢፋኖስ/

፲፬. የክፉ አባቶቻችን ልጆች ልትሆኑ ከወደዳችሁ እነርሱ የጻፉትን እንጂ ምንም ሌላ አትመኑ። /ቅዱስ አትናቴዎስ/

፲፭. በሚያልፍ ሥጋዊ ሕይወት የሚያልፍ ሥራ መሥራት ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ ነው። /ብፁዕ አቡነ አስጢፋኖስ/

፲፮. በሕዝብ መመላለሻ ትራንስፖርት ስትንዝ ወይም መጓጓዣ በምትጠብቅበት ቦታ /አካባቢ/ ወይም አንድን ሰው ቀጥረህ እርሱን በምትጠብቅበት ጊዜና ቦታ ወዘተ አጭር የሕሊና ጸሎትን በመጸለይ ራስህን ጠብቅ፡ ይህን በማድረግህ ከፍርሃትና ከጭንቀት ከመረበሽና ከመሳቀቅ ልትጠብቅ ትችላለህና። /አቡነ ሺኖዳ/

፲፯. ከእንቅልፍህ በነቃህም /ከመኝታህ በተነሣህም/ ጊዜ ይህን ጸሎት ደጋግመህ በመጸለይ ወደ ዕለታዊ ተግባርህ ተሠማራ። በመሆኑም በሕሊናህ የሚቀረጸው ቀዳሚ ሃሳብህ መንፈሳዊ ይሆናል። በመጀመሪያ የምትነጋገረውም ከእግዚአብሔር ሥራ ይሆናል።

/አቡነ ሺኖዳ/

፲፰. መንፈሳዊ ነገርን ለመጨመር ብትፈልግ ቀኑን ሙሉ እግዚአብሔርን በመፍራት ራስህን ጠብቅ በሥርዓት ሕዋሳትህን ጠብቅ ራስህን ለማይገባ ደስታ አሳልፈህ አትስጥ።

/መጽሐፍ ጨዋታ ገጽ 14/

፲፱. መንፈሳዊ ሕይወት ሁልጊዜ ከእድገት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ከናጽምናት ወደሚልቅ ፍጽምናት የሚደረግ ሽግግር ነው።

/ቅዱስ ሺኖዳ/

፳. በመንፈሳዊ መንገድ ውስጥ ዝግ ብለህ አትጓዝ። በጎዳና ላይ በምትመለከታቸው ትዕይንቶች አማካይነት አትማረክ፣ አትቱምም ጠላቶችህም ሆኑ ወዳጆችህ ያሰናክሉህ ዘንድ አት ፍቀድላቸው ።

/አቡነ ሺኖዳ/

፳፩. በአንድ የጽድቅ ሥራ የምትተዋሉ ከሆነ ጠባዩን፣ ውጊያዎቹን እንቅስቃሴዎቹንና ሕአዚህን ሁሉ እንዴት ድል እንደ ምትነ ባቸው ተማክረህባቸው።/አቡነ ሺኖዳ/

፳፪. የምትጸልየ ከሆነ ጸሎታችሁን ላለማቆም ተመኙ፣ ዘላም ለመጸለይ የምትመኙ ከሆናችሁ ሕይወታችሁ ራሱ ጸሎት ይሆናል።/አቡነ ሺኖዳ/

፳፫. በውሳትህ በጎ ሥራ የሠራው ይመስለኝ ነበር ወደ ሰርግና በደረሰው ጊዜ ጥቂት ስንኳ በጎ ሥራ እንዳል ሠራው ታውቀኝ። /ቅዱስ አባ ሞሞስ/

፳፬. ቅዱሳዊ ሚታ ለእሱድ ፊቱን ወደ ምሥራቅ እዙር እጅን ወደ ሰማይ ሰቅሎ ዐሰይ ጀርባውን ስትመታው ጸሎት የጀመረ በማግስቱ እሱድ ጧት ወጥታ ግንባሩን እስከተመታው ድረስ ጸንቶ ይቆም ነበር። ቆሞ በጸሎቱ ካደረ በኋላ "ንሣእ መክፍልተኮ አ ሀሳይ ሥጋ፣ እንተ እስራኤ ደኃማ ሥጋ ሆይ ያውልህ እረፍ ብሎ ያርፍ ነበር። /ቅዱስ ሰራፒዮን/

፳፭. ቅዱሳት መጻሕፍት ክርስቶስ ፍጹም ሰው እንደሆነ እንደ ሚነግሩን ፍጹም አምላክም እንደሆነ ይነግሩናል።

/ጸፈኔዎስ/

፳፮. እግዚአብሔርን መፍራት እርሱን በመውደድ ይቀድማል፣ እርሱን መፍራት እርሱን ወደመውደድ የሚመራን መንገድ ነው። /አረጋዊ መንፈሳዊ/

፳፯. ትግል፡ ፈተናና መከራ ከሌለ የድል አክሊል፡ ጠላት ከሌለ ድልማድረግ አይኖርም። /ባሲልዮስ ዘቂሳርያ/

፳፰. የቤተ ክርስቲያንን ዳር ጠብቁ መባሉ ዳር እንዳይ ሆን።

/ብፁዕ አቡነ በርናባስ/

፳፱. ንቅሐ ልቡና፡ ራስን ማወቅና ራስን መግዛት የነፍስ መሪዎቿ ናቸው። /አባ ጴሜን/

፴. ጠላት በዘዘበት ቦታ የምኖር ከሆነ ብርቱ ወታደር እሆናለሁ።

/አባ ጴሜን/

፴፩. እግዚአብሔርን ከፈለግነው ራሱን ይገልጥልናል፣ አጥብቀን ከያዝነውም ከእኛ ጋር አብሮ ይኖራል።

/አባ አርሳንዮስ/

፴፪. በተጋድሎ ውስጥ ለሚገኝ መነኩሴ የእንድ ሰዓት ዕንቅልፍ በቂ ነው። /አባ አርሳንዮስ/

፴፫. ለሚጠቀሙባቸው ሰዎች የክርስትና መጻሕፍት ፕንዘብ ማድረግ መልካም ነው። እነዚህን መጻሕፍት አብዝተን በተመለከትን ቁጥር ወደ ንጠኢት ማዘንዘላችን ይቀንሳል። በእምነት ጸንተን ጽድቅንም የበለጠ እንፈጽም ዘንድ ያነቃቁናል።

/አባ አጸፋንዮስ/

፴፬. ሰዎች የፈጸሙልንን ክፋ ነገር የምናስብ ከሆነ እግዚአብሔርን ለማሰብ የምንችልበትን ኃይል እናጣለን፡፡ ነገር ግን የእጋንንትን ክፋ ሥራ ዘወትር የምናስብ ከሆነ ጽኑዐን እንሆናለን፡፡ /አባ መቃርዮስ/

፴፭. በፈተና ያላለፈ ሰው መንግሥተ ሰማያትን አይወርስም፡ ያለ ፈተናም ማንም አይድንም፡፡ /አባ እንጦስ/

፴፮. ነፍሳችን በምግባር ትሩፋት እናስጊጣት እንጂ ሥጋ ችንን ልናስጌጠው አይገባም /ዘዮሐንስ አፈወርቅ/

፴፯. በጥፋት የሚኖር ሰው እያንዳንዷን የሕይወቱን መልካም ቀን ማጣጣም እንደሚችለው ሁሉ ጻድቅ ሰው ደግሞ መልካም ማድረግን ሳይተው የመጥፎ ቀንን የመጨረሻ ደረጃ በጽናት ይቋቋማል፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፴፰. በመከራ ጊዜ ወዳጅን ማግኘት በጭንቀት ውስጥ ላሉ ትልቅ መጽናኛ ነው፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፴፱. የሰውነት ድርሻ መወፈርና መጠንከር ብቻ መሆን የለበትም፡፡ ብዙ መከራን የመቋቋም ችሎታም ይኑረው፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፵. ያለ ጽናት የምትለማመደው ሥራ ፍሬ አይኖረውም፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፵፩. ነፍስ በተፈጥሮ ባሕሪዋ ስትገኝ በንጽሕና ትኖራለች እንደተጠራን ሆነን ብንገኝ በጽድቅ እንኖራለን፡፡

/አባ እንጦስ/

፵፪. የኃብቻ ታላቅነት የሚረጋገጥበት ቤተክርስቲያን ደስ ታቀን የምትገልጥበት፣ በረከት የሚታሥጣበት፣ መላእክት

፻፩. ከኃጢያት ሽሽ፣ ወደ ራስህም ጠልቀህ ግባ በነፍስህ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር መንግስት የሚያወጣውን መሰላል ታገኛለህ፡፡ /ቅዱስ ይስሐቅ ዘዕርያ/

፻፪. በየጊዜው ኃጢአትህን የማታስብና ንስሐ የማትገባ ከሆነ ያን ቀን እንደኖካት አትቁጠር /ቅዱስ ይስሐቅ/

፻፫. ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ለእኛ ንስሐ ለገባነው ክብር የሆነ ሰማያዊ አክሊልን ታቀዳጀን ዘንድ የእሾህ አክሊል ደፋህ፡፡ /ቅዱስ ዘርተሎሚዎስ/

፻፬. ጌታ ሆይ የንስሐ ወይንን ትሰጥ ዘንድ በመስቀል ላይ መራራ ሐሞትን ሆምጣጤን ጠጣህ እኛን በቅዱስ ሥጋህና በክቡር ደምህ ታጠግበን ዘንድ ቀኝ ጎንህን ተወጋህ፡፡

/ቅዱስ ዘርተሎሚዎስ/

፻፭. የንስሐ አባት ማለት እርሱን ስትመለከት እግዚአብሔር እና ተእዛዛቱን የምታስታውስበት ሰው ማለት ነው፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፮. ዓለምና ሕይወት በትምህርት የተሞሉ ቃላት ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፻፯. ሰው ስለድካሙ ሊወድቅ ይችላል፣ የማይወድቅ ማንም የለምና ይሁን እንጂ አንድ ሰው ንስሐ መግባትና ከው ድቀቱ መማር አለበት፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፻፰. እንኪያስ ፈጥነን ንስሐ እንግባ እርያዎች ከሚበሉት ተረንቃሞ /አስር/ መጥገብ አይቻልም፣ ፈጣሪያችንን የሰማዩን የምድሩን ያህል አንተን በደልን፣ ላንተ ልጆች

ለምስክርነት የሚገናኙበት፣ እግዚአብሔር የሚያጸናው ጋብቻ ነው፡፡ /ሊቁ ተርቱልያን/

፻፱. ወንድሞች ሞት የሚመጣው ድንገት ነው፣ በማታ፣ በጠዋት ወይም በቀትር ሊመጣ ይችላል፣ ተጠንቀቁ፣ ንቁ፣ እንቅልፍ አያሸንፋችሁ፣ በዚህ ከጸናችሁ ፍጻሚያችሁ ያማረ ይሆናልና፡፡ /ቅዱስ እንድርያስ/

፻፲. እግሮቻችሁ በብረት ችንካር እንደተተከሉ እንደ ጽኑ ዓምዶች ጸንታችሁ በቤተ እግዚአብሔር ትኖሩ ዘንድ እነግራችኋለሁ፡፡

/ቅዱስ አትናቴዎስ/

፻፲፩. ለረጅም ጊዜ ጸንተህ በመታገስ ለፍጻሜ የማታደርሰው ስትድ ሁሉ ፍሬ ቢስ ነው፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፻፲፪. አቤቱ መንፈሳዊ አይኖች ስጠን ዘወትር እንቱን ያዩ ዘንድ ጆሮዎቻችንም ያንተን ቃል ብቻ ያደምጡ ዘንድ፡፡

/ዕዮተ ቅዳሴ ዘአግዚእ/

፻፲፫. ክርስቲያኖች የክርስቶስን ምሳሌ በመከተል በማይለ ወጠው የጸናው እምነታቸው ወደ ሊላ ምግባር ይመቸዋል ፡፡

/ቅዱስ ፖሊካርፐስ/

፻፲፬. በጎ በጎውን ያይልናል ያውቅልናል፣ ክፋ ክፉውን ያይ ብናል ያውቅብናል ብላ በሰቂለ ሕሊና ጸንተን እንዲህ ሆነን እንኑር፡፡ /ቅዱስ አትናቴዎስ/

፻፲፭. ከሰው ተለይቶ ወንድሙን የሚመክር ሰው እሱ የፍቅሩን ጽናት ብዛት ያስረዳል፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፻፲፮. ጽናት የሊለባት ጸሎት በነፍስ ተዘክሮተ እግዚአብሔርን ታሳድራለች ታመጣለች፡፡ /ሳሰልዮስ/

መሰል አይገባ ንምና ከእገሊጋዮችህ እንደ አንዱ አድርገን እንጂ እንበለው፡፡

/ሃይማኖት አበው/

፻፲፰. ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! በእኛ ንስሐ ለገባነው ክብር የሆነ ሰማያዊ አክሊልን ታቀዳጀን ዘንድ የእሾህ አክሊል ደፋህ፡፡ ዮሴፍ ዘርተሎሚዎስ/

፻፲፱. ጌታዬ እግዚአብሔር ከሊላ ንኩራም የለም

/ቅዱስ ይስሐቅ/

፻፳. ደህሱን ሰው ወደ ንስሐ መራንን? አገልግሎት ወደ ወደንም ደሞ እንቅስቃሴ አይደለም፣ አገል ሊሳው የሚሰጠው መንፈሳዊነት እንጂ፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፳፩. ስንሐ መግባት ማለት ሕይወት ሲሆን ንስሐ አለመግባት ግን ሞት ነው፡፡ /አረፃው ሄርማ/

፻፳፪. ምንባቢም ቢሆን ስለ ኃጢአቶቹ በእግዚአብሔር ፊት ወደን ያመለከሰና ፈተናን አስክ ሕይወቱ የመጨረሻ እስከሚሰጠው ድረስ የሚጠባበት ሰው ሥራው ታላቅ ሥራ ነው፡፡

ስለ መልካሳናቸን ምንም አይነት ትጣት የማንቀበል ቢሆን ግር እግዚአብሔር ሕሊናን የሚያነል ፈራጅ ዳኛ በመሰጣትን አይፈጥርም ነበር፡፡ /ቅዱስ አትናቴዎስ/

፻፳፫. ስለ ኃጢአት ሸንስሐና በእንባ ራስን እንደ መው ቀስና አንደ መሳለስ ያለ ጠቃሚ ነገር የለም፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፳፬. ልባችንን ጠራና በስባሽ ከሆነው ከምድራዊው ምኞት ርቀን ከዘደለ ሸንስሐ ነፃ ካደረግነው በጸጋ መንፈስ ቅዱስ

የተሞላን እንሆናለን፡፡ /አባ አብርሃም መፍቀሬ ንዳያን/

፻፳፯. በንስሐ ባርነት ከፈጣሪ ወደሚገኝ ቸርነት እንቀር ባለን፣ ንስሐ ለሚሿት ሰዎች የተከፈተች የይቅርታ በር ናት፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፳፰. ከመንግሥተ ሰማያት እንዳትለዩ ንስሐን ፕዘዘ አድርጉት ፡፡

/አረጋዊ መንፈሳዊ/

፻፳፱. ኃጢአቴን የማይናገር ሰው ሥረያት አያገኝም

/ማር ይስሐቅ/

፻፴. እጠገናለሁ ብሎ መሰበር እንዳይመች ንስሐ አገባለሁ ብሎ ኃጢአት መሥራት አይገባም፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፻፴፩. እግዚአብሔር ለሴሰኝነትና ለአመጽ ዕድሜ አይሰጥም፡ ለንስሐ ግን ሁሌም እንደታገሠ ነው፡፡ /ዘዘፀዓ አቡነ እንድርያስ/

፻፴፪. ዘመኔን ሁሉ በኃጢአት ያሳለፍኩ ጎዋእ አባሲ የምሆን እኔን የንስሐ ሥራ እንድጠብቅ አድርግኝ፡፡ /ማርይስሐቅ/

፻፴፫. በንስሐ ምክንያት የእግዚአብሔርን ቸርነት እናገኛለን፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፴፬. ንስሐ እግዚአብሔርን ለመፍራትና በሃይማኖት በልቡና የምትገኝ ሁለተኛ ጸጋ ናት፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፻፴፭. በየጊዜው ለንስሐ ፈጪ፡፡

/ቅዱስ እንጦንስ/

፻፴፮. ኃጢአትን አለመሥራት እጅግ መልካም ነው፡፡ ብትሠራ ግን ንስሐን ባትታወም ጥሩ ነው፡፡ ንስሐ ከገባህ ደግሞ ወደኃጢአት ባትመለስ የተሻለ ነው፡፡ ወደ ኃጢአት ካልተመለስክ ደግሞ ይህን ያደረገልህን አምላክ ማመስገን መልካም ነው፡፡ /ቅዱስ ባስልዮስ/

ፍቅር

፻፴፯. ወደ እውነተኛ ፍቅር ስንደርስ ወደ እግዚአብሔር መድረሳችንና ጉዞአችንን መጨረሳችን ነው፡፡ በእውነተኛ ፍቅር ተንሳፈን ከዓለም ባሻገር አብ፡ ወልድን መንፈስ ቅድስ ወዳለበት ደሴት እንሸጋገራለን፡፡

/ቅዱስ ይስሐቅ ዘዕርያ/

፻፴፰. በፍቅር ኃጢአቶቻችን ይቅር ይባሉልናል፡፡

/ቅዱስ ቀለምንጦስ/

፻፴፱. ጸም ከጸሎት ይበልጣል ይልቁንም በጎ ሥነምግባር ከሁሉ ይልቃል እንደዚሁም ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ያጠፋል፡፡

/ቅዱስ ቀለሜንጦስ/

፻፵. እግዚአብሔር ወሰን በሌለው ፍቅሩ ሰውን ይወደዋል፡፡ ስለወደደውም በእርኢያውና በአምሳሉ ፈጠረው፡፡

/ቅዱስ ሄሬኔዎስ/

፻፵፩. ፍቅር በእውነት ሰማያዊ ጎባዕትና የአእምሮ ምግብ ነው፡፡

/ቀለሜንጦስ ዘእስክንድርያ/

፻፵፪. ክርስቲያን ወንድምህን በፍቅር ባየኸው ጊዜ እግዚአ ብሔር ማየትህ ነው፡፡

/ቀለሜንጦስ ዘእስክንድርያ/

፻. የሰው ልጆችን የእግዚአብሔር ልጆች ለማድረግ የእግዚአብሔር አብ የባህሪ ልጅ የሰው ልጅ ተባለ፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፩. ጌታችን ነፍትን የከፈተበት ወደ ሰማያዊው መንግስቱ እኛን ያስገባበት በፊታችንም ላይ ሲኦልና ዝሆንምን የዘጋበት በመስቀሉ ነው፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፫. ክንስሐ አባትህ ጋር ስትሆን ጥያቄህን እንጂ ውሳኔህን አታቅርብላቸው በልብህ ካሰብከው ጋር እንዲስማሙ ሳይሆን በሁላብ ላይ ሀሳባቸውና ምክራቸውን እንዲሰጡህ አድርግ

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፬. ንስሐ ለተጠመቁ ሠዎች ከጥምቀት በኃላ የተሰጠች ሀብት ናት፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፭. ንስሐ ከጥቂት ቆይታ በኃላ የሚመለሱበት የኃጢያት እረፍት አይደለም፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፮. የሚያሰደንቅ የሚያዋርድ ኃጢአት ከመሥራት እድን ዘንድ የንስሐ አጋዥ የሚሆኑ አፍአዊ ትሀትናን፡ ውስጣዊ ትህትናን፣ ጸሎት ዘወትር፡ ምሕረት ምፅዋትን፡ እንብዕ ዘወትርን መያዝ ይገባል፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፯. ኃጢአቱን ተረድቶ ንስሐ የሚገባ ኃጢአተኛ፡ ምንም በደል ከሌለበት ነገር ግን ራሱን እንደ ጻድቅ ከሚቆጥር ሰው የበለጠ ይሻለኛል፡፡

/አባ ሳርሚታስ/

፻፰. እግዚአብሔር ተአምራት ባለማድረጋችን ወይም የተሰወረውን ምስጢር ባለማወቃችን ወይም የተራቀቀ ነገር ባለመማራችን አይወቅሰንም፡ ስለ ኃጢአታችን ባናለትስና ንስሐ ባንገባ ግን ስለዚህ ይወቅሰናል፡፡

/አባ ወቅሪልን/

፻፱. መስቀል የክርስቲያኖች ተስፋ፡ መስቀል የሙታን ትንሳኤ፡ መስቀል የእውራን መሪ፡ መስቀል ተስፋ ቅቡጸን፡ መስቀል ትንቢተ ነቢያት፡ መስቀል ስብክተ ሐዋርያት፡ መስቀል የሰማዕታት ክብር፡ መስቀል የጻድቃን ሞገስ፡ መስቀል የቤተክ ርስቲያን መሰረት፡ መስቀል የዓለም መረጋጋት ሰላም፡ መስቀል የቤተክርስቲያን ጌጥ ነውና በአዕምሮአችሁ እንደ ማንተም አትሙት፡ ክፋ መንፈስ የተመታብትንና የቆሰለበትን ነዙ ወደ ባለሰይፍ ሲቀርብ ፈጽሞ አይችል ምና፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፲. እርጉም በሆነ ከይሲ ምክር ትእዛዙን ባፈረስን ጊዜ ከተድላ ገነት ወደ ጥፋት ከህይወት ወደ ሞት ከነጻነት ወደ መገዛት ከኀጢያት ቀንበርም ተገዝን እርሱ ግን ፍጥረቶቹን አልተወንም፡፡ ቸልም አላለንም፡፡ እርሱ እንደበደልነው መጠን ፈጽመን እንጠፋ ዘንድ በኃጢያታችን አልተቀየመንም ወደደን እንጂ፡፡ ጉብኝንም ማረን ይቅርም አለን ከሚገዝንም እጅ አዳነን አዳኝ መድኂኒት የምክሩ አበጋዝ ለአባቱ ቀኝ እጅ ከንድ ሀይለኛ ጥበቡ የሚሆን ልጁን ላክልን በእርሱም ከዚህ ዓለም ወገን የወ ደደውን ሁሉ አደረገ፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፲፩. ስለወንድሙ መዳን የማይደክም ድኗል ብዙ አላምንም፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፲፪. እግዚአብሔር ሰዎችን በማዳጅና በተጽእኖ ሰውን ወደርሱ አያቀርበውም በታላቅ ፍቅሩ ግን ይስበዋል፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፺፮. እግዚአብሔር በፈቀደ በአቅሚ ለቤተክርስቲያን የሚቻ ለኝን አገልግሎት ፈጽሜአለሁ ወደማይቀረው እየተጓዝኩ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የቤተክርስቲያን ሥራ የበለጠ ብታጠናክሩት በእርግጥም ልጆቼ ናችሁ ብትተውት ግን እድሜ ይወቅሳች ኋል፡፡

/አባ እንየው/

፺፯. እኛ ወደእርሱ መውጣት ሲያቅተን እርሱ ወደኛ ወረደ፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፺፰. ሰው ሕያውነትን ማግኘት የሚችለው ከእግዚአብሔር ጋር ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ከሁለቱም ጋር ባለው ተዛምዶ የተነሳ ሁለቱንም አካላት መካከል ሆኖ ለማስታረቅ የቻለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱ ሰውን ወደ እግዚ አብሔር አቀረበ፤ እግዚአብሔርም ለሰው ገለጠው፡፡

/ሊቁ ሄሬኔዎስ/

፺፱. ለጥበቡ ባሕር ድንበር የለውም ለትእዛዙም ይቅርታ መስፈርት፤ ለመንግሥቱ ስፋት ዐቅም የለውም፤ ለእግዛዙም ስፋት ወሰን የለውም ... ሳይጠይቅ ሕሊናን ይመረምራል፤ ሳይመረምር ልቡናን ይፈትናል፤ ያለመብራት በጨለማ ያለውን ያያል ... ሁሉ በእርሱ ዘንድ የተገለጠ ነው፡፡

/ቅዱስ አጺፋንዮስ/

፻. ቂመኛ ሰው ሥጋ የለበሰ ሰይጣን ነው ... የክርስቶስ ፍቅር ሥራቸው ለሞት ታብቃቸዋለችና፡፡

/አረጋዊ መንፈሳዊ/

፻፩. ከእባብ ማሳት ምክንያት በበደልን ጊዜ ለዘለዓለማዊ ሕይወት ራቅን ደስታ ካለበት ከገነትም ወጣን አንተ ግን ለዘለዓለሙ አልጣልኸንም፡፡ በቅዱሳን ነቢያትህ ነፀኛነን እንጅ በኋላ ዘመንም በጨለማና በሞት ለምንኖር ለእኛ ታየህልን በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ሰው የሆነ የአንድ ልጁንም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን በእኛ ላይ አብረህ የአንድ ልጁንም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን በእኛ ላይ አኖርህ፡፡

/ባስልዮስ ዘቂሳርያ/

፻፪. ፀፀት ባለችበት ኃጢአት ምን ትሠራለች፤ ትዕቢት ባለችበትስ ፍቅር ምን ትጠቅማለች፡፡

/አባ ኤልያስ/

፻፫. በልቡ እግዚአብሔርን የያዘ ሰው ሕግጋቱን መፈጸም ይችላል፡፡ ነገር ግን በከንፈሩ ብቻ ጌታ ሆይ የሚል ልቡናው ተጠራጣሪ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ሕግ መፈጸም አይችልም፡፡

/አረኛው ሄርማን/

፻፬. ወንድሞቼ በመስመሩ መጨረሻ ላይ በደረስኩ ጊዜ ፍቅራችሁ ስለጎዳኝ ፈራሁ እናንተም የሕይወቴን ጉዞ ዳግመኛ እንድሮጥ ፈለጋችሁ፡፡

/ቅዱስ አትናቴዎስ/

፻፭. ስለተቀበልናቸው ስጦታዎች ብቻ የምናመሰግን ከሆነ ፍቅራችንን የምንገልጠው ስጦታዎቹን ለሰጠን ለእግዚ ብሔር ሳይሆን ለተሰጡን ስጦታዎች ብቻ ይሆናል፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፮. ጾምን እንጹም ባልንጀሮቻችንንም እንውደድ እርስ በርሳችንም እንዋደድ፤ ንጹም ጾም ወናፍቅር ቢጽነ መንፈቀ በበይናቲነ፡፡

/ቅዱስ ያሬድ/

፻፯. ወደ እውነተኛ ፍቅር ስንደርስ ወደ እግዚአብሔር መድረሳችንና ጉዞአችንና መጨረሳችን ነው፡፡ በእውነተኛ ፍቅር ተንሳፈን ከዓለም ባሻገር አብ ወልድም መንፈስ ቅዱስ ወዳለበት ደሴት እንሻገራለን፡፡

/ቅዱስ ዮሐንስ ዘሰሬያ/

፻፰. ለእሳት ገንዘቧ የሚሆን ሁለት ግብር /ዋዕይና ብርሃን/ እንዳላት ለንስሐም ሁለት ግብር አሏት፤ በፈሪሃ እግዚአ ብሔር በፍቅረ እግዚአብሔር ትፈጽማለች፡፡

/ፊልክስዩስ/

፻፱. የሰው ልጅ በወደቀ ጊዜ እግዚአብሔር መምሰል ተነጥቆ ነበር፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ያጣነውን መልክ ሊመልስልን ነው፡፡

/ቅዱስ ሚናስ/

፻፲. ፍቅረ ቢጽ ከፍቅረ እግዚአብሔር የሚያደርስው ነው፡፡

/አረጋዊ መንፈሳዊ/

፻፲፩. ንስጥሮስ ሆይ አንተን እወድሃለሁ ትምህርትህን እጠላዋለሁ፡፡

/ቅዱስ ቄርሎስ/

፻፲፪. ከሰው ተለይቶ ወንድሙን የሚመክር ሰው እነሆ የፍቅሩን ጽናት ብዛት ያስረዳል፤ ባልንጀሮች ፊት የሚነቅፈው ግን የቅናቱን ጽናት ያስረዳል የምቀኝነቱን ጽናት ያስረዳል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፲፫. ሰው ክፉ ስላደረገ እበቀለዋለሁ ብሎ አይገስጸው ተግሳጽ በፍቅር ካልሆነ ተግሳጽ አይባልም ፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፲፬. ኃያል ወልድን /ክርስቶስን/ ፍቅር ከመንበሩ ሳበው እስከ ሞትም አደረሰው ፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፲፭. አንዳንድ ሰዎች ሰውን መውደድ ስህተትን መደበቅ ለእርሱ መከራከር ይመስላቸዋል፡፡ ነገር ግን እውነተኛ ፍቅር ሰውን ከስህተቱ መጠበቅ ስህተቱን እስኪተው ድረስ መገሰፅ ሊሆን ይችላል፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፻፲፮. ቅዱሳን ለመለኮታዊ ማዕጠንት የተቀጣጠሉ ዕጣን ሲሆኑ የተቀጣጠሉትም በፈጣሪያቸው ፍቅር ነው፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፲፯. ፍቅርን ገንዘብ ያደረገ ሰው ሁልጊዜ ክርስቶስን ይመገበዋል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፲፰. የብቃት ደረጃ ላይ ስትደርስ እንኳ የሥነ ምግባር ሕንፃዎችን ስለሚያፈርስብህ በወንድምህ ላይ ስላለህ ክፉ ሐሳብ ተጠንቀቅ፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፲፱. ፍቅር መያዣ የሌለውን የሰው ልብ እስር ለመሳብ የሚያገለግል የሰላም መንገድ ነው፡፡

/እንጋረ ፈላስፋ/

ተስፋ

፻፳. ያለ ተስፋ ሕይወት አጥተን ስንኖር በዘመናት መጨረሻ ጌታችን ሕይወታችንን መልሶልናል ስለዚህም እናመሰግነዋለን፡፡ /አረኛው ሄርማን/

፻፳፩. የእንጨት ፍሬን በመብላት ባለመታዘዝ ምክንያት የመጣውን ሞት ኢየሱስ ክርስቶስ በመታዘዝ በእንጨት /በመስቀል/ ላይ ተሰቅሎ ሞትን አስወግዶ ሕይወትን ሰጠን፡፡

/ቅዱስ ሄሬኔዎስ/

፻፳፪. በማንኛውም ወቅት ቤተ ክርስቲያን ስትልካችሁ ተሸንፋችሁ እንዳትመጡ፡፡ /አባ እንየው/

፻፳፫. በአገልግሎት ውስጥ አንተ ትጠቀማለህ ሌሎችንም ትጠቅማለህ ፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፻፳፬. ምንም እንኳን መንፈሳዊ ሕይወትህ ደካማ ቢሆንም ተስፋ አትቁረጥ ተስፋ መቁረጥ ዲያብሎስ በእጆቹ ትወድቅ ዘንድ ሞራልህን የሚያዳክምበትና ችሎታህን የሚያጠፋበት ውጊያ ነውና ፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፻፳፭. ሰይጣን እኛን የሚዋጋበት ታላቁ ውጊያው ተስፋ ማስቆረጥ ነው፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፳፮. እርሱ ጻድቅ የሆነ አምላክ ተስፋን ሲሰጥ እታለል ይሆንን ብሎ መጠራጠር ለማን ይቻለዋል! ሊሰጠን ባይፈልግ ኖሮ እንለምነው ዘንድ ባላሻውም ነበር፡፡

/አውግስጢኖስ/

፻፳፯. እኔ ተስፋ ላጣው ተስፋ፤ ረዳት ለሌለው /ለችግረኛው/ ረዳት ለህመምተኛው ፈዋሽ ያጡትንም ትንሣኤ ነኝ ፡፡ ይላል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ /

/ቅዱስ ተግሳ/

፻፳፰. ማንኛውም ነገር ጌታን መጠየቅ ሳትፈልግ ብዙ ኃጢአት ከሠራሁ በኋላ እንዴት ጸሎቴን ከአምላኬ መልስ እቀበላለሁ አትበል፡፡ እንዲህ አይነት አሳቦችን ቦታ አትስጣቸው ነገር ግን በሙሉ ልብህ ወደ ጌታ ተመለስ ያለማመንታትም ጠይቀው የተትረፈረፈ ምሕረቱን ትማራለህ፡፡

/አረኛው ሄርማን/

፻፳፱. ያለ ተስፋ ሕይወት አጥተን ስንኖር በዘመናት መጨረሻ ጌታችን ሕይወታችንን መልሶልናል ስለዚህም እናመሰግነዋለን፡፡

/አረኛው ሄርማን/

፻፴. ከልባቸው የእግዚአብሔር አገልጋዮች በሆኑ ሰዎችና ተስፋቸውን በእግዚአብሔር ላይ በጣሉት ሰዎች ላይ ዲያብሎስ ጌታ ሊሆን አይችልም ጌታ የሆነው እግዚአ ብሔር እንጂ፡፡

/አረኛው ሄርማን/

፻፴፩. በዚህች ምድር ላይ ተስፋ ማጣትህ ለድኅነትህ መጀመሪያ ሊሆን ይችላል፡፡ የምትድነው ግን ተስፋ በማጣትህ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸርነት ነው፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፴፪. የሙታን ትንሣኤ፤ የዕውራን መሪ፤ ተስፋ ቅቡጸን፤ ትንቢተ ነቢያት ስብከተ ሐዋርያት፤ ክብረ ሰማዕታት፤ የጻድቃን ሞገስ፤ የመነኮሳት ጽሙና፤ የደናግል ንፅሕና፤ የቤተ ክርስቲያን መሠረት መስቀል ነው፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፴፫. እግር የሌለው ሰው እና ተስፋ የሌለው ሰው ካሰበው አይደርስም፡፡

/ሊቀ ትጉሃን ኃይለ ጊዮርጊ

፻፴፬. አሁን የምንኖራት ሕይወት ምን ያህል ውድ እንደሆነች ልታውቅ ትወዳለህን? ይህች ሕይወት ለዘለዓለማዊ ሕይ ወታችን መሠረት የትግል ዐውድማ እንዲሁም በገነት ያለችውን አክሊል የምትሰጥ ናት፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፴፭. የአሁኑ ትውልድ ነገ በተሻለ መንገድ ሊራመድ የሚችለው ትናንት አባቶቹ የተራመዱበትን መንገድ ያወቀ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ስለነገው በምናስብበት ጊዜ የትናንትናውን ማስታወስ አለብን፡፡ የትናንቱን ጊዜ ለዛሬም መማሪያ መጽሐፍ ነውና፡፡

/ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ/

ምጽዋት

፻፴፮. ገንዘብ ቢኖርህ በአራጣ አታበድር ነገር ግን ለማይ መልስልህ ስጠው፡፡

/ቅዱስ አግናጥዮስ/

፻፴፯. ምጽዋት መስጠት ገንዘብን ይባርከዋል፤ ያነጻዋል፤ ያበረክተዋል እንጂ አያሳንሰውም አያጎድለውም፡፡

/እንጋረ ፈላስፋ/

፻፴፰. ለተቸገረው ሰው በጎ ነገርን ማድረግ አትከልክል ልታደርግለት የሚቻልህ ሲሆን በወዳጅህ ላይ አትክፋ፡፡

/ቅዱስ ፖሊካርፐስ/

፻፴፱. ለድኀ የምትሰጠው ከግል ንብረትህ አይደለም የራሱን ታስረክበዋለህ፡፡ ለሁሉ የጋራ ጥቅም ሆኖ የተሰጠውን አንተ የግል አድርገህ ወስደኃልና ዓለም ለሐብታሞች ብቻ አልተፈጠረችም ለሁሉም እንጂ፡፡

/ቅዱስ አምብሮስ/

፻፵. እውነተኛ ምጽዋት የበደለውን ታግሦ በመስጠት ይታወቃል፡፡

/ማርይስሐቅ/

፻፵፩. በዝናም ያበቀለው በፀሐይ ያበሰለው የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው ብለህ ምጽዋትህን በትሕትና መጽውት፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፵፪. የማትመጸውት የምትሳሳ ስውነት ጥበብን አታገኝም፤ የምትራራ የምትመጸውት ነፍስ ግን ከመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ እውቀትን ገንዘብ ታደርጋለች፡፡

/ማርይስሐቅ/

፻፶፫. ዘይት ፋናን እንዲመግበው እንዲያሰፋው ምጽዋትም የነፍስን እውቀት ታሸንፋለች፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፶፬. ዝሙት እየሠራህ ብትመጸውት ምጽዋትህን አይቀበልህም፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፶፭. ሠጥቶ መጽውቶ የሚመሰገን ሰው ውዳሴ ከንቱ አይጎዳውም፡፡ "እንድም ወዶ ካልተቀበለው ዋጋ አያጣም ክብር አይጐድለውም" ኑ ያባቴ ቡሩካን ተብሎ መመስገንን አያስቀርበትም ውዳሴ ከንቱ ግን ደስ ቢያሰኘው ያለ ምንዳ የሚሠራ ገበሬን ይመስላል፡፡

/አረጋዊ መንፈሳዊ/

ሰላም

፻፶፮. ሰው ለሰላም የተሠራ መሣሪያ ነው፡፡

/ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ/

፻፶፯. ክርስቲያን በተፈጥሮ የማስተዋል፣ የእርምጥ የጥንቃቄ እና የሰላም ሰው ነው፡፡

/ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ/

ትኅትና

፻፶፰. እግዚአብሔር አንድን የመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታ ሊሰጥህ ቢወድ ፀጋውን ልትጠብቀው ከምትችለው ከትህትና ጋር ይሰጥህ ዘንድ ለምነው አለበለዚያ ግን ከአንተ እንዲያርቀው ጠይቅ፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፶፱. የምታስተምረውን ሕዝብ በሕይወት፣ በእውቀትም ካልበለጥከው በቀር አገልግሎትህ ከንቱ ድካም፣ የሚሰማህም አታገኝም፡፡

/አባ እንጦንስ/

፻፷. ከላይህ ያለ ሰው አስተማሪ የሚሆነው በእውቀቱ ከሆነ ሊቅ ልትሆን ትችላለህ በህይወቱ ከሆነ ግን ክርስቲያን ትሆናለህ ፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፷፩. የተቀደሰ ፀሎት ስትጀምር ወደ አንተ ለሚመጣው ነገር ሁሉ እራስህን አዘጋጅ፡፡

/ቅዱስ አትሬክ/

፻፷፪. እውነትን የሚወድና ዘወትር እንደዐቱን ለእውነት የሚከፍት ሰው ከምንም ነገር በላይ መብቱን ከሰዎችና ከራሱ ከመውሰዱ አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ይወስዳል ፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፷፫. ጨዋ ሰው በሌሎች ሰዎች መጎሳቆል ላይ የራሱን ምቾት አይገነባም፡፡ እርሱ የሌሎችን ሰዎች ምቾት ለማደላደል የራሱን ምቾት ይረሳል፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፷፬. በሁሉም ነገሮች ውስጥ ራሱን የሚወቅስ ሰው ቡሩክ ነው፤ እርሱ ስለ ዘላለማዊነቱ ትኩረት ይሰጣል እንጂ በሰዎች ላይ ለመፍረድ ትኩረት አይሰጥም ፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፷፭. የመንፈሳዊ ሰው ሕይወት ስኬት ወይም ውድቀት የሚመዘነው በውስጡ ባለው የጸጋ አሠራርና ለዚህ አሠራር ያለው ምላሽ ወይም ይህን የጸጋ አሠራር በመቃወሙ ነው፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፷፮. ገበሬ ዘሩን ተክሉን ከብት እንዳይበላበት አጥር ቅጥር ባያበጅለት ገቢታ ዘሩን ተክሉን በበላቸው ነበር፡፡ እኛም ጌታ የሠራት ትሕትናን አጥር ቅጥር ይዘናል፡፡

/አባ እንጦንስ/

፻፷፯. ለድኅነትህ ምንም ዓይነት ጠቀሜታ የሌላቸውን ተረድቶ በሚያወሩና ዋዛ ፈዛዛ በሚያበዙ ሰዎች መካከል ስትሆን ሕሊናህን በጸሎት እንዲጠመድና እንዲተጋ አድርግ፡፡ ከነዚህ መሰል ሰዎች መለየት እነርሱን ሊያስከፋ አንተንም ሊያስጨ ንቅህ ይችል ይሆናል፡፡ ዳሩ ግን ቢያንስ በአካል ብትገኝ ሕሊናህ ከእነርሱ አንድነት መለየት ትችላለህ፡፡ ማንኛቸውም ሳያስተውሉህ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ሕሊና በመነጋገር ልብህን አቅና፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፻፷፰. ወደ መኝታ ከመሔድ በፊት ይህን ጸሎት በተደጋጋሚ መጸለይን ቸል አትበል፡፡ ይኸም ከጸሎቱ ባሻገር ሕሊናህን በመንፈሳዊ ነገር ለመጠበቅ ያስችልሃል፡፡ እንዲሁም ይህን በማድረግህ መኝታህ ይቀደሳል ሕልምህም እውነተኛና ንጹሕ ይሆናል፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፻፷፱. ትሑት ሰው ኢጋንንትን አይፈራም እግዚአብሔር ሁሉን ያስገዛለታልና፡፡ /አባ መቃርስ/

፻፸. አቤቱ የእኔ አገልግሎት ለአንተ የሚያስፈልግህ አይደለም፣ የአንተ አምላክነት ለእኔ ያስፈልገኛል እንጂ፡፡

/ቅዱስ አባ አርሳንዮስ/

፻፸፩. ጸጋ እግዚአብሔርን ማግኘት የሚወድ ማንም ቢኖር እርሱ ስለተሰጠው አመስጋኝ ይሁን፣ ስለተከለከለውም ታጋሽ ይሁን፣ እንድትመለስለትም ይለምን እንዳትጠፋም ጠንቃቃና ትሑት ይሁን፡፡ /ቅዱሳን አባቶች/

፻፸፪. ከሰዎች መካከል አንዱ እንደ ከንቱ እና እንደሌለህ አድርጎ ቢቆጥርህ ከአፈር እንደተፈጠርህና ወደ እርሱም እንደምትመለስ ተናገር አንተ ወራዳ ከንቱ ብሎ ቢሰድብህም አንተ ራስህን አፈርና አመድ ነኝ ብለህ ጥራ፡፡ እራሱን እንዲህ ብሎ ከጠራው ከተከበረው አባት ከአብርሃም የበለጥህ አይደለህምና፡፡ /ማስልዮስ ዘቂሳርያ/

፻፸፫. እንደበትህ በእርምጥ /ዝምታ/ የተመላ ይሁን፣ ልብህን በእርጋታ አኑረው የሁሉም መጨረሻና የሁሉም አገልጋይ ለመሆን በጣም ትጋ ለከንቱ /ወሬ/ ንግግር አትፍጠን፣ ነገር ግን የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል በማወቅና በማስተማር ድኅነትን የሚያስጡ ናቸውና ብልህ ሁን፡፡

/ማስልዮስ ዘቂሳርያ/

፻፸፬. ትሑት ሰው ራሱን ከቅዱሳት መጻሕፍት በላይ ብቻ አድርጐ አያስቀምጥም፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፻፸፭. እግዚአብሔር ሆይ አትተወኝ፣ በፊትህ መልካም የሆነ ምንም ምግባር የለኝም፡፡ ነገር ግን ስለቸርነትህ ስትል መልካሙን ነገር እንዴት እንደምጀምረው ግለጥልኝ፡፡

/ አባ አርሳንዮስ/

፻፸፮. ለሰው ልጅ ታላቁ ነገር በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ስለ በደሉ መውቀስና እስከ መጨረሻዋ ሕቅታ ድረስ ፈተና ሊጠፋ አለመቻሉን ማሰብ ነው፡፡ /አባ መቃርስ/

፻፸፯. ውሻ ከእኔ ይሻላል፣ እርሱ ለሌሎች ፍቅር አለው፣ በማንም ላይም አይፈርድም፡፡ /አባ ኦሎ/

፻፸፰. ብርሃን ወደ አንድ ቤት ውስጥ ሲገባ ጨለማን እንደሚያስወግድ ሁሉ እግዚአብሔር መፍራት ወደ አንድ ሰው ልብ ሲገባም አለማወቅ /በኃጢአት የሚወድቅባትን/ ያስወግዳል፡፡

/አባ እንጦንስ/

፻፸፱. ሰው የጠላውን እግዚአብሔር ያነግሣል፣ እግዚአብሔር የጠላውን ግን ማንም አያነሳውም፡፡

/ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ/

፻፹. የትሑት ሰው መዝገቡ በልቡናው ውስጥ ነው፣ ይኸውም እግዚአብሔር ነው፡፡ /አረጋዊ መንፈሳዊ/

፻፹፩. በራሳችን ላይ ከፈረድንበት እግዚአብሔር በኛ ይደሰታል፡፡ /እንጦንስ/

፻፹፪. እግዚአብሔርን መፍራትና ትሕትና ከሁሉም የሚበልጥ መልካም ሥራ ነው፡፡ /አባ ዮሐንስ ሐጺር/

፻፹፫. እግዚአብሔር ሆይ አፈርና ትቢያ ሆኜ ሳለ ጻድቅ አድርገው ከሚቆጥሩኝ ሰዎች አድነኝ፡፡ /እንጦንስ/

፻፹፬. ከዕውቀት ክብር የተለየች ማለት በእውቀት ከሚሠራ ትህትና የተለየች ሰውነት በትዕቢት መከራ ትያዛለች፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፹፭. ክብርን ትህትና ይቀድማታል አለ በትህትና ይሰጣታል እንድም ትሁት ቢሆን ጸጋ ይሰጣል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፹፮. አቤቱ ጌታዬ ንጉሤ ሆይ የራሴን ጥፋት አስመልክተን እንጂ በወንድሜ ላይ እንድፈርድ አታድርገኝ፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፹፯. ወንድሜ ሆይ ሳይፈረድብህ በፊት በራስህ ፍረድ፡፡

/ቅዱስ መቃርዮስ/

፻፹፰. በሌሎች ላይ መፍረድ የአንድ ሰው የእብሪት ውጤት ነው፡፡ ትሑት ሰው ግን ሁሉንም ሰው ከእርሱ እንደሚሻል ያስባል፡፡ /ቅዱስ ስንባቴም/

፻፹፱. ትሕትና መድኃኒት ነው ከሰይጣን አሽከላ ያድናል፡፡

/አባ እንጦንስ/

፻፺. ፍጹም ትሕትናም በሐሰት የተናገረውን ነገር ደስ ብሎት በመቀበል ትታወቃለች፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፺፩. እውነተኛ ትሑት በበደላት ጊዜ የማያዝን ነው፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፺፪. ሰው ትሑት በሆነ ጊዜ ይቅርታን ያገኛል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፻፺፫. ልግት ማለት መሬትን መቆፈር ብቻ አይደለም፡፡ የሰውን ልቡና በትምህርተ ወንጌል ቆፍሮ ማለምለም፣ በሰው አእምሮ ፍቅርና ስምምነትን መዝራትና መትከል፣ ሰውን ከስህተት መመለስና ማስተማር ከልማቶች ሁሉ የበለጠ ነው፡፡

/ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ/

፻፺፬. የወንድምህን ኃጢአት መስማትን ወይም በእርሱ መፍረድን ለራስህ አትፍቀድለት

/ቅዱስ ኢሳያስ/

፻፺፭. ምስጋናና /እግዚአብሔርን ማመስገንና/ ትህትና ሰውን በምድር ላይ ያለ መልአክ ያሰኙታል፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፻፺፮. የቤትህ በራፍ ሰባት ክንድ ያህል ከፍታ ቢኖረውም እንኳ ራስህን ዝቅ አድርገህ ግባበት፡፡

/እንጋረ ፈላስፋ/

፻፺፯. የትሑት ሰው መዝገቡ በልቡናው ውስጥ ነው፡፡ ይኸውም እግዚአብሔር ነው፤ እንድም የትሑት ሰው ክብሩ በልቡናው ውስጥ ነው ይኸውም እግዚአብሔር የሚሰጠው ነው፡፡

/አረጋዊ መንፈሳዊ/

፻፺፰. ኃጥእ ነኝ ማለት ብቻ እውነተኛ ትሕትና እንዳይደለ በእውነት እናገራለሁ፡፡ እውነተኛ ትህትና ትሩፋትን መሥራት ነው፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፺፱. ትሁት ሰው አጋንንትን፣ ክፉ ሰዎችን፣ እንስሳትን አራዊትን እንኳን አይፈራም፣ ትሁት ሰው ፍርሃት የሌለበት ሆኖ ይኖራል ፡፡

/ቅዱስ መቃርስ/

፪፻. የኃጢአት መጀመሪያና መንደርደሪያው ግዴለሽነት /አለ መጠንቀቀ/ ነው፡፡ /

አባ ጴሜን/

፪፻፩. ልጅ እያለሁ አንድ ቀን መልካም ነገር አደርግ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርግ ነበር፡፡ አሁን ግን ይኸው ሸመገልኩ፣ እስካሁን ግን መልካም የሚባል ነገር አላደረ ኩም፡፡

/አባ መጣል/

፪፻፪. በፈተናዎች ባልተፈተንን ጊዜ ራሳችንን የበለጠ ማዋረድ ይኖርብናል ምክንያቱም እግዚአብሔር ደካማነታችንን አይቶ እየጠበቀንና ፈተናውን እያስቀረልን ነውና፣ ራሳችንን ከፍ ካደረግን ግን ጥበቃውን ከእኛ ያርቅብንና እንጠፋለን፡፡

/አረጋውያን/

፪፻፫. መርከብ ያለ ምስማር ሊሠራ እንደማይችል ሁሉ ድኅነትም ያለ ትሕትና ሊገኝ አይችልም፡፡

/ቅድስት ሰንቀሊጢቃ/

፪፻፬. የትሕትና ከፍታ እጅግ ታላቅ ነው፣ የመታበይ ጥልቀት ደግሞ እጅግ ጥልቅ ነው፣ የመጀመሪያውን እንድት ከተል ወደዚህኛው ደግሞ እንዳትወድቅ እመክራለሁ፡፡

/አባ ኤስድሮስ/

፪፻፭. ሰውን ሊያድነው የሚችለው ብሕትውና ወይም ትጋሃ ሌሊት ወይም ማንኛውንም ዓይነት መከራ መቀበል ሳይሆን እውነተኛ ትሕትና ብቻ ነው፡፡ /አረጋውያን አበው/

፪፻፮. ምድር ከሁሉም በታች ስለሆነ ካለባት ወደ ታች አይወርድም፣ ራሱን ዝቅ የሚያደርግም እንዲሁ አይጣልም፡፡ ዝቅተኛ የሆነች ምድር ውኃን ትቀበላለች፣ ራሱን በትሕትና ዝቅ የሚያደርግም እንዲሁ ከሁሉም በላይ ይጠቀማል፣ በክርስ ቶስ ቀኝም ያለ ነቀፋ ሆኖ ይቆማል፡፡

/አባ ጴሜን/

እምነት/ሃይማኖት

፻፲፭. እምነት ማለት የስሜት ሕዋሳት በሮችን ዘግቶ በዓይነ ሕሊና ማየት መጀመር ነው።።

/ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ/

፻፲፮. እኛ ሁላችን አምላካችን እግዚአብሔር መሆኑንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ የለበሰው ቃል መሆኑን እናምናለን። እርሱ በመለኮቱና ሰው በመሆኑ ፍፁም እንደሆነ እናምናለን። አምላክነቱ ከሰውነቱ ለትጽዝት እንኳ እንዳልተለየም እናምናለን። ሰው መሆኑ ከመለኮቱ ጋር ያለ መቀላቀል ያለ መለወጥ፣ ያለ መከፋፈልና መለያየት የሆነ ነው።።

/ቅዱስ ቄርሎስ/

፻፲፱. የሚያምነውን እምነት ምንነት ላያውቅ የሚኖርን ሰው የጌታውን ቤት በማያውቅ፣ ከቤት እንስሳት በማያንስ በዱር አውሬ ይመስሉታል።።

/ሊቃውንት/

፻፳. ሰው እንደ እምኑቱ ይጠቅማል፣ እንደ እምኑቱም ይጎዳል።።

/ቲቶ ትንሽን ኃይል ጊዮርጊስ ናቸ/

፻፳፩. እናመልከው ዘንድ እኛን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን /ክብር ይግባው።። /ቅዱስ ያሬድ/

፻፳፪. ሰው ያለሃይማኖት በምግባሩ ብቻ ሊጸድቅ አይቻለውም እይገባውም፣ አስቀድሞ በማመን የሁሉ አባት እንደ ሆነው እንደ አብርሃም ሃይማኖቱን፣ ምግባሩን አንድ አድርጎ እጽንቶ ይዞ ልጁን ለመሥዋዕት አቀረበ እንዳለ።። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

ጸሎት

፻፳፫. ለአምላካችን መዓዛ ያለው ሽታ ፈጣሪን የሚያመሰግን ልብ ነው።። /ቅዱስ አትናቴዎስ/

፻፳፮. ለመጸለይ የሚያስችል እድልን ባገኘህ ጊዜ ለመጸለይ ወደ ኋላ አትበል አትቦዝንም።። ከዚህም የተነሣ ጊዜህን አላግባብ ከማጥፋት ይልቅ በጸሎት መጠቀም ትችላለህ።።

/አቡነ ጢሞቴ/

፻፳፯. እነዚህ ዅሉም ጸሎታት ግን ያለመሰልቸት በእግዚአብሔር ፊት መቆምንና ሌሎች ጸሎቶችን ከማድረስ የማያግዱ አይደሉም ።። /አቡነ ጢሞቴ/

፻፳፰. ሰው ጸሎትን በተወ ጊዜ የሞት መሣሪያውን መሥራት ይጀምራል።። /ቅዱሳን አበው/

፻፳፱. ጸሎት ለሚወዱ ሰዎች እግዚአብሔር ያድርባቸዋል ... መከራ ከሚመጣባቸው ከሚያሳዝናቸው ከሰይጣን ያሳርፋቸዋል።።

/አረጋዊ መንፈሳዊ/

፻፴. በጸሎት ልብ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ይሆናል፣ ፈጣሪውን ይመስላል።። ብዙውን ሀብት ገንዘብ ያደር ጋል።። ምሥጢራት ከእርሱ ይገኛሉ።። በጸሎት ሀብታት ምሥጢራት ይገለጽለታል።። ሀብታት ምሥጢራትን ደስ እያለው ገንዘብ ያደርጋል።።

/አረጋዊ መንፈሳዊ/

፻፴፩. የማይጸልይ ሰው ቅጽር የሌላትን ሀገር ይመስላል፣ ያን ማኽም እዮብ እንዳያጠፈው እርሱም የተነሳበትን ዐጋ ያጣል።።

/ማር ይስሐቅ/

፻፴፪. ሃይማኖት ርእይ ግዙፋን ፍጥረታትን በዓይነ ሥጋ እንድናይ በዓይነ ነፍስ የምትታይ የምሥጢር መገኛ ናት።።

/ማር ይስሐቅ/

፻፴፫. እምነት፣ ባሕርን ከፍሎ ያሻግራል፣ በበረሃ መካከል ከሚገኝ አለትም ውኃ አፍልቆ ያጠጣል።። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል የሚለው።።

/ብፁዕ አቡነ ጢሞቴ/

፻፴፯. ከሕፃንነት ያለፈ ሰው ሁሉ ለመዳን ጸሎት የግድ እንደሚያስፈልገው የሃይማኖት ትምህርት ነው።።

/ፊልክስዩስ/

፻፴፱. ለሚያገለግል ሰው ከፍጹምነት የምታደርስ የተወደዱች የተመረጠች ተልእኮ ጸሎት ናት።።

/አረጋዊ መንፈሳዊ/

፻፵፩. ሊሊት እግዚአብሔርን ለማመስገን የፈተጠረ ልዩ ጊዜ ነው።። / ቅዱስ አባ ይስሐቅ/

፻፵፫. ነፍስ የሊለው ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ጸሎትን የማታደርግ ነፍስ ሕይወት የላትም።።

/ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፵፭. ከንቱነት፣ ከትጉህ ልቡና ጋር ያለ ጸሎት የጠር ዕቃ ነው።። ነፍስ ከእግዚአብሔር አንድ ከሆነች፣ የተጋች የነቃች ከሆነች ወደ እግዚአብሔር የምትመለክት ከሆነች ንብረቷ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ይሆናል።።

/ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፵፯. ንጹሕ ጸሎት ምንድን ነው? ተብሎ ተጠይቆ ሲመለስ "ለዓለም መሞት ነው።። /ቅዱስ ዮሐንስ ዘአስዮት/

፻፵፰. ልጅ ከአባቱ እንደሚጫወት በጸሎት ከልዑል እግዚአብሔር ጋር ተጫወት።። /ማር ይስሐቅ/

፻፵፱. በእግዚአብሔር ፊት ለጸሎት ስትቆም ልክ የአሳት ፍም አጠገብ እንደቆምክ አስብ።።

/ታላቁ መምህር ይስሐቅ/

፻፶. ዕንባሕን ከመፍሰስ እንዲያቆም ከወደድህ ዘወትር ኃጢአትህን እያሰብህ በጸሎት ጽሙድ ሁን።።

/ማር ይስሐቅ/

፻፶፩. ቅዱሳን አባቶቻችን እንደሚያደርጉት አንድን ችግር በእግዚአብሔር ፊት በማስቀመጥ፣ በመጸለይና በመጾም መፍትሔ ማግኘት ይቻላል።። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፶፪. የተቆጣ ሰው ጸሎት የረከሰና ተቀባይነት ያጣ ዕጣን ነው፣ የተቆጣ ሰው መሥዋዕት ተቀባይነት የለውም።። ቁጣ የዕብደት ድርጊት ነው።። ሰዎችን እንደ አውሬዎች ያደርጋ ቸዋል ... የተቆጣ ሰው ዐይኖቹ በደም የተሞሉ ጥቆሮች ናቸው፣ የጨዋሰው ፊት ግን ብሩን ሲሆኑ ዐይኖቹም በክብር ይመለከታሉ።። /ማር አውሳሪስ/

፻፶፫. የጻድቃን መባቸው የንስሐ እንባ /የዓይኖቻቸው እንባ/ ነው።። /ማር ይስሐቅ/

፻፶፬. ኃይለኛ መድኃኒት መርዘኛ ፍጥረታትን ነትሎ እንደሚያወጣ፣ ጸሎትም ክፉ ሐሳቦችን ነትሎ ይጥላል።።

/አማሆይ ዕንጦጲጦስ/

፻፶፭. በእንተ ላይ ክፋ በሠራብህ ወንድም ላይ ለበቀል የሠነዘርከው ነገር ሁሉ በጸሎት ጊዜ በልቡናህ እየመጣ ይፈት ንሃል።። /አባ እስይ/

፻፶፮. ጸሎት የደግነት ፍሬ፣ የቁጣም አለመኖር ነው፣ ጸሎት የትሕዜና የውስጣዊ ሐዘን ማስታወሻ ነው።።

/አባ እስይ/

፻፶፯. ነገሮች ሁሉ እንት እንደምትፈልጋቸው እንዲሆኑ አትመኝ እግዚአብሔርን እንደሚያስደስቱት እንጂ እንደዚህ ከሆነ የማትታወክና በጸሎትህም ጊዜ አዘውትረህ የምታመሰግን ትሆናለህ።።

/አባ እስይ/

፻፶፰. ሁልጊዜ የሚያመሰግን እንደበት ከልኡል እግዚአብሔር ዘንድ በረከን ያገኛል።። /ማር ይስሐቅ/

፻፶፱. በጸሎት ነፍስ ከእግዚአብሔር ጋር ተዋሕዳለች የእኑቱን ምሥጢር ታየለች ደስ እያላት ሥራዋን ሁሉ በርሱ ብርሃን ታያለች የሚያሸበርቅ የጌታን መልክ በማየት ታበራለች።። / አረጋዊ መንፈሳዊ/

፻፷፩. የተናቀውን ፡ ምስኪኑን የተጨነቀውን በቃል አርዳ፣ ሁሉን በሚችል በእርሱ የቀኝ ክንድ ትረዳለህ፣ በመከራ ውስጥ ያሉትን በዘወትር ጸሎትህና በልብ ሐዘንህ ተካፈል፣ ለዋያቄ ዎችህ /ሁሉ ከምሕረት ምንጭ መልስ ታገኛለህ።። /ቅዱስ አፍሬም/

፻፷፪. ፈጣሪዬ ሆይ በፊትህ የምንቀጠቀጥና ኃይል የሌለኝ ባሪያህን እንተ አስበኝ፣ በሞገስና በቸርነትህ አትለየኝ።።

/አቡነ ቄርሎስ/

፻፷፫. ሁላችንም ኃጥአን፣ ተላላፊዎች ሆነናልና ኃጥኡን አትሞላው፣ ግድ ካዘዘስ ለእርሱ ኤልቅስት፣ ለሰናብም ጸልይለት።።

/ቅዱስ እንጦንስ/

፻፷፬. መነኮሳት በበአቶቻቸው ውስጥ የጀመሯቸውን ጸሎቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲሰባሰቡ ማጠናቀቃቸው የተለ መደ ነገር ነው።። የጋራ /ማሕበር/ የሆኑትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተጀመሩት ጸሎቶችም በበአት ውስጥ መጠናቀቃቸውም እንዲሁ፣ በቅዳሴ ላይ ተግኝተው የሚቀበሉት የቅዱስ ቁርባን ምሥጢር ግን ያለ ማቋረጥ በልባቸው ጽላት ላይ መቅረቡን ይቀጥላል።። /አባ አጽድስ/

፻፷፭. በምስጋና ቃል እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑት እንሁን፣ በዜማ የሚያመሰግኑ አሉ፣ የሚዘምሩም አሉ በልብ የሚያመሰግኑ አሉ።። /ቅዱስ አትናቴዎስ/

፻፷፮. ከእራት በኋላ ያለው ጊዜ የምስጋና ጊዜ ነው።። ምስጋናን የሚያቀርብ ደግሞ ንቁና የተረጋጋ ይሆናል።። ከእራት በኋላ ወደ ጸሎት እንጂ ወደ መኝታ እንሂድ።። ያለበለዚያ ግን በደመ ነፍስ ከሚመሩት አውሬዎች የበለጠ በደመ ነፍስ የምንመራ እንሆናለን።። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፷፯. በጸሎት ሕይወት ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ሰው በየዕለቱ ከቅዱሳት መጻሕፍት ላይ መመገቡ አስፈላጊ ነገር ነው።። /አቡነ ጢሞቴ ማለላዊ/

፻፷፰. ጸሎት ኀንዘብ ሊያስገኝ ይችላል፣ ኀንዘብ ግን ጸሎትን ሊያመጣ አይችልም

/ብፁዕ አቡነ ናትናኤል/

፻፷፱. ደዌ የሌለባቸው ዓይኖች ብርሃን ማየት መውደድ እንዲሰማቸው እንደዚሁም ሁሉ በፈሊጥ ለሚሆን ለጸም ጸሎትን መውደድ እንዲሰማቸው ማለት ጸሎትን ማዘውተር ያስማምዖል።።

/ማር ይስሐቅ/

፻፸. ጾም፣ ጸሎት ከስግደት ከምጽዋት ጋር ከሆነ የጠር ዕቃ ነው።። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፸፩. ሳንሞት እንትን ማሰብን ትጋትን አላድርብን ።።

/ማር ይስሐቅ/

፻፸፪. ከመንግሥት ሰማያት እንዳትለዩ ንስሐን ገንዘብ አድርጓት ።። /አረጋዊ መንፈሳዊ/

፻፸፫. የክርስትና ትክክለኛ ሕግ፣ ቀጥተኛ ትርጉም፣ ከፍተኛ ጉልላት ይህ ነው።። ይኸውም የሁሉ ጥቅም የሆነውን ነገር መሻት ነው /ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፻፸፬. እግዚአብሔር ሆይ ለራስህ ፈጥረኸናልና በእንተ ዕረፍት እስካላገኙ ድረስ ልቦቻችን ዕረፍት አልባ ናቸው።። ማንኛውም ዓይነት ስስት ያንተን ፈቃድ ከማወቅ እንዳይ ገታን፣ ድካማችን ፈቃድህን ከማድረግ እንዳያግደን የልብ ንጽህናንና የዓላማ ጥንካሬን ስጠን።። በእንተ ብርሃን ብርሃንን እናያለን፣ በእንተም ልዩ አገልግሎት /ጥቅቶት/ እውነተኛ ነፃነትን እናገ ኛለን።።

/ታላቁ አውግስጢኖስ/

፻፸፭. አሳቦቻችንን መጠበቅና በበዛ ፀጥታና ሰላም መጸለይ ለጸሎት መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው።። /ቅዱስ መቃርስ/

፻፸፮. ጌታዬ ሆይ! በፊትህ ምንም ዓይነት መልካም ሥራ ባልሥራም እንደ ቸርነትህ አቁመኸኛል! ስለዚህ ከአሁን በኋላ መልካም መሥራትን ስለምጀምር እባክህ እትተወኝ።።

/አባ አርሳኒዎስ/

፻፸፯. ሕሊናውን ከተዘከሮተ እግዚአብሔር ላያርቅ የሚ ተኛ ሰውን ተዘከሮው ይጠብቀዋል።። ዮሐንስ ሐሂር ሲተኛ ቅዱስ ሚካኤል ቅዱስ ገብርኤል ከንፋቸውን እኔ ልጋርድ እኔ ልጋርድ ሲሉ ያይ ነበር።። /ማር ይስሐቅ/

፻፸፰. በመከራህ ጊዜ ልቡናህን ከጸሎት ጋር አንድ ለማድረግ ተዘከሮተ እግዚአብሔር በልቡናህ ይጸናል።።

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፴፰. እግዚአብሔር ጸሎትህን እንዲይጸየፍብህ ሌሎችን አትጸየፍ፡፡ /ቅዱስ እንጦንስ/

፩፻፴፱. ጸሎት የነፍስን ተራ ስሜቶች ፀጥ ያደርጋል የቁጣን ዓመጽ ያበርዳል፡ ቅናትን ያጠፋል፡ የዓለማዊ ነገሮች ፍቅር ያመነምናል፡ ለነፍስም ታላቅ ሰላምና እርጋታን ያሰጣል፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፵. ሰው ረድኤተ እግዚአብሔርን እንዲያሻው ያወቀ እንዲሆን አብዝቶ ይጸልያል፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፩፻፵፩. ሰው በጸሎት ሁብታት ምሥጢራትን አእምሮ መንፈሳዊን ገንዘብ ያደርጋል /ማር ይስሐቅ/

፩፻፵፪. ሰውነትህን ዘወትር ለመጸለይ አትጋት፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፩፻፵፫. ወዳጄ ከጸሎት ተለይተህ ከቡር እግዚአብሔርን ርዳኝ ሳትል እግዚአብሔር በጻፋቸው መጻሕፍት ያለውን አነባለሁ እተረጉማለሁ አትበል፡፡ በመጽሐፍ ያለውን ትርጓሜ ምሥጢር የማውቅበትን ዕውቀት ስጠኝ በል እንጂ፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፵፬. ጸሎት እምላክ ባጻፋቸው መጻሕፍት የተጻፉ፡ የተረዱ የትርጓሜ፡ የምሥጢራት መሪ መገኛ እንደሆነ እወቅ፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፵፭. ታላቁንና ታናሹን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፵፮. ቅዱስ የሆነ የወንጌልህን ቃል እንድንሰማና እንዲ ሰማነው እንድንሠራ በቅዱሳን ጸሎት የበቃን የተዘጋጀን አድርገን፡፡ /ጸሎተ ቅዳሴ/

፩፻፵፯. ጸሎት ለማድረግ ወደ እግዚአብሔር ስትቀርቡ ራሳችሁን እንደ አንድ አነስተኛ ጉንዳን፡ እንደ አንድ በምድር ላይ እንደሚሳብ አነስተኛ ፍጥረት፡ እንደ አንድ ደቃቅ አልቅትና እንደ አንድ ተብታባ ሕፃን ቁጠኝ፡፡

/አባ ይስሐቅ/

፩፻፵፰. በምትጸልዩበት ጊዜ አሳባችሁ በተደጋጋሚ የሚሰ ረቅባችሁ ቢሆንም እንኳ ይህንኑ ጸሎታችሁን በድጋሚ መልሳችሁ ለማምጣት ታገሉ፡፡ በጸሎት ጊዜ ትኩረታችን ቢሰረቅብን ትጋት እንተበልም፡ ጸሎታችንን በድጋሚ መልሰን ማምጣት ከቻልን ግን ትጋታችን አይቀርልንም፡፡

/ቅዱስ ዮሐንስ/

፩፻፵፱. የንጉሥን መመለስን ነው እንጂ ሞቱን የማትወድ ሆይ አቤቱ የሚያገለግልህ ልቡናን ስጠኝ፡፡

/ቅዱስ ባስልዮስ/

፩፻፶. ቍጣን የሚያበልየው ፀሎትና ገበሬ በባህር ዘርቶ አጭዶ የሚያገኘው ምርት እኩል ነው፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፩፻፶፩. የትሕትና ስብእና መገኛ መንገድ ራስን መግዛት፡ ጸሎትና ራስን ለሁሉም ፍጥረታት የበታች አድርጐ ማሰብ ነው፡፡

/ቅዱስ እንጦንስ/

፩፻፶፪. ያለ ጸሎት ከሚፈጸም አገልግሎት ይልቅ፡ ያለ አገል ግሎት የሚፈጸም ጸሎት ይሻላል፡፡

/ዘወ አቡነ ሺኖዳ/

፩፻፶፫. ንቃት ከጸሎት ሕይወት ጋር ሊነጣጠል አይችልም ክንፍ የሌላት ወፍ እንደሌላች ሁሉ ያለ ንቃት የሚሆን የጸሎት ሕይወትም ሊኖር አይችል፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

ፈሪሐ እግዚአብሔር

በሕይወቴ ሦስት ነገሮችን ሳስብ እፈራለሁ፡፡

፩፻፶፬. እኔ በሕይወቴ ሦስት ነገሮችን ሳስብ እፈራለሁ፡፡ ነፍስ ከሥጋዬ የምትለይበትን ሰዓት ወደ እግዚአብሔር ፊት እንድቀርብ መላእክት በሚወስዱኝ ሰዓት ፊት እንድቀርብ ... ለመስማት በፊቱ ከፈጣሪም እንደበት የፍርድ ቃል ለመስማት በፊቱ የምትቆምባትን ሰዓት፡፡

/ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ/

፩፻፶፭. የንጉሡ የክብር ዘቦች በፊት ለፊቱ በተጠንቀቅ ሲቆሙ ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ አይመለከቱም ልክ እንደዚሁ አንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ሲቆመ እንደዚሁ እንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ሲቆመ ሁልጊዜ በፍርሃት ውስጥ ሆኖ እርሱን ሊመለከት ይገባዋል፡፡

/አባ ሰራፕዮን/

፩፻፶፮. በልቡ የፍሪሐ እግዚአብሔር ድምፅ የሌለው ሰው ምውት መሆኑን ይወቅ፡፡ /አባ ቀሌሜስ/

ጾም

፩፻፶፯. ስም የትሩፋት ሥራ ሁሉ መጀመሪያ የጽሙዳን ክብራቸው ናት፡፡ /ማር ይስሐቅ/

ከአቅማችሁ በላይ የሆነ ሥራ በመሥራት ሊሆን ይችላል፡፡ ቅዱሳን ይህን አስመልክተው ሲናገሩ ይህን ብለዋል ትንሽ ቀጣይ ሥራ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከሚቆም ትልቅ ሥራ ይሻላል፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፩፻፶፰. በትጋህ ሌሊት ጊዜ መቆም መስገድ ባይቻልህ አልጋህ ላይ ተቀምጠህ ሳለህ ትጋህን ያዝ ተኝተህም ቢሆን ሁለት ቀን ወይም ባይቻልህ እስከ ሠርክ ጹም፡፡ እስከ ሠርክም ወይም ባይቻልህ መጥነህ ተመገብ እስከትጠግብ እንዳትመገብ ተጠበቅ፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፩፻፶፱. ይህን ዓለም ማሰብ በመዓልት እንዲዋጋን እንዲ ሠለጥንብን የታወቀ ስለሆነ ዘወትር ጾምን ጽኑ ጋሻ ልንይዝ ይገባል፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፷. የአንደበት ጾም ከአፍ የተሻለ ነው፡፡ የልብ ከፍ ትወት መከልከል ደግሞ ከሁሉም የተሻለ ነው፡፡

/ቅዱስ ይስሐቅ/

፩፻፷፩. ጾም መከታ ነው፤ ማንኛውም ሰው የዲያቢሎስ ኃይል በጾም መመከት አለበት፡፡ /ቅዱስ እንድርያስ/

፩፻፷፪. አንድ ንጉሥ የጠላቶቹን ከተማ ለመያዝ ከፈለገ በመጀመሪያ ማድረግ ያለበት የጠላቶቹን የውኃና የምግብ መስመር ሙሉ ለሙሉ ማቋረጥ ነው፡፡ በሥጋም ቢሆን ልክ እንደዚሁ ነው፡ አንድ ሰው ሲጾም በጣም ስለሚርበው የነፍሱን ጠላቶች ፈጥነው ይደክማሉ፡፡

/ዮሐንስ ሐጺር/

፩፻፷፫. ከመብል ከመጠጥ ታቅቦ የሚጾም አንድ ሰው በሐሜት የሰዎችን ሥጋ መብላትን ከቀጠለ ይህ ጾም የማብዘኑት ነው፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፷፬. ከጾም የተነሣ እንደ ግስላ፡ እንደ ነብር የሚነሣሡ በሥጋ የሚያስቡ ፈቃዳት እንደ በግ ይለዝባሉ፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፷፭. የመብልና የመጠጥ ጸርነታቸውን /ፈታኝነታቸውን/ ልንፈራ ይገባናል፡ መብል መጠጥ፡ ጥጋብ፡ የክፉ ሥራ መጀ መሪያ እንደሆነ፡ የእንቅልፍ ብዛት ዝሙትንም ያበዛል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፷፮. ከኃጢአት ጸር ከፍትወት አንዱንም አንዱን ድል ለመንሳት ለማጥፋት በጾም መክብም፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፷፯. ጾም የሥራ መጀመሪያ ናት
የጽሙዳን ክብራቸው ናት
የድንግልና የንጽሕና ጌጣቸው ናት
የንጽሕና መገለጫ ናት
የወንጌል ሥራ መጀመሪያ ናት
የጸሎት ምክንያት ናት
የዕንባ መገኛ ናት
እርምሞን የምታስተምር ናት

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፷፰. ሰው ጾም በጀመረ ጊዜ በጾሙ ሐሊናው በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋራ መነጋገር ይጀምራል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፷፱. ጾም ገንዘብ ያደረጉትን መንፈሳዊ ሥራ ያሠራ ቸዋልና፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፸. ጾም ክብር ይግባውና ጌታችን በሠራልን በወንጌልና በኦሪት መካከል የተሠራች ሕግ ናት፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፸፩. የመንፈሳዊ አካል ማጠንከሪያ መስገድ፡ ንስሐ፡ ጾም፡ እግዚአብሔር ደጅ መቅረብ፡ ምጽዋት ነው ፡፡

/ሊቀ ትጉሃን ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኜ/

፩፻፸፪. ጾምን የናቀ ያቀለለ በጎውን ነገር ሁሉ ከራሱ አራቀ፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፸፫. ጾም የጸሎት እናት የእንባዐ ንስሐ ምንጭ እርምሞን የምታስተምር ናት፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፸፬. ኃይለኛ መድኃኒት መርዘኛ ፍጥረታትን ነቅሎ እንደሚያወጣ፡ ከጾም ጋር የተባበረ ጸሎትም ክፉ ሐሳቦችን ነቅሎ ይጥላል፡፡

/ቅድስት ወንቅሊጠቃ/

፩፻፸፭. ሁል ጊዜ የምትጾም ከሆነ በቅዕበት ራስህን ወደ ላይ አታውጣ፡ ከዚህ የተነሣ ራስህን ከፍ አድርገህ የምትመ ለከት ከሆነ ግን ሥጋ ብትበላ ይሻልሃል፡፡ ለአንድ ሰው ራሱ ን በትዕቢት ከመንፋትና ራሱን ከማክበር ሥጋ ቢበላ ይሻለዋል፡፡ /አባ ኢስድሮስ/

ራስን መግዛት

፩፻፸፮. ሀብት መልካም የሚሆነው ባለቤቱ በቅንነት በብርቱ መጠጥና ጉዳት በሚያስከትሉ ፈንጠዝያዎች ሲጠቀ ምበት ሳይሆን በመጠኑ ዘና ብሎ በሚተርፈው የድሆችን ሆድ ለመሙላት ሲያከፋፍለው ነው፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፸፯. ልቡናን መቆጣጠር፡ ራስንም ለእግዚአብሔር ሲሉ ከመሻቱ ማራቆት ነው

/አባ አጋቶን/

፩፻፸፰. በራስህ ጽድቅ አትታመን፡ ስላለፈው አትጨነቅ፡ ይልቁን አንደበትህንና ሆድህን ግዛ፡፡

/አባ ረኢሳይያስ/

፩፻፸፱. ለመኖር ያህል የሚበቃንን መመገብ ሰውነታችንን እናለማምደው እንጂ የሚያጩናንቀንንና የሚያደልበንን ለመ ብላት አይሁን፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፹. ሰው ፍላጎቱን ካላሸነፈ የእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም ከሰውም ከእግዚአብሔርም የሚያጣለው የፍላጎት መኖር ነው፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፹፩. የሥጋ ፍላጎቶችን ማሸነፍ ለእክሊለ ሕይወት የሚያበቃ ሰማዕትነት ነው፡፡

/ቅዱስ ይስሐቅ/

፩፻፹፪. ሐኬት መብል መጠጥ ማብዛት ነው፡፡ ሰው በዚህ እግዚአብሔርን ከማገልገል ይመለሳል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፹፫. ማስተማር መልካም ነው፤ ከዚህ ደግሞ ራስን ንጹሕ ማድረግ ይበልጣል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፹፬. ሰው አዋቂ ተብሎ የሚመስገነው የዚህን ዓለም ፍጻ ሜ የሚያስከብር ኃጢአትን በቃኝ ሲል ነው፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፹፭. ስጋ የሚበረታው ነፍስ በደከመችበት መስፈሪያ መጠን ሲሆን ነፍስም የምትበረታው ሥጋ በደከመበት መስፈሪያ መጠን ነው፡፡

/አባ ዳንኤል/

፩፻፹፮. መብል መጠጥ ከመታቀብ በላይ የሆነች ራስን መግዛት የወንድምን ሥጋ እና ደም ወዳለመብላት ወዳ ለመጠጣት የምታደርስ ናት፡፡

/ዮሐንስ ሐጺር/

፩፻፹፯. መብል መጠጥ ማጣት ሰውን በትሩፋት ጽሙድ ሆኖ መኖርን ያስተምሩታልና፡፡ መብል መጠጥ ብናገኝ እፋ ችንን ከፍተን እግራችንን ዘርግተን ብንበላ ብንጠጣ ሰውነታ ችንን መክኖ መኖር አይቻለንምና፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፩፻፹፰. በዝሙት ጸር በፈተና ጊዜ ሰውነትን ምግብ ነስቶ ማድከም ይገባል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፩፻፹፱. ከመብል ከመጠጥ፡ ተለይቶ መኖር ለሥጋ አይቻለውም ለነፍስ ግን ከመብል ከመጠጥ ከሌሎች ይዘይ ዘንይ ይቻለዋል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፫፻. አራዊትን መግራት ማልመድ ችሎ የነበረ ሰው እንደበቱን መግራት አልቻለም /ያዕ ፫፥፰/ የጌታን ቃል የማይፈራ እርሱ፥ ወንድሙንም "አንተም ሞኝ" የሚል ማንም የሲያል እሳት አደጋ ውስጥ ነው፡፡

/ሊቀ አውግስጢኖስ/

፫፻፩. ዘወትር የሚደረግ ኃዘንም በነፍስ ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን ማሰብ ያሳድርበታል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፫፻፪. ሰው መብል መጠጥን የተወ እንደሆነ ትሩፋት ወደ ሚሠራበት ወደ ተግቶ የተመለሰ እንደሆነ ጾር ትርቅበታለች ትጠፋለታለች፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፫፻፫. ብዙ ከመብላት የሚገኝ ሐልዮ ኃጢአት ልቡናን ከዕውቀት ዕውቀትን ከልቡና የሚለይ ነትዐ ሐልዮን ያመጣል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፫፻፬. ፈቃደ ሥጋውን ለፍቃደ ነፍስ ያላስገዛ ፈቃደ ነፍሱ ለእግዚብሔር አይገዛም

/ማር ይስሐቅ/

፫፻፭. ሰውነቱን ብዙ የሚመግባት የሚከባከባት የሚያ ስመቻት ሰውነቱን ወደ ጽኑ ፃር ያገባታል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፫፻፮. መብል መጠጥ እውነተኛና ደመኛ ጠላት ነው ፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፫፻፯. ብዙ መብልና መጠጥ ክፉ ፈቃድን ያበዛል፡፡

/ማር ይስሐቅ/

ራስን መናቅ/መግታት

፫፻፰. በራሱ የሚፈርድ ወንድሙንም የሚያከብር እርሱ ብፁዕ ነው፡፡ በሰዎች ድካመት ውስጥ የራሱን ውድቀት የሚያይ እርሱ ብፁዕ ነው፡፡

/ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ/

፫፻፱. ራስህን ጻድቅ አድርገህ እንዳታስብ ከሚመራህ ማንኛውም ሐሳብ፥ ወንድምህንም ከመናቅ ራስህን ጠብቅ፥ ምክንያቱም ሌሎችን የሚያከብር ራሱንም የሚን ቅ እጅግ ብፁዕ ነው፡፡

/ቅዱስ ዕንባቆም/

፫፻፲. በሌላው የመፍረድ ፀጋ በገጠመህ ጊዜ ኃጢአትህን አስታውስ፥ እንዲህም በል "ያሰው ከእኔ ይልቅ ፃድቅ ነው፥ ምክንያቱም እኔ እንዲህ እና እንዲያ ነገሮችን አድርጌአለሁ፥ እርሱ እኔ በወደቅሁበት ዓይነት ነገር ሊወድቅ አይችለም፡፡

/ቅዱስ ዕንባቆም/

፫፻፲፩. ምስጋና ስም እንደ ማጥፋት፥ ድህነትም እንደ ብልጽግና፥ እጦትም እንደ ማግኘት ወደ አንተ ከመጡ አትሞትም፡፡በእርግጥም በጽናት የሚያምንና በፍቅር የሚተጋ ባልጠፉ ስሜቶች ውስጥ ስለማይወድቅ የርኩሳን መናፍስት ከትክክለኛው መንገድ ወጥቶ በጥፋት ጎዳና ላይ ሊነዳ አይች ልም፡፡

/አባ መቃርስ/

፫፻፲፪. በራሳችን ላይ ብንፈርድ፥ በሌሎች ላይ አላግባብ መፍረድ የሚሆን ጊዜ አይተርፈንም፡፡

/ቅዱስ ጂሚን/

፫፻፲፫. ለኩበለሉ መዓረጋቸውን ለጣሉ ለኢጋንንት ተገዥ እንዳትሆን ተርታ ልብስ መልበስን ውደድ፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፫፻፲፬. ኃጥያት ከሰው አይርቅም ሰው ግን ከኃጥያት መራቅ ይችላል፡፡

/ሊቀ ትጉሃን ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኘ/

፫፻፲፭. ኃጢአት ሠራን ብለን የምናዝነውን ኃዘን ጸጋ እግዚአብሔር እንደበጎ ሥራ ትቆጥርልናለች፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፫፻፲፮. በኃዘን መኖር ሥጋዊ ሥራን ሁሉ ያርቃል፡፡

/ቅዱስ ጎርጎርዮስ/

፫፻፲፯. አንድ ክርስቲያን በራሱ ብቻ ሣይሆን ለሌላውም ጠቃሚ መሆን እንዳለበት ክርስቶስ በግልጽ አስተምሮናል እኛን ዓለም ጨው እርሾ እንዲሁም ብርሃን ናችሁ፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፫፻፲፰. ትዕግሥት ከሰፊ አእምሮ፥ ልበ ሰፊ ከመሆን የሚገኝ ነው፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፫፻፲፱. በመጠን የምትመገብ ሰውነት ብዙ ፍሬ እንደም ታስገኝ እንኳ ደምቢያ መሬት ናት፡፡ እንድም አብዝቶ ከመ መገብ የተለየች ሰውነት ብዙ ትሩፋት ትሠራለች ብዙ ጸጋ ክብር ታገኛለች፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፫፻፳. ቀላል የሆነውን ሸክም ወደ ጎን ጥለነዋል፥ ይህም ማለት ራስን መውቀስን ማለቱ ነው፤ በራሳችን ላይም ከባዱን ሸክም እንጭናለን፥ ይህም ራስን መከላከልና ማጽደቅ ነው፡፡

/አባ ዮሐንስ ሐጺር/

፫፻፳፩. ራስን መውቀስ የመሰለውን ቀላል ሸክም ከላያችን ላይ አውርደን ከጣልን በኋላ አሁን የተሸከምነው ራስን ማጽደቅ የተባለውን ከባድ ሸክም ነው፡፡

/ዮሐንስ ሐጺር/

አርአያ

፫፻፳፪. ከአንተ በፊት የነበሩ ነገሮችን አድንቅ ተጨማሪ ዕውቀት ለማግኘት ይህን የመጀመሪያ መሠረት አድርግ፡፡

/ቀሌምንጦስ/

፫፻፳፫. ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ መምህራችን ነው፡፡ ነቢያትም አስቀድሞ በመንፈስ እርሱን በማየት ደቀ መዛሙርት ነበሩ፡፡ /ቅዱስ አግናጥዮስ/

፫፻፳፬. የእውቀት መጨረሻው ዕውቀቱን በተግባር ማዋል ነው፡፡ /ብፁዕ አቡነ በርናባስ/

፫፻፳፭. አንዲት ክፉ ቃል መልካሙን ሰው ምንኳ ክፉ ታደርገዋለች፥ አንዲት መልካም ቃል ግን ክፉውን ሰው መልካም ታደርገዋለች፡፡ /አባ መቃርዮስ/

፫፻፳፮. ከዳር ሆነህ ስለ መነኩሳት ከምታወግዝ መነኩስና መነኩሴ መሆን ያለበትን ሁን፥ ስለ ካህናት ከምታወራ ክህነት ተቀበልና ካህናት ሊሠሩት የሚገባውን ሥራ፤ ያለበለዚያ ዋጋ የለውም ፍቱን መድኃኒት የማይነጥፍ የቤተ ክርስቲያን አካል ሆኖ መገኘት ነው፡፡ /ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ/

፫፻፳፯. ሰማዕትነት መዝገበ ቃላት ላይ ሣይሆን የሚነበበው በራሳችን ሕይወት ላይ ነው፥ የሰው ትልቁ ስንፊት አውቄአለሁ ብሎ የአእምሮውን በር መዝጋቱ ነው፡፡ / ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ/

፫፻፳፰. ሰባኪ ማለት የጠለቀ የቤተክህነት ዕውቀት ያለው ብቻ ሳይሆን በአለባበሱ፥ በአነጋገሩ ክርስትናውን የሚያንፀባ ርቅም ሰባኪ ነው፡፡ /ብፁዕ አቡነ ሺኖዳ/

፫፻፳፱. ሰባኪ ማለት በቃልም በሕይወትም ከአበው የተማረ ቱዋ የሚያስተምር ተቀምጦ የሚማር የማይነቅፍ ወይም የማ ይቱች፡፡ /ብፁዕ አቡነ ሺኖዳ/

፫፻፴. አንድ ክርስቲያን በራሱ ብቻ ማይሆን ለሌላውም ጠቃሚ መሆን እንዳለበት ክርስቶስ በግልጽ አስተምሮናል እኛን ዓለም ጨው እርሾ እንዲሁም ብርሃን ናችሁ፡፡

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፫፻፴፩. ልጆቼ እናንተ ድልድዮች ናችሁ ያውም ብዙ ከባድ ነገር በላያችሁ ተሸክማችሁ ማሳለፍ ያለባችሁ ድልድዮች እናንተ ዝላችሁ ሸክሙን መሸከም ካልቻላችሁ ብዙና ከባድ የሆነውን ከእናንተ አልፎ ዓለምን የሚጠቅመው ነገር ወደሚወ ርደው ወንዝ ወድቀ ሳይመለስ ላታገኙትም በውሃ ተወስደ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ እንዱ ሌላውን ያበረታና ሸክሙን ተሸከሙ፡፡

/አንድ አባት/

ተምሳሌት

፫፻፴፪. ቤተሰብ የመንግሥተ ሰማያት ሕይወት መታወቂያ ነው፡፡ /ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

ጥንቃቄ

፫፻፴፫. እንዴት በሚገባ መያዝ እንዳለበት እንድ ሰው ካላወቀ ሐብት አባብ ነው፡፡ እባብን ዝም ብለው ሳይጠነቀቁ ከጅርባው ጫፍ ከያዙት እጅ ላይ ተጠምጥሞ እንደሚነድፍ ሐብትም በጥበብና በጥንቃቄ ካልያዙት እንዲሁ ነው፡፡

/ቀለሚንጦስ ዘእስክንድርያ/

፫፻፴፬. ሰው ልቡን ካልጠበቀ የሰማውን ሁሉ መርሳትና መዘንጋት ይጀምራል፥ ስለሆነም ጠላት በርሱ ውስጥ ቦታ ያገኛል፥ ገልብጠም ይጥለዋል" ልክ ዘይት ተሞልቶ እንደሚ ያበራ መብራት ማለት ነው፡፡ /አባ አርሲዮስ/

፫፻፴፭. በኑሮህ ሁሉ የእንግዳ ሰው ዓይነት ልቡና ይኑርህ፤ ልክ በመጀመሪያ ያገኘሃቸው ቀን የምትሆነውን ዓይነት በጣምም አትቅረባቸው፥ በጣምም አትራቃቸው፡፡

/አባ ኢጋቶን/

፫፻፴፮. ከሰይጣን ይልቅ ልማድን ፍራ፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፫፻፴፯. ኃጥአንን ውደዳቸው በሥራ ግን አትምሰላቸው፡፡

/ማር ይስሐቅ/

፫፻፴፰. መኖሩ የታወቀ ገንዘብ እየተቀነሰለትና እያለቀ ይሄዳል፥ እንዲሁም መልካም ምግባርም በሰዎች ዘንድ ከታወቀና ከተገለጠ በእሳት ፊት ሲሆን እንደሚቀልጥ ሰም ይቀልጣል፡፡ ነፍስም በሰው የምትመሰገን ከሆነች ትደክማለች ኃይሏም ይጠፋል፡፡ /ቅድስት እማሆይ ሲንቅሊጢቃ/

፫፻፴፱. የኃጢአት መጀመሪያና መንደርደሪያው ግዴለሽነት / አለ መጠንቀቅ/ ነው፡፡ /አባ ጴሜን/

መልካም ጓደኛ

፫፻፵. ባልንጀሮችህ አንድ ሺ ሊሆኑ ይችላሉ፥ ያንተን ምሥጢር ደብቆ የሚይዘው ግን አንድ ነው፡፡

/ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፫፻፵፩. ሰዎች ሁሉ ትክክለኛ ነህ ብለው ቢያምኑህ እንኳ እውነቱን በመናገር ስሕተትህን የሚገልጥልህ እርሱ ባልንጀራህ ነው፡፡ /አንድ ሊቅ/

፫፻፵፪. ከመልካም ባልንጀራ ጋር ከሆንክ በመንፈሣዊ ሕይወትህ ወደፊት ትራመዳለህ ነገር ግን ከክፉ ባልንጀራ ጋር ከሆንክ ትወድቃለህ ወይም አንድ እርምጃ ወደ ኋላ ትመለሳለህ፡፡ /ቶቀድሞ አባቶች/

፫፻፵፫. ማንነትህን እንድነግርህ ከፈለግህ ጓደኛህን ንገረኝ፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፫፻፵፬. ድንግሊቱ ሔዋን የእባብን ቃል ሰምታ አለመ ታዘዝንና ሞትን ፀነሰች፥ ወንድሙን የሚገድለውን ልጅ ገዳይ ቃየልን ወለደች፡፡ ድንግል ማርያም ግን የብርሃና ዊውን መልአክ የቅዱስ ገብርኤልን ብስራት ሰምታ ታዛዥ ሆነች /እንደቃልህ ይሁንልኝ አለች ሕይወት ክርስቶስን ፀነሰች ለሕዝቡም የሚሞተውን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደች፡፡

/ሰማዕቱ ቅዱስ ዮስጢኖስ/

፫፻፵፭. ስለ አንተ ድካመት የሚነግርህን ሰው ጥሩ ባልንጀራ አድርገህ ያዘው፡፡ /ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፫፻፵፮. ከዝሙት ትለይ ዘንድ ከዘማውያን ራቅ፡፡

/ማር ይስሐቅ/

ተግሳጽ

ቸ፪፵፯. ተግሳጽ በመጨረሻ በኃጢአት ጥልቅ ውስጥ ገብተን እንዳንሰጥም የሚጠብቀን የሕሊችን ቅዱስ መልሕቅ ነው።

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

ደስታ

ቸ፪፵፰. ደስታን እንድናገኝ የነገሥታት ንጉሥ ሁሉን በእጁ ይዞ የሚገዛ አብ አንድ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ ምክር እኛን በማዳን ተሰቀለ።

/ቅዱስ ዮሐንስ/

ቸ፪፵፱. ወንድሞቻችን ሆይ ክፋ ሰዎች በዚህ ዓለም በተድላ በደስታ ሲኖሩ አይተን በተድላ በደስታ የማያኖሩቸው ምክንያቶቹን በጠይቃቸው አይደለምን ብሎ ማለት እንዳይገባ፡ በጎ ሰዎች በዚህ ዓለም በመከራ ሲኖሩ አይተን በመከራ የሚያኖሯቸው ሃይማኖታቸውን ምግባ ራቸውን ባይወድ ጎቸው አይደለምን ብለን ልቦናችን ተስፋ እንዳይቆርጥ መሆን ይገባናል። በጎውም ሆነ ክፋው የምግባር ዋጋ ከዚህ ዓለም አይደለምና። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

⇒ ከክፋ ሰዎች ተድላ ደስታ ሲያደርግ ያየነው ሰው ቢኖር ልቡናችን አይጠራጠር እንደነዊ ያለ ነው። በጎውን ሰው ተሻግሮ ስናየው እንሸበር እንደ አልአዛር ያለ ነው።

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

ቸ፪፻. ለአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመናት መርገመ ኃጢአት ተይዞ፡ በሞት ጥላ ሥር ወድቆ፡ በሁለንተናዊ ሕይወት አዝኖና ተክዞ የነበረው የሰው ልጅ በብሥራተ ፍጹም ደስታንና መጽናናትን አገኘ።/ቅዱስ ያሬድ/

ቸ፪፻፩. ቤተ ክርስቲያን የፍግ እሳት ናት ጠፍታለች ሲሏት ሕያው ትሆናለች።

/ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ/

ቸ፪፻፪. ሰውን ብትታገልና ብትዋጋ ታሸንፈዋለህ ወይም ያሸን ፍሃል፡ ቤተ ክርስቲያንን ግን ማሸነፍ አይቻልም። ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ትዋጋለች፡ ተሸንፋም አታውቅም፡ ዲያቢሎስ ዝናሩን አራገፈ ቀስቱን ጨረሰ፡ ቤተ ክርስቲ ያንን ግን አልጎዳትም።

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

ቸ፪፻፫. የጠፋ በግ አዳምን የፈለገው ባገኘውም ጊዜ የተሸከመው እውነተኛ ቸር ጠባቂያችን ክርስቶስ ነው።

/ተአምረ ማርያም/

ቸ፪፻፬. ሳትደክም ሁሉን ትሸከማለህ፡ ሳታንድል ሁሉን ትመግባለህ፡ ሳትዘነጋ ሁሉን ታስባለህ፡ ሳትተኛ ሁሉን ትሰማለህ፡ ሳትበቀል ሁሉን ይቅር ትላለህ።

/ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ/

ቸ፪፻፭. ወደ ንጉሥ የቀረበን ሰው ጠላቱ ሊያገኘውና ሊጎዳው እንደማይችለው ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የቀረበን ሰውም ዲያብሎስ ምንም ሊያደርገው አይችልም። ነገር ግን ው ጊዜ ራሳችንን ከፍ ስለምናደርግና ድካማችንን ስለማናስ ጠላት እኛን ወደ ታች ለመጣልና ወደ አሳፋሪ ኃጢአ ለማውረድ አይቸገርም።

/እንድ አረጋዊ/

የእግዚአብሔር ጥበቃ/እርዳታ

ቸ፪፻፩. ዲያብሎስ ዝናሩን አራገፈ ቀስቱን ጨረሰ ቤተ ክርስቲያንን ግን አልጎዳትም። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

ቸ፪፻፪. ሁሉም ከእኔ ነው ሁሉም በእኔ ነው እንተም በሁሉ አለህ በግናናነትህ ከልዑላን ይልቅ ልዑል ነህ።

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

ቸ፪፻፫. ለበጎተኛው የሚጠቅመውን የሚያውቅ ሐኪሙ እንጂ በሽተኛው አይደለም። /ቅዱስ አውግስጢኖስ/

ቸ፪፻፬. ሕይወታችን በተፈጥሮ ያልተረጋገጠና በየዕለቱ በእግዚአብሔር ቸርነት የሚታደስልን ነው። /ጴጥሮስ/

ቸ፪፻፭. በእግዚአብሔር ቸርነት የምትሠራ ሥራ ስትጀምር ጥቂት ናት፡ ኃላ ግን በሥራ ትሰፋለች። /አረጋዊ መንፈሳዊ/

ቸ፪፻፮. የእኔን ባርነት እንተ አትፈልገውም እኔ ግን የእንተን ጌትነት አሻዋለሁ። /ቅዱስ ገርጎርዮስ/

ቸ፪፻፯. እንተ ሰማይን ለእኔ እንደ ጣሪያ አዘጋጅተህልኛል እራመድባትም ዘንድ ምድርን አደላድለህልኛል። እንተ ባሕሩን አርግተህልኛል አውራውንም ለማዳ አድርገህ ልኛል። ከቡርና ድንቅ ከሆኑት ሥራዎችህ አንዳችም ያስቀ ህ ነገር የለም።

/ቅዱስ ገርጎርዮስ/

ቸ፪፻፰. ለቤተ ክርስቲያን ስትል በአደባባይ በጥፊ የተመታህ፡ አቤቱ ይህን ማድረግህ እርስዋን በክብረ ደምህ ትቀድሳት ዘንድ ነው። ለስዋ ሲል ታሥሮ መንተት የቻለ፡ የበደለውም በደል ሳይኖር ርኩስ ምራቅን ሲተፋብት የታገሠ አምላክ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ። /ቅዱስ ቁርዮስ/

ጥበብ

ቸ፪፻፱. ጠላትህን የምታስወግድበት መንገድ እርሱን ባልን ጀራህ አድርገህ በመቀየር ነው።

/ዮሐንስ አፈወርቅ/

ቸ፪፻፲. አንድ ጠቢብ ሰው "ዝምታን የተማርሁት ከለፍላፊ ሰው ነው" ብሏል ይህም ማለት የመለፍለፍን ጉዳት መገንዘቤ የዝምታን ጥቅም እንዳውቅ አድርጐኛል እንዲህ ያለውን መጥፎ ጠባይም እንዳስወግድ ረድቶኛል።

/ቅዱስ እንጦንስ/

ቸ፪፻፲፩. መጻሕፍትን ካነበባችሁ እነርሱን እንዴት እንደም ትድኑ ይነግሯችኋል፡ ያድኗችኋል።

/አባ እንጦንስ/

ቸ፪፻፲፪. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት በተሰበሰቡበት በተዘጋ በር ገባ። በመሀላቸውም ተገኘ፡ ጌታችን በተዘጋ በር እንዴት እንደገባ ስትነግረኝ እኔም በድን ግልና ወንሳ መውለዴን እነግርሃለሁ።

/አባ ጀሮም/

ቸ፪፻፲፫. የሰብኩት ጥበብ ሰውን ወደ ሕይወት መጥራት ነው።

/መልአኩ ሰላም ዳኖቹው ካኖውን/

ቸ፪፻፲፬. ከፈላስፎች እንዱ እንዲህ አለ ነፍሴ ሦስት ነገሮችን ጠላች፡ ተወየፈች እነርሱም ይህ ሲሆን ትዕቢተኛነ፡ ባለፀጋ ሲሆን ሐሰተኛነ፡ ሽማግሌ ሲሆን ዕብድን ናቸው።

/እንጋረ ፈላስፋ/

ዝምታ/እርምጥ

ቸ፪፻፫. መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ እንድናጠናው እና በጥልቀት እንድንመረምረው እንዲሁም አስቀድመን የማናውቃቸውን ሐብቶች እንድናገኝ ያደረጉንን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥርጣሬ ያነሱትን ሁሉ እናመሰግናቸዋለን።

/ቅዱስ አትናቴዎስ/

ቸ፪፻፬. እውነት እንዳልናገር የዚህ ዓለም ሰዎች ጠሉኝ፡ ሐሰትም እንዳልናገር ፍርድህ ያስፈራኛል ከሁሉ ግን ዝም ማለት ይሻለኛል።

/ቅዱስ ይስሐቅ/

ቸ፪፻፭. ዝምታ ሃይማኖትን ትጠብቃለች።

/መጽሐፈ መነኮሳት/

ቸ፪፻፮. ከጸር መዳንን የምትወድ ከሆነ በአርምሞ ሁልጊዜ ደስ ይበልህ።

/መጋቢ ሐዲስ አቡቱ/

ቸ፪፻፯. በልቡና የምትታሰብ ትዕቢት ሁልጊዜ በነፍስ መከራን ታመጣለችና።

/ማር ይስሐቅ/

ቸ፪፻፰. ወንድሜ አርምሞን ትጠብቀህ ዘንድ ያገ ነ በዝምታ ሕይወትን ታገኛለችና። /

/ማር ይስሐቅ/

ቸ፪፻፱. ውስን ዛፎች መልካም ያልሆነውን ፍሬ ያፈራሉ ውስኑ ደግሞ መልካም ፍሬን ያፈራሉ። ማንም ቢሆን መጥፎውን ጥሩ ጥሩውንም መጥፎ በማለት ራሱን ኢያታልል። ያለምርምር ነገሮች ሁሉ ግልጽ ሆነው ይታያሉና፡ በነዚህ ነገሮች ራሳችንን ልናታልል እንችልም።

/ሊቁ አውግስጢኖስ/

ቸ፪፻፲. በራስህ ኃጢአቶች ላይ የማታተኩር ከሆነ፡ እነር ሱንም በማሰብ የማትጠይቅ ከሆነ በሌሎች ሰዎች ኃጢአት ውስጥ ትወድቃለህ።

/ማር ይስሐቅ/

ቸ፪፻፲፩. ልብህ የራስህን ኃጢአት ያስተውል ይመርምር ያስብ።

/ማር ይስሐቅ/

ቸ፪፻፲፪. ይህ ትውልድ ብዙ ቦታ ሲሄድ ወደ ራሱ ያልሄዱ፡ ሌላውን ሲመለከት ወደራሱ ያልተመለከቱ፡ ብዙ ነገር ሲያውቅ ያላወቀ ትውልድ ነው።

/መጋቢ ምሥጢር አባ ወርቅነህ/

ራስን መመርመር

ቸ፪፻፭. ሁሉን ያወቀ ራሱን ማን የማያውቅ ሁሉን አጣ።

/ቅዱስ አትናቴዎስ/

ቸ፪፻፮. በአሳብህ፡ በእንደበትህ ወይም በሥራህ ከእውነት የምትርቅ ከሆንህ ደግሞ ከእግዚአብሔር እየተለየህ ነው ።

/አቡነ ሺኖዳ/

ቸ፪፻፯. በሌሎች ላይ እርማትን ከመሰንዘር በፊት የራሳ ችንን ስህተት ማረም ይጠቅማል።

/ባስልዮስ ዘቂሳርያ/

ቸ፪፻፰. ሰው ወደ እግዚአብሔር በቀረበ መጠን የዝ ኃጢአቱ ይታየዋል።

/አባ መጣሕ/

ቸ፪፻፱. በእንድ ሰው በተተችህ ጊዜ እንተም በውስጥህ ራስህን ውቀሰው፡ በውስጥና በአፍአ ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ እንድትችል።

/ማር ይስሐቅ/

ቸ፪፻፲. በዝ ዐይኑ ያለውን ምሰሶ የሚመለከት፡ በወንድሙ ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ የሚመለከትበት ጊዜ የለውም። በሌሎች ላይ የሚያየውን ድክመት የማያስተካክል ሰው ለራሱም መንፈሳዊ መስታወትን አግኝቷል። ሌሎች ስሕተት እየሠሩ መሆናቸውን ስናስተውል፡ እኛም ያንን ስሕተት እየሠራን እንዳያሠሩን ራሳችንን መመርመር አለብን። ሌሎች የተወገዙበት ተግባር በእኛ ዘንድ ካለ ራሳችንን እናስተካክላለን።

/ቅዱስ አፍሬም ሶርያዊ/

ሰማዕትነት/ምስክርነት/ተጋድሎ

ቸ፪፻፲፫. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የማይናገሩ /መናገርን የሚፈሩ/ ሰዎች ለእኔ የመቃብር ድንጋዮች እና የሞቱ ጣዖቶች ናቸው። /ቅዱስ አትናቴዎስ/

ቸ፪፻፲፯. በሰማዕታት ዘመን የሞት ቅጣት ብቁላ ሆኖ ቢለወጥም ቅዱሳን በጸጋ አድርገው ለውጠውታል፡ በዚህም በረከቱንና አክሊሉን ተቀብለዋል። /አቡነ ሺኖዳ/

ቸ፪፻፲፰. ሻማ ለሌሎች ብርሃን ለመስጠት ይቀልጣል፡ ለሌሎች ሲል መሥዋዕት ይሆናል ማለት ነው። በቅድሳን ሰዎች ሥዕላት ፊት ሻማዎች የምናስቀምጥበት ምሳሌ ይህ ነው። /አቡነ ሺኖዳ/

ቸ፪፻፲፱. አዲስ ችግኝ በውሃ ሕይወት የሚያገኘውን ያህል ገድለ ቅዱሳንም ለክርስቲያን ሕይወት የሚሠጥ ጣፋጭ ምግብ ነው። /ማር ይስሐቅ/

ቸ፪፻፳. ኃላፊነት ያለብኝ የቤተ ክርስቲያን አባት ነኝ። ስለ ሀገሬና ስለ ቤተ ክርስቲያን እቆረቆራለሁ። ከዚህ በቀር ለእናንተ ችሎት የማቀርበው ብር የለኝም። ለፈጣሪም ብቻ የምናገረውን እናገራለሁ በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ ተከታዮቼን ግን አትንኩ።

/ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ/

ቸ፪፻፳፩. የመልካም ተጋድሎ ሕይወትን ዋጋ ስጥ፡ አክብረ ውም፡ የውዳሴ ከንቱ ተገዢ ግን አትሁን፡ ያኛው የማይጠፋ ይሽኛው ግን ፈጥኖ የሚያልፍ ነውና።

/አባ አስድሮስ/

፪ጴጥ፲፱. ሰማዕታትን እራሱ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀምሶ ባርኮ ለክርስቲያኖች የሰጠው ስለሆነ ስለ ስሙ ብለው በተግባር የሚፈጽሙት የመጨረሻው ደረጃ ነው።

/ቅዱስ ፖሊካርፕስ/

፪ጴጥ፲፫. ሰማዕታት በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት የተመረጡ ዕንቁዎች እህሊሎች ናቸው።

/ቅዱስ ፖሊካርፕስ/

የማዳመጥ ክህሎት

፪ጴጥ፩. ማድመጥ በሥራ ባይደገፍ እንኳ እድምጥ! ከማድመጥ ሥራ ሊከተል ይችላልና። ሥራ ባትጀምር እንኳ ስለ ኃጢአት ትህ ታፍራለህ። አሁንም ሥራ ባትጀምር እንኳ ያለህበት ሁኔታህ ይለወጣል። እንደገና አሁንም ሥራ ባትጀምር ሥራ ባለመጀመርህ ራስህን መርገምህ ወይም ማውገዝህ አይቀርም።

/ጵሐንስ አፈወርቅ/

ነፃ ፈቃድ

፪ጴጥ፪. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃዱ የሰዎች ድኅነት መሆኑን ተናግሯል። ነገር ግን ሰው መዳንን ካልፈቀደ ራሱን ወደፈቀደበት ይጨምራል።

/ባስልዮስ ዘቂሳርያ/

፪ጴጥ፪. ያለ እግዚአብሔር ጸጋ ምንም ማድረግ አንችልም! እግዚአብሔርም በፈቃደኝነት ካልተረባንለት ምንም ማድረግ አይችልም። /ቅዱስ መቃርዮስ/

፪ጴጥ፭. ቁጡ ብስጩ አትሁን፣ ቁጣ ነፍስ ወደ መግደል ያደርሳልና።

መከራ

፪ጴጥ. ችግር እና መከራ የሌለበትን ህይወት ፈጽሞ አትመኙ የምታተርፉት ምንም ነገር የለምና ።

/ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. ችግር መከራ የሌበትን ሕይወት ፈጽሞ አትመኙ የምታተርፉት ምንም ጥሩ ነገር የለባትምና።

፪ጴጥ. ክፋትን እየሠሩ በኃጢአት የሚኖሩ የመጨረሻው ፍርድ ከመምጣቱ በፊት በዚህኛው ሕይወታቸው ቅጣት አለባቸው።

/ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. መከራ ስለ መጣብህ አትዘን፣ መከራን መጥላት ምልክቱ የነፍስ ሕጸጽ ነውና። /ማር ይስሐቅ/

፪ጴጥ መከራን በመከራነቱ ሳይሆን በመካሪነት ውደደው

/ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. ያለመከራ የሰይጣን ጸር በምንም በምን አይቀርም አይጠፋም። /ማር ይስሐቅ/

፪ጴጥ፩. ክርስትና የመከራ፣ የፀዋትወ መከራ ገዳም ነው። ክርስትና ገድል ከተለየው ከንቱ ይሆናልና።

/ሊቀ ትጉሃን ኃይለ ጊዮርጊስ ዳኜ/

፪ጴጥ፲፪. ያለመከራ ከሚሠራ ብዙ ሥራ ስለ እግዚአብሔር ጥቂት መከራ መቀበል ይበልጣል። /ማር ይስሐቅ/

፪ጴጥ፲፫. አሠቃዩን፣ ሰቀሉን፣ ነቀፋን፣ ክኅንን፣ አቃጠሉን፣ የእናንተ ክፋት ግፍና ቋንቋ የእኛ ንጽሕና ማረጋገጫ

ምክንያተኝነት

፪ጴጥ፲. ከዘማዊት ጋር ዝሙትን የፈጸመ ዘማዊት እርያ ወደ ገዳሟ እንደመራችውና ምክንያት አድርጎ ቢጎትት እድድንም። /ባስልዮስ ዘቂሳርያ/

ቁጣ

፪ጴጥ. ቁጣ የበርታ አመራ ነው። /ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. ተቆጣ ሰው ሙት ቢያስኘግ እንኳ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አያኖረውም፣ ሰዎችም እርሱን እንደሚገ ትም። /ዕዝራ ሶርያዊ/

፪ጴጥ. ቁጣ የሰውን ምሬት በመሳ ሰውነት ላይ ያሰራጫል።

/ዕዝራ ሶርያዊ ዘኦርቶዶክስ/

፪ጴጥ. ቁጣ ሰው ራሱን ይገድላል። በወቀሳ እንግዳና ሰውነቱ ዘንጊዘው የሚጠወልግበት በሽተኛ ይሆንበታል። መንፈስ ቅዱስን ሰለሚያሞ በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላ ያደርጋል።

/ዕዝራ ሶርያዊ ዘኦርቶዶክስ/

፪ጴጥ. ቁጣ ምንድር ነው? ቁጣ ለብቀላ የሚሆን ፍላጎት ነው እኛ እንደምንፈጽመው ጥቃት እግዚአብሔር በእኛ ላይ በቁጣት የተሞላ የብቀላ እርምጃ ሊወስድብን ባይፈልግም እኛ ለራሳችን ብቀላ በመጠየቅ በየዕለቱ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንሠራለን።

/አባ አጋቶን/

፪ጴጥ. ቁጡ ሰው ምንም እንኳ ሙት የማስነሣት ችሎታ ቢኖረው በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ተቀባይነት የለውም ።

/አባ አጋቶን/

ነው። እናንተ በወገራችሁንና በቆረጣችሁን ልክ ቁጥራችን እልፍ ይሆናል፣ ደመ ሰማዕታት የክርስቲያኖች ዘር ነው።

/መርመሰኤ/

፪ጴጥ. የዕውቀት ደግነቱ ከሁሉ ጋር መስማማትና መግባባት ነው፣ የማይቻለውን እሸከማለሁ የሚል ሰው ለመሸከም የሚችለውን ያጣል። /አንጋረ ፈላስፋ/

፪ጴጥ. ማር ብታገኝ በመጠን ተመገብ አብዝተህ ተመግ በህ እንዳይወጣብህ የመዓር ጽጋብ እንዲሉ እንደዚሁ ሁሉ ጸጋ ቢሰጥህ በተሰጠህ ጸጋ አመስግን ያልተሰጠህን እንዳታማ። /ማር ይስሐቅ/

፪ጴጥ. በሰጡት ጸጋ የማይኖር ሰው ቅጽር የሌላትን ሀገር ይመስላል ብሎ ያን ማንም እያነሳ እንዲዘርፈው እሱም የተሰጠውን ጸጋ ያጣል። /ማር ይስሐቅ/

፪ጴጥ. እኛ ጥቂት እናውቃለን ብዙን ግን መርምሮ ማወቅ አይቻልም። እንደተፃፈ ከጥልቅ ባህር ጥቂት ውኃ እንደመጠጣት እኛም እንዲሁ እግዚአብሔርን ከማወቅ ወገን ጥቂት እንናገራለን።

/ገዳማናት አበው/

፪ጴጥ. ዕድገት የማናሳይበት ምክንያት ዓቅማችንንና ልካችንን ስለማናውቅ ነው። እንዲሁም በጀመርነው ሥራ ስለማጽናና የመልካም ምግባር ሕይወትን /ዮትድስና ሕይወትን/ እንዲሁ ያለ ድካም ማግኘት ስለምንፈልግ ነው።

/አባ አጋቶን/

፪ጴጥ. በልቦና የምትታሰብ ትዕቢት ሁልጊዜ በነፍስ መክራን ታመጣለች። /ማር ይስሐቅ/

፪ጴጥ. ሰውነትህን ዕለት ዕለት በመከራ ፈትናት።

/ማር ይስሐቅ/

፪ጴጥ. በመከራው ጊዜ እግዚአብሔርን ማመስገን ከሚችል ሰው የሚበልጥ ቅዱስ ሰው የለም። /ጵሐንስ አፈወርቅ/

ጠቅላላ ሥነ ምግባር

፪ጴጥ. ነፍስ በተፈጥሮ ባሕሪዋ ስትገኝ በንጽሕና ትኖራለች እንደተሠራን ሆነን ስንገኝ በጽድቅ እንኖራለን።

/አባ እንጦንዮስ/

፪ጴጥ. ያለ እግዚአብሔር ጸጋ ምንም ማድረግ አንችልም፣ እግዚአብሔርም በፈቃደኝነት ካልተረባንለት ምንም ማድረግ አይችልም። /ቅዱስ መቃርዮስ/

፪ጴጥ. ሰው ትንሿ ዓለም ነው። በንጽሕና ሆኖ ራሱን ሲያይ በዓለም መስታወትነት እግዚአብሔርን፣ ያያል ሰውነቱን መንፈሳዊ ሲያደርግ በዙሪያው ያሉትን ሁሉ መንፈሳዊ ማድረግ ይቻለዋል። /ሊቀ ጳጳስ ካሊስቶስ ዌር/

፪ጴጥ. የነፍስ ምግቧ ቃለ እግዚአብሔር ነው።

/ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. እውነተኛው የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜና ዶክማ /ትምህርተ ሃይማኖት/ የሚገኘው በእውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ብቻ ነው። የቤተክርስቲያን ትውፊት ርዕሰ የሆነው የአበው እምነት እንዳይበረዝ የሚጠብቅ አጥር ነው።

/ቅዱስ ሲፕሪያን/

ቤተክርስቲያን በጸጋው ትመላለች። /ቅዱስ ሄሬኔዎስ/

፪ጴጥ. ወጣቶች ምሳቸውን ጥቂት ዳቦ ይመገቡ መጠጥ ግን በሞራሽ አይጠጡ በሰውነታቸው ያለውን ትርፍ የፈተና ፈላሽ ደረቅ ዳቦ ይመጠዋልና።

/ቅዱስ ኔሬኔዎስ/

፪ጴጥ. እንተ ካስፈለገህ እና ሁለት ጊዜ ከተጠየቅህ በመጠኑ ተናገር መልስህም በጥንቃቄ እና በዕውቀት ባጭሩ የሰዎችን አዕምሮ የማያሰጨንቅ ይሁን።

/ቅዱሳኒመሰ ዘአስክንድርያ/

፪ጴጥ. ሴቶች በክርስቶስ መዐዛ ምዑዛን ይሁኑ እንጂ በቆዳ ቅባትና በሽቱ አይደለም። /ቅዱሳኒመሰ ዘአስክንድርያ/

፪ጴጥ. ሰነፍ ሰው ሲሰቅ ይጮሃል /ድምፁን ከፍ ከፍ ያደርጋል/። /ቅዱሳኒመሰ ዘአስክንድርያ/

፪ጴጥ. የሚስት አክሊሏ ባሏ ነው። የባልም ጋብቻው። ሁለቱ የጋብቻቸው /አንድነታቸው/ አበባም ልጃቸው ነው። ይህም አሠራር በመለኮታዊ መሪነት ከሥጋ እርሻ የተገኘ ፍሬ ነው። /ቅዱሳኒመሰ ዘአስክንድርያ/

፪ጴጥ. ሞኪኔ የተመላ ጠላትነት በሰው ላይ የሚፈጽመ ቁጣን የተመሉ ሰዎች ከመርዛማዎች የዱር እንስሳት ጋር አንድ ናቸው ኢሳያስም እኒህን ዲዳ ውሾች ይላቸዋል።

/ባስልዮስ ዘቂሳርያ/

፪ጴጥ. ከምቀኝነትና ከክፋት የሚከፋ ምንም ነገር የለም።

/ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. አንድ ሰው በራሱ ላይ ጉዳት ከሳመጣ በቀር

፪ጴጥ. የመናፍቃን የክህደት ቀስት ዓላማው ዶግማችንን መበረዝ ነው፣ ለዚህ ተግባራዊ መሆን ከሚጠቀሙበት መንገድ ደግሞ እውነተኛው እምነታችንን፣ ሐዋርያዊ ትውፊታችንን ማጣጣል እና ማናናቅ እንዱ ነው።

/ቅዱስ ባስልዮስ/

፪ጴጥ. ትውፊታችንን በክርስትና ጉዞአችን መጠቀማችን የግድ ነው። ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለሁሉም ነገር እልተጻፈምና፣ አባቶቻችን ሐዋርያት ሃይማኖትን ለኛ ያወረሱን በጽሑፎቻቸውና በትውፊታቸው ነው።

/ቅዱስ ኢሬኔዎስ/

፪ጴጥ. ፊሪሳው ያን በክብቶች ግርግም ተኝቶ የማይበላ ወይም ከብቶችን የማያስበላ ውሽን ይመስላሉ። /ቅዱስ እንጦንዮስ/

፪ጴጥ. ሰው በቀመሳቸው ጊዜ ከሚመሩ ፍሬዎች /ከመና ፍቃን ትምህርት/ ሽሽ እነዚህ ፍሬዎች የእግዚአብሔር አብ ተክሎች አይደሉምና። /ቅዱስ እንጦንዮስ/

፪ጴጥ. ዲያቢሎስን እትፍሩ ስራውን ግን ፍሩ።

/ጸሪኛው ሄርማን/

፪ጴጥ. አራዊት ሰውን በመርዛቸው እንደሚነዱና እንደሚገድሉ ኢታላዞችና ሐሚተኞች እንዲሁ ይነዳሉ ይገድላሉም።

/ጸሪኛው ሄርማን/

፪ጴጥ. ተግሳጽ ነፍስን በመልካም ምግባር ለማጠናከር ምክንያታ ነው። /ታላቁ ባስልዮስ/

፪ጴጥ. ቤተ ክርስቲያን በምትገኝበት ቦታ የእግዚአብሔር መን ፈስ ይገኛል። የእግዚአብሔር መንፈስ በሚገኝበትም

ማንም ሊጎዳው አይችልም። /ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. መራትሁን ከመባል ያነሰ የውርደት ቋንቋ የለም ሰው አምላክ ሆነ ከመባል በላይ የሚበልጥ የክብር ቋንቋ የለም /ሰው የገጠመውን ውርደት እና ያገኘውን ክብር በማድነት/ የተናገረው ቃል ነው። /ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. ፍጡራንን መርምሮ ማወቅ ካልተቻለ ሁሉን የፈጠረ እርሱን መርምሮ ማወቅ እንደምን ይቻለናል ።

/ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. ቤተክርስቲያን በጥምቀት አማካይነት አንድ የሆኑ የክርስቲያኖች የትንሳኤያቸው እና የድኅነታቸው ምንጭ የክርስቶስ አካል ናት። /ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. ሀብትን እናወግዘውም ከሀብት በስተጀርባ ያለውን ትዕቢትን ግን እናወግዛለን።

/ጵሐንስ አፈወርቅ/

፪ጴጥ. ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ መሥራት አለብን።

/አባ እንየው/

፪ጴጥ. በአንድ ቃል አንድ ሰው ደስ ማሰኘት ትችላለህ፣ በሌላ ቃል ደግሞ ልታሳዝን፣ ልታበሳጭ፣ ልታሸብር ወይም ጠላት አድርገህ ልትቀይረው ትችላለህ።

/አቡነ ሺኖዳ/

፪ጴጥ. አንተ ሊሎችን ነፃበርህ ሊሎች አንተን ያከብሩሃል።

/አቡነ ሺኖዳ/

፪ጴጥ. ኃጢአት መሥራት ማለት ለእግዚአብሔር ታማኝ አለመሆን በእርሱ ላይ ማመፅና ትእዛዙቱን መተላለፍ ማለት ነው። /አቡነ ሺኖዳ/

፪ጴጥ. ዓለምና ሕይወት በትምህርት የተሞሉ ቃላት

ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፬፻፶፪. ኃጢአት ማለት ከእግዚአብሔር መለየት ከእርሱ፣ ከፍቅሩና ከመንግሥቱ መቆራረጥ ማለት ነው፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፬፻፶፫. ወደ ገዳም የሚደረግ የጉብኝነት ጉዞ ለማየት ወይም ለመንሸራሸር የሚደረግ ጉዞ አይደለም፣ በረከትና መን ፈሳዊ ጥቅም ለማግኘት የሚደረግ ጉዞ እንጂ፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፬፻፶፬. ወደ ገዳም ስትገቡም ሆነ ወጥታችሁ ስትሄዱ መንፈሳዊ ጥቅማችሁን እንዳታጡ የጉብኝት ጊዜያችሁን ከጓደኞቻችሁ ጋር በሳቅና በቀልድ አታባክኑት፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፬፻፶፭. በጾም ወቅት ራስን መግዛትና ሥጋን መቆጣጠር አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፬፻፶፮. ሳትዘሩ ምርት የምትመለከት ከሆነ ትጸጸታለህ የመዝሪትን ጊዜ አባክነሃልና፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፬፻፶፯. አንድ ክፉ ሰው ድል ነሣሁ ብሎ ሊያስብና ለክፉ ቢችልም በገዛ ራሱ ትዕቢት ወድቋልና በእርግጥም ድል ተነሥቷል፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

፬፻፶፰. ለጸሎት የምትቆሙ ከሆነ ጸሎታችሁን አንድ ነገር በመሻት አትጀምሩት፣ የምትጸልዩት ስለምትፈልጉት ነገር ብቻ በማሰብ ይሆናልና፡፡ /ቅዱስ ባስልዮስ/

፬፻፶፱. በውስጤ ማንኛውንም ነገር መመኘትና ማንኛውም ነገር መፍራት እንደሌለብኝ ሲሰማኝ በዓለም ላይ እቀመጣለሁ፡፡ /ሊቀ እውግስጢን/

... ሐሜት የሚታማውን ግደሆን የሚጎዳው የሚያማውን ... ሰው ነው፡፡

... ጥቂቶችን ብቻ ይሰማል፣ እግዚአ ... የፈለገውን ሁሉ ይሰማል፡፡

... ጠላትነት በሰው ላይ የሚፈጸመ ... ከመርዛማዎች የዱር እንስሳት ጋር ... እነዚህን ዱዳ ውሾች ይላቸዋል፡፡

... በመልካም ምግባር ለማጠናከር

... ዘወ አካል ላይ ኃጢአትን በሚሠራበት ... ቅዱስ እየለየ ነው፡፡ /አቡነ ሺኖዳ/

... በእኔ ዘንድ መራር የምለው ... እንደ እንቅልፍ ነው፣ ነገር ግን ስለ ... በእናንተ ዘንድ መራር ይሆንባችኋል፡፡

... በደል በአንደበታቸው ነው፣ የኃጥአን ... ሰውነታቸው ነው፡፡ /አባ ኢሳይያስ/

... ብረትን ለመቀጥቀጥ የሚሄግ ሰው አስቀድሞ ... ለመሥራት እንዳሰበ መወሰን አለበት፣ መጥ ... እኛም በምን ዓይነት የሕይወት ... ለማፍራት እንዳሰብን አስቀድመን ... ማዘጋጀት አለብን፡፡

፭፻፪. ዲያብሎስ ቀስቱን ጨረሰ ዝናሩንም አራገፈ ቤተ ክርስ ቲያንን ግን አልጎዳትም፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፭፻፫. ጸጋ ክብር ለማግኘት ምግባር ትሩፋትን አብዝቶ ለመሥራት የሚወድ ሰው ቢኖር አስቀድሞ ከዓለማዊ ግብር መለየት ይገባዋል፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፭፻፬. በእግዚአብሔር ቃል በስተቀር በልባችንም ሆነ በአንደበታችን ውስጥ ሌላ ምንም ነገር የለም፡፡ በመሆኑም በገነት የምንደሰት እንጂ በምድር ላይ የምንኖር መሆና ችንን አይታወቀንም፡፡ /አባ ቴዎድሮስ/

፭፻፭. በማንም ላይ ክፉትን አትሥሩ፣ አትፍረዱ፣ ይህንን ከጠበቃችሁ ድኅነትን ትወርሳላችሁና፡፡ /ቅዱስ መቃርዮስ/

፭፻፮. የነፍስ ምግቧ ቃለ እግዚአብሔር ነው ፡፡

/ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፭፻፯. ልዑል እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን "እንዲህ ብለህ ጻፍ፣ እንዲህ ብለህ ተናገር" እያለ ድምጹን እያሰማ፣ በራዕይ እየገለጠ በልቡና እየቀረጸ እንዲጻፍ በማድረጉ "መጻሕፍተ እምላካውያን" ተብለዋል፡፡

/የትርጓሜ መምህራን/

፭፻፰. የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ /የነቢያት ትንቢትን ሊገልፅና ሊያብራራ የሚችለው ቀድሞውኑ መጽሐፋቱን ያጻፋቸው የጌታ መንፈስ ነውና፡፡ /ቅዱስ ጎርጎርዮስ/

፭፻፱. ለመናፍቅ ተናግሮ ለሆዳም ጋግሮ ላያበቁ መጻረቁ፡፡

/መምህር ደጉ ዓለም ካሣ/

፭፻፲. መናፍቅ ውኃ ሲወስደው "ድሮም ቆላ መኖር ሐሳብ ነበረኝ" አለ ይባላል፡፡ /መምህር ደጉ ዓለም ካሣ/

፭፻፲፩. የመናፍቅ ትርጓሜና የትምባሆ ልምላሜ አንድ ነው፣ ከመቃጠል ሌላ ረብ የለውምና፡፡ /መምህር ደጉ ዓለም ካሣ/

፭፻፲፪. የሚታበይ ሰው ይናቃል፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፭፻፲፫. ለወንድሙ የሚንቀፍበትን ስም የሚያወጣን ፈታኢ በርትአ እግዚአብሔር እንዲሰደብ ያደርገዋል በሌላ አድሮ ያሰድበዋል፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፭፻፲፬. ለነፍስ በእውነት በክብረ ሥጋ በክበረ ነፍስ ከባሕ ርያችሁ የተገኘን ልጆቻችሁ ነን እነሆ ልጆቻችሁ እኛን ኃጢአት እንደ እሳት ሆና በላችን ፈቃደ ሥጋም አቃጠለችን የሥጋ ፍቃድ ብቻም አይደለም የደማዊት ነፍስን የሚጎዳ /የሚያስኮንን/ ነው እንጂ፡፡

/ቅዱስ አትናቴዎስ/

፭፻፲፭. ክርስቲያናዊ ፍጹምነትን ለማግኘት የምትፈልግ ከሆነ ሕሊናህን ለነፍስህ ከማይጠቅም ወሬ መጠበቅ አለብህ /አቡነ አትናስዮስ/

፭፻፲፮. ጸሎት ለማድረግ ወደ እግዚአብሔር ስትቀረቡ ራሳችሁን እንደ አንድ አነስተኛ ትንዳን፣ እንደ አንድ በምድር ላይ እንደሚሳብ አነስተኛ ፍጥረት፣ እንደ አንድ ደቂቅ አልቅትና እንደ አንድ ተብታባ ሕጻን ቁጠሩ፡፡ /አባ ይስሐቅ/

፭፻፲፯. አንቺ ቀራንዮ ጎልጎታ ሆይ! በአንቺ የዓለም መድኃኒት ተሰቀለ፡፡ /ቅዱስ ያሬድ/

፭፻፲፰. በሌሎች የሚፈርድን ሰው መንፈሳዊ ሳይሆን ስሜታዊ ነው፡፡ /ማር ይስሐቅ/

/አባ እንጦንስ/

፬፻፹፰. እግዚአብሔር ስላዳነን የምናመሰግነው ምስጋና ከደረሰብን ችግር ስለማያጋልጠው ስጦታዎቹን ለሰጠን ለእግዚ አብሔር ባይሆን ለተሰጡን ስጦታዎች ብቻ ይሆናል፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፬፻፹፱. የእኛ ጥሩ መዓዛ ግን ሽቱ ሳይሆን መልካም ሥራ ሊሆን ይገባል፡፡/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፬፻፺. እያንዳንዱን ሰው መመልከት ያለብን ውጪያዊውን አለባበሱን ሳይሆን ውስጣዊ አመለካከቱን ወይም አስተ ሳሰቡን ነው፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፬፻፺፩. እግዚአብሔር አዳምን ከገነት ካባረረው በኋላ ይኖር ዘንድ ያስቀመጠው ከገነት ፊት ለፊት ነበር፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ገነትን በተመለከታት ቁጥር መከራውን እንዲያስብና ስለ መውደቁ ግልጽ የሆ እውቀት እንዲኖረው ነበር፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፬፻፺፪. እኛ በአገልጋይ ባልንጀራችን ዋጋ ላይ የምንመ ራመርና የምንጠይቅ ከሆነ እግዚአብሔር ደግሞ በእኛ ላይ እንደዚሁ ያደርግብናል፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፬፻፺፫. እያንዳንዱ ቅጣት በኃጢአተኞች ላይ ከመጣ የኃጢአት ሸክማቸውን ያቀልላቸዋል፣ በጻድቃን ላይ ከመጣ ደግሞ ነፍሶቻቸውን የበለጠ ድንቅ ያደርግላቸዋል፡፡ የሚያስ ልገውም መከራን ከምስጋና ጋር መቀበል ስለሆ ታላቅ ጥቅምን ያገኛሉ፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፬፻፺፬. ሲኦል እምነት ላላቸው በግልጽ የምትታይ ስትሆን እምነት በሌላቸው ዘንድ ግን አትታይም፡፡/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፬፻፺፭. ወዳጆቹ እውነተኛውን ሹመትና ምርቃት ልብን ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስነት ማስመረቅ ነው፡፡ እግዚአ ብሔር በመጨረሻው ቀን የሚጠይቀን የስልጣና ክህነታ ችንን ድርሻ ሳይሆን የልባችንን ንጽሕና ነው፡፡

/አቡነ ሺኖዳ ግልላዊ/

፬፻፺፮. በቀደሙት ጊዜያት ምእመኑ የሚቀድስ ካህን፣ የሚያወድስ መዘምር ካገኘ ይበቃው ነበር፣ ዛሬ ግን ቤተ ክርስቲያን ለእኅለ ሙታን ማሳደጊያ በቤተ ሕሙማንና በእረኞውያን መጠርያ ተከባ ማየት ይሻል፡፡

/ብፁዕ አቡነ አስጢፋኖስ/

፬፻፺፯. ከፊቱና የሚሸሽ ከእግዚአብሔር ይሸሻል፡፡

/አባ ጳውሎ/

፬፻፺፰. አንድ ሰው በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ እንዳለ ካወቀና እግዚአብሔር ሁሉንም ያከናውንልኛል ካለ ልቡ ፍጹም ይሆናል፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፬፻፺፱. እምነት ባሕርን ከፍሎ ያሻግራል፣ በበረሃ መካከል ከሚገኝ ዓለትም ውኃ አፍልቆ ያጠጣል፡፡ በዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል የሚለው፡፡

/አቡነ ሺኖዳ/

፭፻. የእግዚአብሔር ቃላት የነፍስን ሙቀት ያድሳሉ፡፡ እንድታድግ ከፈለግህ የእግዚአብሔርን ቃላት እንደ ሕፃን ልጅ መጥባት አለብህ፡፡

/ቅዱስ አትናቴዎስ/

፭፻፩. የምትናገረው ነገር ሁሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት የራቀ ማስረጃ ሊኖረው አይገባም፡፡

/ቅዱስ እንጦንስ/

፭፻፲፱. መሪዎቻቸው ደካሞች ምእመናን ግን ደጎች ናቸው፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ በካህኑ ላይ አይመካም፡፡ ይህንንም የምለው የቄሱን ሕይወት በመመርመር ስለከበረ ትእዛዙ ማንም ሰው እንዳይጠራጠር ነው፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም ነገር የሚደረገው በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በኩል ጸጋን በሚያድል በእግዚአብሔር ስለሆነ ነው፡፡

/ሊቀ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፭፻፳. ከቅዱሳት መጻሕፍት የምሥጢር መዝገብ እናንተን ሳልመገብ /ሳላስተምር/ አንዲት ቀን እንኳን እንድታል ፍብኝ አልፈቅድም፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፭፻፳፩. ሰውን ከአምላክ ጋር የሚያገናኝ ጥልቅ የሆነ ፍላጎትን በሁሉ የሚፈጥር ፍልስፍና የዚህ መንገዱ ደግሞ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ብቻ ማንበብ ነው፡፡ /አቡነ ቄርሎስ/

፭፻፳፪. እሳት ከአንተ ወጥቶ ሌሎችን የሚያቃጥል ወይም ስለ እርሱ ስለተቃጠሉ ነፍሳት እንደሚጠይቅህ እወቅ፡፡

/ቅዱስ ይስሐቅ/

፭፻፳፫. ኃጢአትን መደበቅ በራሱ ኃጢአት ነው፡፡

/አባ ቀውስጦስ/

፭፻፳፬. እባብ በወሬው ለሔዋን ከገነት መጥፋት /መሰደድ/ ምክንያት እንደሆነ ወንድሙንም የሚያማ እንዲህ ነው፡፡ እንዲህ ያለው ሰው ለሰሚዎቹ ነፍስ መጥፋት ምክንያት ይሆናል፡፡ እባብ ከእርግማኑ እንዳላመለጠ የዚህም ሰው የራሱ ነፍስ ከጥፋት አያመልጥም፡፡ /ቅዱስ ኤፍሬም/

፭፻፳፭. ከድንግል ማርያም በተዋሕዶ ሰው የሆነው መድኃኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ የሕይወት መገኛ

የበረከት ሥጋ ወነፍስ ምንጭ ነው፡፡ /ቅዱስ ያሬድ/

፭፻፳፮. የእመቤታችን ቅድስት ማርያምን የአምላክ እናትነት በትክክል የማያምንና የማይቀበል ሁሉ ከአምላካዊ ጸጋ ዕድል ፈንታ፣ ጽዋ ተርታ የለውም፡፡

/ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ/

፭፻፳፯. እኛ አንድ ሰው ስናከብር ሰው ሁሉ ያከብረናል፣ አንድ የሆነው እግዚአብሔርን ስንጠላ ደግሞ ሁሉም ሰው ስለሚጠላን እንጠፋለን፡፡ /ዮሐንስ ሐጺር/

፭፻፳፰. በነፍስ ድንቁርናን የሚያመጣ ልስማ ልስማ፣ ልናገር ልናገር ማለት ነው፡፡ /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፭፻፳፱. ቤተ ክርስቲያን የምታገናኝ ናት፣ ሕዝብንና ሕዝብን የምታዋሕድ አንድ የምታደርግ፡፡

/ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ/

፭፻፴. ስላደረገልህ ፍቅር ባንተ ዘንድ ግሩም ይሁን፡፡

/ቅዱስ ቄርሎስ/

፭፻፴፩. ሊታናሽ ኃጢአት መቆምን ቸል የሚል ሰውን በታላላቁ ይቆማል ብለው አይመኑት፡፡ /ባስልዮስ ዘቂሳርያ/

፭፻፴፪. በሕይወታችን በድርጊታችን የሚደረግ ትምህርትና ምክር የበለጠ ኃይል ያለው አስተማሪ ነው፡፡

/መጋቢ ምሥጢር አባ ወርቅነህ/

፭፻፴፫. የሰውነት መሞት የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው፡፡ የነፍስ መሞት ማለት ግን የነፍስ ከእግዚአብሔር መለየት ነው ፡፡

/ሊቀ እውግስጢኖስ/

፭፻፴፬. ሀብታምና ድኃ የሚባሉት አንዳንድ እንጀራ ስለሆን የሀብትና የድኅነት ልዩነት አለኝና የለኝም ማለት ብቻ ነው፡፡ /አንጋረ ፈላስፋ/

፩፻፵፩. አገልግሎትን የሚያስወድደው አስደሳችነቱ እንጂ ብዛቱ አይደለም:: /እንጋረ ፈላስፋ/

፩፻፵፪. ከዕለታት አንድ ቀን ጥቂት የሆኑ ነገሮች ለመሸጥ ወደ ገበያ ወጥቼ እንዳለሁ ንዴት ሲቀርበኝ ተመለከትሁት "በዚህ ጊዜ ያመጣኋቸውን ነገሮች እዚያው ትቼ ወደ መጣሁበት ተመልሼያለሁ!" /አባ አልደር/

፩፻፵፫. ተማሪዎች በትምህርታችሁ ጥሩ ውጤት የምታመጡትና ነገ ትልቅ ደረጃ የምትደርሱት ዛሬ የተቀመጣችሁበት ወንበር እስኪያልበው ድረስ ተግታችሁ ያጠናችሁ ከሆነ ነው" /ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ/

ትጋት

፩፻፵፬. ሰውን ሞት እንጂ ሥራ አያሸንፈውም :: /አባ እንጦን/

፩፻፵፭. መጀመር ቀላል ነው፤ ብርታት የሚያስፈልገው ግን መቀጠል ላይ ነው:: /አቡነ ሺኖዳ/

፩፻፶. ለእግዚአብሔር ራሱን የሰጠ ሰው ፀሐይ ንጋት ላይ ስትወጣ በእጆቹ ላይ መጽሐፍ መገኘት አለበት:: /ቅዱስ አትናቴዎስ/

፩፻፶፩. አጋንንትን ድል ትነሣ ዘንድ:: ልቡናህ ዘገ አይሁን ተዘክሮተ እግዚአብሔርን አትተው:: /ማር ይስሐቅ/

ስንፍና

፩፻፶፪. ሰው የያዘውን የሚጥለው ሲያንቀላፋ ነው:: /ብፁዕ አቡነ በርናባስ/

፩፻፶፫. ምኞት የቁም ሕልም ነው፤ ሕልምም በሐሳብ ተፀንሶ በቅዠት የሚወለድ ነው:: /እንጋረ ፈላስፋ/

መስቀል

፩፻፶፬. ዓለም የክርስቶስን መስቀል አይገፋው የማይገፋ ነውና:: ቀድሞ አይሁድ የክርስቶስን መስቀል እንደ ቀበሩት ዛሬም መስቀል በአደባባይ ላይ እየተጣለ እየተወረወረ ነው:: መስቀሉ በሠሪዎቹ እየተደበቀ ነው:: ዛሬ መስቀሉን የምታወጣ እሌኒ ታስፈልገናለች:: ያለመስቀል ሰላም የለም:: ረኀቡ፣ ጦርነቱ እንዲጠፋ የተሰወረውን መስቀል ማግኘት ያስፈልጋል:: /ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ/

ውዳሴ ከንቱ

፩፻፶፭. ዝናው ከሥራው በላይ የገነነበት ሰው ያልታደለ ነው:: /አባ ጎልምናስ/

፩፻፶፮. ከመጠን በላይ የሚመሰገንና የሚከበር ሰው ብዙ ኩነኔ ያገኘዋል:: በሰው ዘንድ እቁም ነገር ሳይቆጠር መልካም ሥራ ያለፈ ሰው ግን በሰማይ ታላቅ ክብር ይጠብቀዋል:: /አባ አውር/

፩፻፶፯. አቦ አቦ ከመባል የተለየ ሰው ሰውነቱን ትመጣ ዘንድ ላላት ለመንግሥተ ሰማያት አበቃን:: /ማር ይስሐቅ/

፩፻፶፰. እግዚአብሔር የሚወዳችሁ እግዚአብሔርን የምትወዱት እናንተ ክብር የሚያስገኝ ስለሆነ ውዳሴ ከንቱ ከመውደድ ትለዩ ዘንድ እማልዳችኋለሁ:: /አረጋዊ መንፈሳዊ/

ተልእኮ

፩፻፷፩. የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ተግባር ለእያንዳንዱ ሰው እናታዊ ክትትል ማድረግና የድኅነት አገልግሎት መስጠት ነው:: /አቡነ ሺኖዳ/

፩፻፷፪. ወጣቶች የሌላት ቤተ ክርስቲያን ራእይ የሌላት ነገ የሚባል ቀን የሌላት ነገን የማትናገር ቤተክርስቲያን ናት :: /አቡነ ሺኖዳ/

በጎ ኅሊና

፩፻፷፫. ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሥራ ሁሉ መጀመሪያ በጎ ኅሊና ነው:: /ማር ይስሐቅ/

ከምኞት መራቅ

፩፻፷፬. የሰዎች ገንዘብ የሆነውን ነገር ከረሳኸው በሰዎች ትወደዳለህ:: /አቡነ ሺኖዳ/

፩፻፷፭. ከዓለማዊ ግብር መለየት ከእግዚአብሔር ጋር አንድነትን ፈጥሮ ያመጣል:: /ማር ይስሐቅ/

፩፻፷፮. ምግባር ትሩፋትን በመሥራት ረቂቅ የሚሆኑ ሀብታት ምሥጢራትን ሊያገኝ የሚወድ ሰው ቢኖር አስቀድሞ ከዓለማዊ ግብር መለየት ይገባዋል:: /ማር ይስሐቅ/

፩፻፷፯. በዓበይት ኃጣውእ እንዳትሰነካከል ከንኡሳን ኃጣውእ ተከልከል:: ንኡሳት የሚላቸው ማየት፣ መስማት፣ ያለመጠን መብላት፣ መጠጣት ናቸው:: /ማር ይስሐቅ/

ክህነት

፩፻፸. የሚከፍትበት ቁልፍ በሐዋርያት አማካይነት ለመርዓቱ /ሙሽራይቱ/ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣት የማሠርና የመፍታት ሥልጣን ነው:: /ቅዱስ ሺኖዳ/

የሐሳብ መከፈል

፩፻፸፩. ልብ የሚሸጥ ቢሆን ኖሮ ዛሬ በረከሰ ነበር፤ ሰው ሁሉ ልብ አልፈልግም ብሏልና:: /ብፁዕ አቡነ ሰላማ/

ብዕል ሠፋጢት /የምታስት ሀብት/

፩፻፸፪. ገንዘብ ሕሊናን ይገዛል ይሸጣልም :: /አቡነ ሺኖዳ/

፩፻፸፫. ቤተሰብ ትንሽ መንግሥተ ሰማያት ነው:: /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፸፬. ገንዘብ እሬሳ ነው እሬሳን ሁሉ እንዲያነሳው ገንዘብም ወድቆ ሲያነሱት የእገሌ ነኝ አይልም ስለዚህ ስጡ ይሰጣችኋል:: /ብፁዕ አቡነ በርናባስ/

፩፻፸፭. ይህን ዓለም ማሰብ ፈጽሞ ከክቡር እግዚአብሔር መለየት ነው:: /ማር ይስሐቅ/

መንፈሳዊ ሕይወት

፩፻፸፮. መንፈሳዊው ሕይወት ወደ እግዚአብሔር የሚደረግ ቋሚ ጉዞ ነው:: ወደ ዘላለማዊነት የሚደረግ ቀጣይ እምነትም ነው:: /አቡነ ሺኖዳ/

፩፻፸፯. ትዕግሥት የመልካምነት ዘውድ ነው:: /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፸፰. ከሥጋ ጋር የማትሞትና የማትበሰብስ ነፍስ በሥጋችን እንዳለን እናስታውስ:: /ቴሐዋርያት አመክንዮ/

መታዘዝ

፩፻፹፩. የእንጨት ፍሬን በመብላት ባለመታዘዝ ምክንያት የመጣውን ሞት ኢየሱስ ክርስቶስ በመታዘዝ በእንጨት /በመስቀል/ ላይ ተሰቅሎ ሞትን አስወግዶ ሕይወትን ሰጠን:: /ቅዱስ ሄሬኔዎስ/

፩፻፹፪. ከእግዚአብሔር ለመራቅ ሔዋን በክፉ መልአክ ተታላ በትዕዛዙ ላይ ሸፈተች:: ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ግን በመታዘዝ እግዚአብሔር ወልድን እንደምትወልድ ብስራትን ከብርሃናዊው መልአክ ከቅዱስ ገብርኤል ሰማች:: /ቅዱስ ሄሬኔዎስ/

፩፻፹፫. መታዘዝ መታዘዝን ይጠራዋል:: አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ሲታዘዝ እግዚአብሔር ደግሞ ልመናውን ይሰማዋል:: /አባ መቃ/

ኅሊና

፩፻፹፬. ሰዎች ከሚወቅሷቸው ዳኞች ይልቅ የገዛ ሕሊናቸው እየወቀሰ የሚያሰቃያቸው እጅግ ብዙ ናቸው:: /እንጋረ ፈላስፋ/

ትምህርተ ሃይማኖት

፩፻፹፭. ድንግል ማርያም የብሉይ ኪዳን ተስፋ የተፈጸመባት ዳግማዊት ሔዋን የሕይወት ሁሉ እናት /ዘፍ ፫፥፳/ የሚለው ቃል የተፈጸመባት ናት:: /ቅዱስ የሐናን/

፩፻፹፮. ኢየሱስ ክርስቶስ ድል አድራጊ ንጉሥ ነው የምንለው ተሰቅሎ ሞቶ ስለተነሳ ስላየሁት ብቻ አይደለም

እርሱ ለዘመናት ድል አድራጊ ነውና:: /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፹፯. የእግዚአብሔር ቃላት የነፍስን ሙቀት ያድሳሉ:: እንድታይም ከፈለግህ የእግዚአብሔርን ቃላት እንደ ሕፃን ልጅ መጥባት አለብህ:: /ቅዱስ ጎርጎርዮስ/

፩፻፹፰. በምድረ በዳ ብቻውን ለመኖር የሚመኝ ሰው ከሦስት ተቃዋሚ ነገሮች ነፃ ሊወጣ ይገባዋል:: እነርሱም መስማት፣ መናገርና መመልከት ናቸው:: ከእነዚህ ለላ የሚቃረነው ተቃዋሚ ቢኖር ዝሙት ነው:: /አባ እንጦንስ/

፩፻፹፱. ድንግል ማርያምን ለማክበር የሚቃወሙ ሰዎች የምሥጢረ ሥጋዌ ምሥጢር እና ትምህርት ያልተረዱ ናቸው:: /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፺. የእምነት መሠረቱ የእግዚአብሔር ለፍጥረቱ መገለጥ ነው:: ለፍጥረቱ ራሱን በፈጣሪነቱ ባይገለጥ ኖሮ በፈጣሪና በፍጡር መካከል በእምነት መገናኘት አይኖርም ነበር:: /ቀሲስ ታደለ አይደከሌ/

፩፻፺፩. ማንም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምን ፀረ ክርስቶስ ነው ማንኛውም በመስቀል ላይ መከራ መቀበሉን የማያምን ዲያቢሎስ ነው:: ማንም የክርስቶስን ትምህርት ለራሱ እንዲመቸው የሚያጣምም እና ትንሣኤና የመጨረሻ ፍርድ የለም የሚል ይህም የሰይጣን የበኩር ልጅ ነው:: "ክርስቶስ ኢየሱስ ኃጢአት ያልፈጸመ በአንደበቱም ሐሰት ያልተገኘበት በመስቀል ላይ መከራን በመቀበል ኃጢአታችንን ተሸከመ ነገር ግን እኛ በእርሱ እንኖር ዘንድ በመስቀል ላይ መከራን በመቀበል ኃጢአታችንን ተሸከመ:: /ቅዱስ ፖሊካርፕ/

፩፻፺፪. ከተግባረ ሥጋ ከተግባረ ነፍስ አስቀድሞ ሃይማኖትን ሊማሩ ሊሰሙ ይገባል:: /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፺፫. ከባሕርይ አባቱ ከእግዚአብሔር አብ ጋር በቅድምና የነበረ ዘላለማዊ አምላክ በማኅፀን ማርያም በግዕዝ ሕፃናት ተፀነሰ:: /ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ/

፩፻፺፬. ኢየሱስ ክርስቶስ የማይጠልቅ ፀሐይ፣ የማይጠፋ መብራት፣ በቅዱሳን ላይ ዘወትር የሚያበራ ፀሐይ ነው:: /ባስልዮስ ዘቂሳርያ/

ትዕግሥት

፩፻፺፭. ከቁጣ፣ ከችኮላና ከጥድፊያ ራስህን ትቆጣጠራለህ፡፡ ፈጥነህ አትናገር፤ ፈጥነህም አስተያየት አትሰንዝር ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ ጣልቃ አትግባ:: እርግጠኛ ባልሆንክበት ነገር ላይ ውሳኔ አታስተላልፍ:: /አቡነ ሺኖዳ/

፩፻፺፮. ቍጣን መቻል ታላቅ ቅድስና ነው፤ በቍጣት ሐሴት ማድረግ ደግሞ የሚበልጥ ቅድስና ነው:: /አቡነ ሺኖዳ/

፩፻፺፯. በአጋጣሚ ነገሮች ላይ ንግግራችን በጥንቃቄ የተመጠነ መሆን አለበት ሌሎች ከውዳሴ ከንቱ እንዳንደገፍ ቢጠይቁንም በአርምሞ እንቀመጥ:: /ቅዱስ ቀሌምንጦስ/

፩፻፺፰. በማኅፀን ውስጥ ያለው ሽል ከመወለዱ በፊት ብዙ ወራቶች እንደሚፈልግ ሁሉ፤ እኛም መንፈሳዊ ሽል ያለ ጊዜው እንዲወለድ ሳይሆን በሚገባ እስኪደርስ

ድረስ ትዕግሥተኞች መሆን አለብን:: /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፩፻፺፱. በክፋትና በተንኮል መልኩ ማንኛውም ሰው በአንተ ላይ ቢቆጣ ስህተቱን በትዕግሥት ተቀበል እንጂ አንተም በመቆጣት እርሱ እንደሆነው በመሆን የተቆጣውን ሰው መስታወት አትሁን:: /ባስልዮስ ዘቂሳርያ/

፪፻. በሥጋችን እንደ ጌታ መቅደስ መጠበቅ አለብን:: /ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮም/

፪፻፩. መከራ በተደጋጋሚና በፍጥነት ሲደርስባችሁ ግራ መጋባትም ሆነ መበሳጨት የለባችሁም:: ይልቁንም መጨረሻውን በትዕግሥት ጠብቁ:: የሚደርስባችሁን መከራ ሁሉ ከምስጋና ጋር ከተቀበላችሁት መጨረሻው ያለ ምንም ጥርጥር የእግዚአብሔርን ታላቅ ቸርነት የሚያስጥ ነው:: /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፪፻፪. ትዕግሥት ከሰፊ አእምሮ፣ ግብ ሰፊ ከመሆን የሚገኝ ነው /ማር ይስሐቅ/

፪፻፫. ወርቅ በእሳት እንደማይጠፋ ትዕግሥት ያለው ሰውም ከመራ ወይም ፈተና አይጠፋውም፤ እሳት ወርቅን ምን ያደርገዋል? ከሚያጠራው በቀር ትዕግሥት ያለው ሰውም እንዲሁ ፈተና ምን ያደርገዋል? የከበረ ከፍ ከፍም ያደርገዋል እንጂ:: /ቅዱስ ያሬድ/

ምርጫ

፪፻፬. በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር መሆን አይችልም /ቅዱስ አርሴንዮስ/

፪፻፭. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃዱ የሰዎች ድኅነት መሆኑን ተናግሯል:: ነገር ግን ሰው መዳንን ካልፈቀደ

ራሱን ወደፈቀደበት ይጨምራል /ዕንባቆም ዘቈጽር/

፭፻፯. ቤተ ክርስቲያን በምትገኝበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ይገኛል፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በሚገኝበትም ቤተ ክርስቲያን በጸጋው ትመላለች፡፡ /ቅዱስ ሄሬኔዎስ/

፭፻፮. የዘለሩ መጻሕፍት ክርስቶስ ሰው እንደሆነ እንዲነግሩን አምላክም እንደሆነ ይነግሩናል፡፡ /ቅዱስ ሄሬኔዎስ/

፭፻፯. ጋብቻ እግዚአብሔርን ሳያስቀድም በሁለቱ ጥንዶች ስሜታዊ ፍላጎት ላይ ብቻ ከተመሠረተ ጋብቻው ቁሳዊ ይሆናል፡፡ /አቡነ ሥሉ ገብጻዊ/

፭፻፰. ለአንተ መልካም ምን እንደሆነ አታውቅም፡ ጤንነት ወይም ሕመም ሊሆን ይችላል፡፡ /ቅዱስ ባሲልዮስ/

፭፻፱. እኛ የተሻለውን ነገር በክፋ እንለውጥም ነገር ግን ክፋውን በመልካም እንለውጣለን፡፡ /ቅዱስ ፖሊካርፕስ/

፭፻፲. አንድ ሰው በሠሜት የወንድሙን ሥጋ ከመብላት የወንድሙን ደም ከመጠጣት ይልቅ ሥጋ ቢበላ ወይንም ቢጠጣ ይሻላል፡፡ /ቅዱስ አፈየስ/

፭፻፲፩. የንጉሥ ኃይል ከሙሉ ሥልጣን ጋር አንዱን ሀገር ወደ ውስጥ ሊላውንም ወደ ውጭ በማለት የሚያዝ ነው፡፡ እኛም ኃጢአትን የማራቅ ጽድቅን የማቅረብ ምርጫ አለን፡፡

/ቅዱስ ይስሐቅ/

፭፻፲፪. ምስጋና ስም እንደ ማጥፋት፡ ድህነትም እንደ ብል ጸምና፡ ኤጥም እንደ ሞያኖት ወደ እንቱ ከመጡ አንሞኖ፡፡ በእርግጥም በጽናት የሚያምንና በፍቅር የሚተጋ ባለጸጋ ስሜቶች ውስጥ ስለማይወድቅ በርኩሳን መናፍስት ኃይል

ለኛው መንገድ ውጥ በጥፋት ጎዳና ላይ ሊጎዳ አይችልም፡፡ /አባ መቃርዮስ/

ማስተዋል

ማስተዋል የራሳችሁን ለማቅረብ፡ የተረበውን ለማራቅ የሚያስችል የአብ መንገድ ነው፡፡ /አጋሪ ፈላስፋ/

ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ይችል ዘንድ ደግሞ ልብህን ዝም አሰኘው፡፡ /ዮሐንስ ዘሰዋስው/

ሥርዓት

በመሠረቱ ሰዓት አሳሪ ጸሎት በመጀመሪያም ሊትጸለየው ቸኮል ይሆናል፡፡ ሥጋህ የሚያስፈልገውን ምግብ ሥጋ ሲሆኖ ጸሎቱም ለነፍስህ ምግብ ይሆናል፡፡ ከዚህም ሌላ በምግብ ጊዜ ሊናገር የሚገባውን የገበታ ሥርዓት ትጠብቃለህ፡፡ /ዮሐንስ ዘሰዋስው/

ጸሎት በሦስትዮሽነት ውስጥ ማንኛው ሰው ሊያናግርህ ቢፈቅድ ወደ መረዘሽ እንዲተመራ ጸጥ በማለት መልስ ሳለመስጠት አትሞክር፡፡ ሳናገረህ ሰው እስኪናገር መልስ ሰጥተህ ወደ አፈራጮችህ ጸሎት ተመለስ፡፡

/ዮሐንስ ዘሰዋስው/

ዕለት ሰንበት የዕረፍት ቀን ናት ሲባል በደጋ እንደ ተደገ ሰው ከአለጋ ተማብኩ ተኝቶ መዋል አይደለም፡፡

/ዮሐንስ ዘሰዋስው/

ለዘች ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊ አርአያ ያለው የመላ እነት ሥርዓት አሳት ቤተ ክርስቲያንስ በሰማይ ያለችውን

መነኮሳትም የውስጥ ሰላማቸውን ኃይል ያጡታል፡፡ ስለዚህ ዓሣ ወደ ባሕር ለመግባት እንደሚጣደፉ እኛም ወደ በእታችን ልንጣደፍ ይገባ ናል፡፡ ይህም የምናደርገውም በውጪ ከቆየን ውስጣዊ ንቃታ ችንን እንዳናጣው በመፍራት ነው፡፡ /አባ እንጦንስ/

፭፻፭. አዲስ ችግር በውኃ ሕይወት የሚያገኘውን ያህል ገድለ ቅዱሳንም ለክርስቲያን ሕይወት የሚሠጥ ጣፋጭ ምግብ ነው፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፭፻፮. ሂድና በእትህ ውስጥ ገብተህ ተቀመጥ እርፀ ሁሉንም ነገር ትነግርህለች፡፡ /አባ ሙሴ ጸሊም/

ክብር

፭፻፯. ሰው በመሆናችን ከእንስሳት እንበልጣለን፡ ክርስቲያን በመሆናችን ከሰዎች እንበልጣለን፡፡ /መጋዚ አፄስ እጹብ/

፭፻፰. በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሞቱ ቅዱሳን ልናከብራቸው ይገባል፡፡ /ጴድስቅልያ/

ምናኔ

፭፻፲. በገዳማት እየኖሩ ነገር ግን በከተማ እንደሚኖሩ የሆኑ ብዙዎች አሉ፡፡ እነዚህ ጊዜያቸውን እያጠፉ ነው፡፡ ብቻውን ሆኖ ከብዙዎች ጋር ለመኖር ሲመኝ ከመኖር ይልቅ በዙሪያህ ብዙ ሰዎች ኖረው የብቸኝነትን ሕይወት መኖር የተሻለ ነው፡፡ /አማሞይ ማቱሮና/

፭፻፲፫. በስስት የሚዋጋህ ጸር ጥቂት ረሃብን ትታገሰው ዘንድ አይተውህም፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፭፻፲፱. በጠባብ በር ለመግባት እንታገል፡ ሣፎች በከረምቱ የዝናም ውሽንፍር ውስጥ ጸንተው ካላለፉ በስተቀር ፍሬ ሊያፈሩ እንደማይችሉ ሁሉ፡ በእኛም እንዲሁ ነው፡ ይህ የአሁኑ ዘመናችን የውሽንፍርና የማዕበል ጊዜ ነው፡ ስለዚህ መንግሥተ ሰማይን ለመውረስ የምንችለው በብዙ ፈተናዎችና ውጣ ውረዶች በኩል በማለፍ ነው፡፡

/አማሞይ ቈጮራ/

ትምህርት

፭፻፳. መራት እንደ እንዲት ዜጋ አትቀበልህም ሰማይ ግን ደህና መጣህ እያለች ትቀበልሃለች፡፡ ዓለም ታሳድድሃለች፡፡ ቅዱሳን መላእክት ግን ወደላይ ወደ ክርስቶስ ይወስዱሃል፡፡

/ባሲልዮስ ዘቂሳርያ/

፭፻፳፩. ቀዳሚት ሔዋን ለሰው ያመጣችውን ክፋ መንፈስ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለድንግል ማርያም ባበሰራት ጊዜ ክፋ መንፈስ ጠፋ፡፡ /ቅዱስ ሄሬኔዎስ/

፭፻፳፪. ሽፍታው በመስቀል ላይ እያለ በአንድ ቃል ጸደቀ፡ ከሐዋርያት አንዱ ሆኖ ተቆጥሮ የነበረው ይሁዳ ያን ሁሉ ድካሙን በአንዲት ምሽት አጥቶ ከመንግሥተ ሰማይ ወደ ሲያል ወረደ፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው ስለ ራሱ መልካም ሥራ አይመካ፡ በራሳቸው የሚታመኑ ሁሉ ይወድቃሉና፡፡ /አባ ዘንትያስ/

ስኬት

፭፻፲፩. ለሕይወታችን ጥቅም የሚሰጥ ውድቀት ስኬት እንጂ ውድቀት አይደለም፡፡ /ጥሑን አፈወርቅ/

ፈተና

፭፻፲፱. ሰይጣን በምድራዊ ሕይወታችን ላለን እግዚአብሔርን በቸርነቱ ለድነንታችን ምክንያት ይሆኑን ዘንድ የሰጠንን ቀናት እንዳናስብ ያደርገናል ፡፡ /ጥሑን አፈወርቅ/

፭፻፲፫. አስቀድሞ የደረሱ ተመሳሳይ ውጊያዎች በዚህ ትውልድ ላይ ያደርሱ ዘንድ እግዚአብሔር አያፈቅድም፡፡ ምክን ያቱም አሁን ያሉት ሰዎች ደካሞች ስለሆኑና ፈጽሞ ሊቋቋሟ ቸው ስለማይችሉ፡፡ /አባ እንጦንስ/

፭፻፲፬. ዓለማዊ መቀማጠል መጀሳደል ባሕር ውስጥ ያለ በውኃ የተሠወረ ሸፍ ደንጊያ ነው፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፭፻፲፭. ወርቅ ያለ እሳት እንደማይፈተን ሁሉ የክርስቶስንም ፀጋና ክብር ሳይፈተኑ ማግኘት አይቻልም፡ የዚህ ዓለም ፈተናና እሳት ቶሎ ያልፋል ይጠፋል፡፡ ኃጢአተኞች የሚገቡበት የገ ሃነም እሳት ግን ለዘላለም እንደ ነደደ ይኖራል፡፡ /ቅዱስ ግናዕ/

፭፻፲፮. ቤተ ክርስቲያን መጠጊያችን ነች፡ ቤተ ክርስቲያን የኖኅ መርከብ ነች፡ በውስጧ እንጠለላለን፡ ከውጪዋ ግን ማዕበልና ቀላያት ተከፍተዋል፡፡ /ቅዱስ እንድርያስ/

፭፻፲፯. እግዚአብሔርን ከማሰብ ፈጽሞ የራቀ ሰው ባልንጀራ ውን በክፉ ነገር ያሰናክል ዘንድ የሚያስብ እርሱ ነው፡፡

/ማር ይስሐቅ/

ንጽሕና

፭፻፳፫. ከሰው መለየት ክቡር እግዚአብሔርን የማወቅ ምሥጢር የሚጥኑበት የንጽሕና መገኛ ናት ይህቺም የጌታ የምትሆን መንፈሳዊ አእምሮ ናት፡፡ /ጥሑን አፈወርቅ/

፭፻፳፬. እንደ በደለኛ አድርገን በራሳችን የምንፈርድ ከሆነ ሌሎችን ንጹህና መላእክት ሆነው እናየቸዋለን፡፡ ነገር ግን በሌሎች ላይ እንደ በደለኛ የምንፈርድ ከሆነ ራሳችንን እንደ መላእክትና ቅዱሳን እናያለን፡፡

/ቅዱስ አትናቴዎስ/

፭፻፳፭. በክርስቶስ ፊት ቁመህ በምትጸልይበት ጊዜ እንዳ ታፍር በሥራህ ሁሉ ንጽሕ ሥጋን ገንዘብ አድርግ፡፡

፭፻፳፮. ልበ ንጹሕ ትሆን ዘንድ ሊሳውን ከማጠልሸትና ከማማት ራስህን ከልክል፡ የማጠልሸትን ነገር የሚሰማ ጆሮ ከቶውንም ልብን ሳይቆሽሽ በንጽህና መጠበቅ አይቻለውም፡፡

/ማርይስሐቅ/ቅዱስ መቃርስ/

፭፻፳፯. ሰው ሥራውን የሚፈጽምባቸው /ፍጹም የሚሆንባቸው ማዕረጋት/ ሶስት ናቸው፡፡ የመጀመሪያይቱ የወጣንያን ማዕረግ ንጽሐ ሥጋ ናት፡፡ /ማር ይስሐቅ/

፭፻፳፰. እንደ ሱራፌል ንጽህና የያዘ ሰውነት ስሙ ይከበርና በእግዚአብሔር ዘንድ መላልሰው ከሚሰጡት ንጽሕ መሥዋዕት ይልቅ የከበረ ነው፡፡ /ማር ይስሐ/

፭፻፳፱. የሥጋ ንጽሕና በሥጋ ከሚሠራ ኃጢአት መጎጻት ነው፡፡ የነፍስ ንጽሕናም በልቦና ከምትኖር ከሐልዮ ኃጢአት መለየት ነው፡፡

፮፻፴፫. ንጽሕ ሆኖ የሚጸልይ ሰው ርኩሳን መናፍስትን ያጠ
ፋቸዋል፤ በግድ የለሽነት የሚጸልየው ሰው ግን የርኩሳን
መናፍሳት መሳለቂያ ሽቀጥ ነው የሚሆነው።
/ቅዱስ አፍሬም/

፮፻፴፬. አንተ ንጹሕ ብትሆን በእመንዝራው ላይ አትፍረ
ድበት፤ አለበለዚያ አንተም እንደ እርሱ ሕግን አፍራሽ
በደልኛ ትሆናለህ። ምክንያቱም "አታመንዝር" ያለ እርሱ
"አትፍረድም" ብሏል። /አባ ጢሞቴዎስ/

ምክር

፮፻፴፰. ቅጣትን ሳይሆን የቅጣት እናት የሆነውን ኃጢአት
እንፍራ። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፮፻፴፫. ከኃጢአት ሽሽ፤ ወደ ራስህም ጠልቀህ ግባ በነፍስህ
ውስጥ ወደ እግዚአብሔር መንግስት የሚያወጣውን መሰላል
ታገኛለህ /ቅዱስ ይስሐቅ ዘቦሪያ/

፮፻፴፱. ጠዋት ከእንቅልፍ ተነሥተህ ሥራህን ከመጀመርህ
በፊት የእግዚአብሔርን ቃል አጥና። እንተ የእግዚአብሔር
ቃል የዘወትር ወዳጅህ አድርገህ የምትይዘው ከሆነህ
በዓለማዊ ነገሮች ባተሌ አትሆንም፤ አትታወክም፤ ኃጢአትም
አትሠራም። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፮፻፴፮. ልብህን ከሥጋዊ ሁከት ለይ ። /አረጋዊ መንፈሳዊ/

፮፻፴፯. ከፋ ስሠራ ወንድሙን በቤቱ ለብቻው ሆኖ የሚመ
ከረው ሰው ግን በመምከሩ አዋቂ ይሆናል፤ አንድም ከመ
ከራው በምክሩ አዋቂ ይሆናል ወንድሙን በእደበይ
የነቀፈ ግን ሐዘን ይጸናበታል። /ማር ይስሐቅ/

፮፻፴፰. ወዳጆን ተሰውሮ የሚመክር ሰው ብልህ ባለ መድኃኒት
ነው፤ እንዲያድግም መክር አስተምሮ ያድነዋል እና።
/ማር ይስሐቅ/

፮፻፴፱. ወንድሙን በብዙ ሰው ፊት የሚያመሰግነው ሰው
እርሱ እውነተኛ ጠላቱ ነው፤ በውዳሴ ከንቱ ይጎዳ ብሎ ነው።
/ማር ይስሐቅ/

፮፻፵. ማንም ቢሆን የወንድሙን የውድቀት ወሬ አይስማ፤
ምክንያቱም በውሸቱ በእርሱ ላይ ከመፍረድ ይድናልና።
/ሙሴ ጸሊም/

፮፻፵፩. ከሐሜተኛ ጋር አትሒድ፤ ስለማንም በክፋ የተነገረን
ሐሜት አትመን። /ሙሴ ጸሊም/

፮፻፵፪. ወንድሙን የሚወቅስ የሚንቀውም ወይም ስለ እርሱ
ክፉን የሚናገር በእውነት ክርስቶሬሌ የራቀ /ፈጽሞ/ ነው።
/ቅዱስ ኢሳይያስ/

፮፻፵፫. ሰውን ስትረዳው ጐሳውን፤ ጸታውን፤ ሃይማኖቱን
ብለህ አትርዳው ነገር ግን በክርስቶስ ስም እርዳው።
/ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፮፻፵፬. ለጠፋት አዛኝ፤ ለወደቁት መሐሪ ሁን። /ዮሐንስ ሐጺር/

፮፻፵፭. ለዚህች ሃይማኖት የተገባህ ሆነህ ልትገኝ ከወደድህ
ልጇ ሆይ ይህንን ትጠብቅ ዘንድ ተዘጋጅ፤ ከሁሉ አስቀድሞ
ፈጣሪህን እግዚአብሔርን ውደደው፤ በፍጹም ልቡናህ
በፍጹም ሰውነትህ በፍጹም አሳብህም ባልንጀራህን እንደ
ራስህ አድርገህ ውደድ። /ሠልስቱ ምእት/

ሥጋ ምግባር

፮፻፵፯. ሃይማኖት ያለው ሰው ቢኖር ምግባሩ ከፋ ከሆነ እነሆ
ሃይማኖቱን ካደ የትምህርትንም ሕግ አሰደበ፤ ምግባር
ሠርቶ ሃይማኖትን ካልተማረ ካላወቀ በምግባር ብቻ
ሊጸድቅ ክርስቲያን ሊባል አይቻለውም።
/ዮሐንስ አፈወርቅ/

፮፻፵፰. የቀናች ሃይማኖት የምግባርን መልክ ትይዛለች፤
በምግባር መልክ ትገለጻለች፤ እንዲህ ካልሆነ ግን ክርስ
ቲያን ተብሎ ሊጠራ አይገባውም። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

፮፻፵፱. ማዕረግ በሥራ ካልታገዘ ዋጋ የለውም፤ እያንዳን
ዳችን የደረብነው የክብር ካባ በሥራ ካልተደገፈ
ማፈሪያችን ነው። ... ስለዚህ አደራችሁን እኛ መሥራት
ያለብን አሁን ስለሆነ እንሥራ ... ነገ የኛ አይደለም
ትናንትም የአባቶቻችን ነበር። /ባህዕ አቡነ ጰውሎስ/

፮፻፶. ልጄ ክሰነፍ ሰው ጸም ይልቅ የአዋቂ ሰው ምክር
ይሻላል። ከልብ መታወር የዓይን መታወር ይበልጣል።
ዓይነ ስውር ተመርቶ ይሄዳል። ልቡ የተሰወረ ሰው ግን
በተና መንገድ ቢመሩት ተመርቶ ለመሄድ አይችልምና።
/አንጋረ ፈላስፋ/

፮፻፶፩. ፍጹማን የሚባሉ ፍጹም የሚያሰኙ አራት ነገሮች
ናቸው። እነርሱም ማስተዋል፤ መስጠት፤ መልካም ጠባይ፤
ምኞትና ፍላጎትን ማሸነፍ ናቸው። /አንጋረ ፈላስፋ/

፮፻፶፪. አግኝቶ ሳለና ሲቻለው የማይበድል ሰው ፍጹም ነው
በኃጢአን ነገር በማድረግ የሚፋጠን ሰው ብልህ ነው። /
አንጋረ ፈላስፋ/

፮፻፶፫. ለልጆችህ መራብንና መጠማትን አስተምራቸው፤ እድገው
ሀብታሞች በሆኑ ጊዜ የተራቡበንና የተጠማውን እንዲያስ
ታውሱ የለመናቸውን ችል እንዲይሉ። /አንጋረ ፈላስፋ/

፮፻፶፬. ሰው ሰውን አላውቀው ያለ አስተድሞ ራሱን ባያውቅ
ነው፤ ራሱን ቢያውቅ ኖሮ ሊላውንም ባወቀ ነበር።
/አንጋረ ፈላስፋ/

የእግዚአብሔር ቃል/ቃለ እግዚአብሔር

፮፻፶፮. ሰዎች የዘጉብህን በር አትመልከት፤ በእግዚአብሔር
እጅ ያለውን ቁልፉ ተመልከት። /አቡነ ሺኖዳ/

፮፻፶፯. ቅዱስ መጽሐፍ በሰውልጅ መዋዕለ ዘመን ተቀድቶ
የማያልቅ ሰፊና ጥልቅ የሆነ የሕይወት ውኃ ምንጭ /ውቅ
ያኖስ/ ነው። /ቅዱስ አፍሬም ሶሪያዊ/

፮፻፶፰. ቅዱስ መጽሐፍ በቅዱስ ትውፊት ካፍነት ላይ
የተገኘ ጥዑም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው።
/የዜና አሙሙ ሊቃውንት/

፮፻፶፱. ቃለ እግዚአብሔር የግነት ፍሬ ነው። የግነት ፍሬ
የእግዚአብሔር ገንዘብ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ በክንቱ
አልፈጠረውም። /ሊቀ ትጉሃን ኃይል ገብርኤል ጻሜ/

ቅናት

፮፻፷. ቅናትን በልቡ ውስጥ የሚሸሽግ ሰው በሞቱ ላይ
እባብ የሚያስቀምጥ ሰውን ይመስላል፤ ሞድስ ንፉኅን
እንደሚ ያባርር ሁሉ ጥላቻም እውቱትን ከልብ ውስጥ
ያባርራል።
/ቅዱስ አፍሬም ሶርያዊ/

፮፻፷፩. ቀናተኛ ሰው ጎረቤቱ በጥሩ ዝና ሲኖር ከማየት ይልቅ
ብዙ ሊሸከማቸው የማይችላቸውን መከራዎች ቢያገል
ይመርጣል። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

ድርሻን መወጣት

፮፻፷፪. ጀግናች ከሌሉ አገርም የለችም። አገርም ከሌለች
ጀግናች አይተኙም እስካለ አገር ነጻነት መሥዋዕት መሆን
እንዳይረሱና እንዳይፈዝ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች
ትውልድ የሚስተማር የማስጠናትና የመቀስቀስ ኃላፊነት
አለባት። /አቡነ ሺኖዳ/

ክኃጢአት መለየት

፮፻፷፫. ዓለም እኔን ሳትንቀኝ አስቀድሚ ንቂያታለሁ።
/ቅዱስ አትናቴዎስ/

ሞትን ማሰብ

፮፻፷፬. ሰው አገሩን ጥሎ በሔደ ጊዜ ሁሉ ያዝንለታል፤
ክርስቴ ክጉልት በተለየ ጊዜ ሁሉ ይራሩለታል ያለቅሱ
ለታል፤ ከመንግሥተ ሰማያት ከተድላ ፡ ከመዓዛ የተለየ
ሰውማ ምን ያህል ልቅሶ ማልቀስ ምን ያህል ዕንባ ማፍሰስ
ይገባው ይሆን። ሬሙኝ ያለቅስ ብዙ ዕንባ ያፈስ ዘንድ
የሚገባው ምን ያህል ይሆን። /ዮሐንስ አፈወርቅ/

የእግዚአብሔር መግቦች

፮፻፷፭. እውቱትሃን ሰጠኸኝ ሕሸሆንም ይረዳኝ ዘንድ ላክህልኝ።
/ማር ይስሐቅ/

ነገረ ድኅነት

፮፻፷፮. እነሆ የመጻኒን ምሥጢራዊ ተአምር ሊነጻጽር የሚችል
አንዳችም ነገር የለም። ጥቂት የደመ መለኩት ጠብታዎች
መላውን ዓለም ዳግመኛ ቤዛዊያ ተፈጥሮ ፈጥረዋልና።
/ቅዱስ ኒርሎሮስ ዘአንጾኪያ/

አቅምን ማወቅ

፮፻፷፯. ዐዋቂ ነኝ ጻድቅ ነኝ አትበል። ዐዋቂ ጻድቅ ሳትሆን
ቀርተህ እንዳታፍር። /ማር ይስሐቅ/

ተአምኖ ኃጣውዕ

፮፻፷፰. በኃጢአት የወደቀ ቢኖር ኃጢአቱን አይርሳ ኃጢአቱ
የማይረሳ ነውና /ቀሐፕንጦስ/

ተአምኖ

፮፻፷፱. ምንም እንደ ማልፈራና ምንም እንደማልፈልግ
በተሰማኝ ጊዜ ዓለምን ረግፏ ይዣታለሁ።
/ሊቁ አውግስጢን/

፮፻፸. እንድ ሰው በእግዚአብሔር እቅፍ ውስጥ እንዳለ
ካወቀና እግዚአብሔር ሁሉንም ያከናውንልኛል ካለ ልቡ
ፍጹም ይሆናል። /ማር ይስሐቅ/

፮፻፸፩. ኃጢአቶችህን ምክንያት በማድረግ ወደ እግዚአብሔር
መቅረብ የምትፈራ ከሆነ ለእርሱ እንቅፋት ስለምት
ሆንበት ቢያንስ ቢያንስ የተወሰነ ያህል የእርሱን ቸርነትና
አባታዊ ፈቃድ ከመግለጽ በመቆጠብ በራስህ ማስተዋል
ጀምረሃል ማለት ነው። ስለሆነም በኃጢአት ምክንያት
ይቀራል ስለምትለው ጸሎት ያለህን ማንኛውንም ፃይነት
ጥርጥርና ማመንታት ከእንተ ዘንድ እርቅ።
/ዮሐንስ አፈወርቅ/

ሥነ ምግባር

፮፻፸፪. በምክረ ከይሲ ተታልላ በኃጢአት እዘቅት ወድቃ
የነበረችው ቀዳሚት ሔዋን በልጇ በዳግማት ሔዋን በድንግል
ማርያም ምክንያትነት ከድቀት ኃጢአት ተነሣች ከመርገመ
ኃጢአት ፊጽማ ዳነች።
/ቅዱስ አራቅሊስ/

፮፻፸፫. የሰው ልጅ በወደቀ ጊዜ እግዚአብሔር በምስል
ተነጥቆ ነበር ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የመጣው ያጣነውን
ክብር ሊመልስልን ነው። /ቅዱስ አትናቴዎስ/

፮፻፸፬. እግዚአብሔር ያለመከለከል ሰሚ፤ ያለመንፈግ ለገሥ፤
ያለቂምና ያለቅናት ኃጢአትን የሚያስተሰርይ ነው።
/ቅዱስ ኢጲፋንዮስ/

ነገረ ማርያም

፮፻፸፭. ከድንግል በተወለደ ጊዜ ድንግልናዋን ያለመለወጥ
አጸናው ቀድሞም ሔዋን ድንግል ነበረችና ዲያብሎስ
አሳታት እንጂ፤ ድንግል ማርያምን ግን ገብርኤል አበሠራት።
/ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፮፻፸፮. የቀዳሚት ሔዋን ያለመታዘዝ ቋጠሮ በዳግሚት ሔዋን
በእመቤታችን መታዘዝ ምክንያት ተፈታ። ድንግሊቱ
ሔዋን ባለማመን ያሠረችውን ድንግል ማርያም በእምነቷ
ፈታችው። /ሰማዕቱ ቅዱስ ጀስቲን/

፮፻፸፯. ነገር ግን ሔዋንን ዲያብሎስ አሳታት የሞት ምክንያት
የሚሆን ቃልን ወለደች። ማርያም ግን መልአክ በአበ
ሠራት ጊዜ ሁሉን ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚመራ
አካላዊ ቃልን በሥጋ ወለደች
/ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/

፮፻፸፰. ለመላው ዓለም አምላካዊ ይቅርታ የተላከበት ጎትምት
ክታብ ወይም የታተመች ደብዳቤ እመቤታችን ናት።
/ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ/

፮፻፸፱. ምስጋና የተመላሽ ድንግ ሆይ ማን በመሰለው፤ ማንስ
በተመሰለበት ምሳሌ እንመስልሻለን? ... ድንግል ሆይ
ቅዱሳን ነቢያት ትንቢት የተናገሩልሽ፤ ምሳሌ
የመሰሉልሽ እንቺ ነሽ። /ቅዱስ አባ ሕርያቆስ/

፮፻፹. እመቤታችን በመርገመ ኃጢአት ውስጥ ለነበረው
መላው ዓለም ተስፋ መስቀልን እንደሰበከችና ተስፋ
ድኅነትን እበሠረች። /ሊቁ አባ ጽጌ ድንግል/

፮፻፹፩. እመላክን የወለድሽ ድንግል ሆይ ልዑል ባሕርይ
እግዚአብሔር ዘጠኝ ወር ከእምስት ቀን ማኅፀንሽን
መቅደስ አድርጎ የተመሰገንብሽ፤ ሰማያዊው ንጉሥ ከተማው
አድርጎ ሉዓላዊ ዙፋኑን የዘረጋብሽና በተዋሕዶ የከተመብሽ
ረቂቅ ሀገሩ አንቺ ነሽ። /ቅዱስ አፍሬም ሶርያዊ/

ተዘክሮተ እግዚአብሔር

፮፻፹፪. ዓሣ ከባሕር ወደ የብስ በወጣ ጊዜ የሚሔድበት
የሚደርስበት አጥቶ እንዲጨንቅ፤ ልቡናም እግዚአብ
ሔርን ከመዘከር በተለየ ጊዜ ይህን ኃላፊውን ዓለም
በማሰብ የወዲህ ኖውን ዓለም ይዘነጋል። /አረጋዊ መንፈሳዊ/

ተግባረ ነፍስ

፮፻፹፫. ከመብል ከመጠጥ ተለይቶ መኖር ለሥጋ አይቻለውም።
ለነፍስ ግን ከመብል ከመጠጥ ከሊሎች ይለይ ዘንድ
ይቻለዋል። /ማር ይስሐቅ/

፮፻፹፩. ነፍስ ልትሠራት የምትወድደው ስግደትን አብዝቶ መስገድ ነው። /ማር ይስሐቅ/

ከባቴ አበሳ

፮፻፹፪. በጌታ እግዚአብሔር ምሕረት ትወለድ ዘንድ የወን ድምህን በደል ሸፍን፤ ከተሰፋ መቁረጥ ስሜት ገጽ እንዲወጣ አጠንክረው። /ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ/

ታሪክ

፮፻፹፫. ኢትዮጵያ ምድሯ ተቆፍሮ የሚወጣው ነው። ኑና እንቆፍር መስቀል፤ ቃለ አዋዲ /ቃጭል ፡ ታቦትና አጽመ ቅዱሳንን እናገኛለን። በገንዘባችሁ ጽድቅን ግዙ በጉል በታችሁ ሰማያዊ ሀብት ተቀናጁ።

/ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ/

፮፻፹፬. አሁን ስላለፈው ጊዜ እያለቀስን የምናባክነው ጊዜ የለንም፤ ዛሬ ሁሉም በእጃችን ነው፤ ለባሕላችን፤ ለታሪ ካችን፤ ለሃይማኖታችን፤ በፈ.ቃደኝነት፤ በኅብረት ሆነን የጥበብ ወዳጅ እንጂ የጥበብ መምህር ሆኖ አለመታየት ታላቅ ዕድል ነው። የሚያስፈልገንን የምናሟላበት ወቅት ነው። ይህች የምንሳሳላት ቤተክርስቲያን መለያ ምልክቷ ሰላም፤ ፍቅር፤ አንድነት ነው። ይህ ደግሞ ዛሬ የተከሰተ ሳይሆን አብሯት የነበረ የዘመናት ዓላማዋ ሆኖ የቆየ ነው። ስለዚህ ሁላችንም ሥራችንን በጥራት ከሁሉም በላይ ከውስጣዊ ስሜት በመነጨ ፈቃደኝነት በመሥራት አገል ግሎታችንን ለማበርከት መዘጋጀት አለብን።

/ብፁእ አቡነ ጳውሎስ/

፮፻፹፭. አባቶቻችን የተውሰ ታሪክና ሃይማኖት አላወረሱንም፤ ከውጭ የተቀበሉት የተበደሩት፤ የተከለሱ ሃይማኖትና ታሪክ የላቸውም፤ ቤተ ክርስቲያናችንም የታሪክና የሃይ ማኖት ምንጭና ዐምድ ናት፤ የጌታን ሕግና ሥርዓት ሳታፋልስ ሳታዛባ የያዘች ሃይማኖት ናት። እኛ የምንከ ተለው ሃይማኖት ጌታችን ያስተማረው፤ ሐዋርያት የደነገ ጉት፤ አባቶች ያጸኑት የተባረ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ነው። እኛ የምንከተለው መጽሐፍ ቅዱስን ነው። መታደስ መሻሻል ያለበት የተሳሳተ ነገር ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግን ምን ጊዜም እውነት ነው፤ እውነት ደግሞ አይሰ ለችም፤ አይለወጥም፤ አይታደስምም።

/ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ/

፮፻፹፮. ኢትዮጵያውያን የማያኮሩ፤ የማይታወቅ፤ ተድበስብሶ የሚታለፍ ታሪክና ሃይማኖት የላቸውም። የኢትዮጵያ ኦርቶ ዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምትከተለው ሃይማኖት የእግ ዚአብሔር ሥራ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው። በአድርባይ የተቋቋመ፤ አቶ እገሌ ወይዘሮ እገሊት በዚህ ቦታ ሄደው አቋቋሙት የሚባል የማኅበር ሃይማኖት ወይም ደግሞ በኮሚቴ የተሻሻለ፤ የተቀየጠ ሃይማኖትም አይደለም። ከመጀመሪያው፤ ከመነሻው ጀምሮ በማይናወጥ የክርስቶስ መሠረት የተቋቋመ ነው። ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጠራ እምነቷን ሳትለውጥ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ጸንታ የቆየችው። የሚሻረው የሚለወጠው የሰው ሥራ ብቻ ነው። /ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ/

አገልግሎት

፮፻፹፯. ወጣቶች ባለ አቅማችሁ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል አለባችሁ፤ ቤተ ክርስቲያን እናታችሁ ናት በመ ሆኑም በተለየ ሁኔታ ልትንከባከቡአትና ልታከብሯት ይገባል። ቤተ ክርስቲያናችሁን ትናንት የነበሩ፤ ዛሬ ያሉ አባቶቻችን ወደዱ ፈጽሞ አትርሷአቸው። ወጣቶች የቤተ ክርስቲያን የጀርባ አጥንቶች ናቸው። ትውፊታዊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የሕይወት መንገድ ሲያያዝ የመጣ የወንጌል መገለጫ ነው። ሃይማኖታችሁ በደማችሁ ውስጥ ናት። ለሃይማኖታችሁ ብርቱ ጥንቃቄ ልታ ደርጉና ለቀጣዩ ትውልድ ልታሸጋግሩአት ይገባል። መንፈሳዊ ተልእኮ አችሁን ከዕለት ተግባራችሁ ጋር ልታጣጥሙና ትጋት ያላችሁ የቤተ ክርስቲያን አባላት ልትሆኑ ይገባል። ክርስትና ከቃላት ይልቅ በተግባር መገለጽ አለበት። ይህም ማለት ከመናገር ይልቅ ማድረግ መሥራት ማለት ነው። ሰዎች ሥራችሁን አይተው በምሳሌነት እንዲከተ ሉአችሁ የክርስትና ሕይወት አርአያ ሁኑ። ሀብታሞች ይሁኑ ድሆች ለሰዎች ክብር ስጡ ምክንያቱም እግዚአ ብሔር ራሱን የሚገልጠው በእነርሱ ውስጥ ነው።

/አቡነ ጎርጎርዮስ/

ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ

፮፻፹፰. ለሰውነትህ ዕረፍትን ታገኝ ዘንድ ዘወትር ቅዱሳት መጽሐፍ መመልከት ውደድ። /ማር ይስሐቅ/

፮፻፹፱. ልጄ ሆይ መጻሕፍት እምላካውያትን መመርመር አትተው በእነርሱ እግዚአብሔርን መፍራት ታገኛለህና። በዚህም

እግዚአብሔር ለሚወዱት ወዳዘጋጀው ዘላለማዊ የሕይወት መንገድ ይመራሃል። /ቅዱስ ያሬድ/

፮፻፺. ንጽሕናና በሰውነትህ ልታሳድር ብትወድ ሁልጊዜ በመጸለይና መጽሐፍ በመመልከት ሐልዮ ኀጣውእን ካንተ አርቅ። /ማርይስሐቅ/

፮፻፺፩. ወደ በጎ ነገር የሚያደርሱ መጻሕፍትን ዘወትር በመመልከት በጎ ነገርን ማሰብ በልቡናው ይጸናል።

/ማር ይስሐቅ/

ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን

፮፻፺፪. ሥር ሳይኖረው መልካም ተክል ሊኖር እንደማይችል ሁሉ ያለ ምሥጢራት ሊኖር የማይችልም ጸሎት የለም፤ በተለይም ያለ ቅዱስ ቁርባን። /አቡነ ሺኖዳ/

፮፻፺፫. ለቤተ ምኩራብ የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘንድ የታወቁና የተረዱ ናቸው። ምኩራብ ዘራች፤ ቤተ ክርስቲያን አጨደች። ምኩራብ ፈተለች፤ ቤተክ ርስቲያን ለበሰች። /አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ/

ለባልንጀራ ማሰብ

፮፻፺፬. በልቡ በሌላው ላይ የሚፈርድና አፍንም በርሱ ላይ የከፈተ፤ በወንድሙ ላይ በፈረደበት ኃጢአት እርሱም ይወድቁበታል፤ መለኮታዊ ጥበቃ እርሱንም ስለፈራጅነቱ ይለየዋልና። /ቅዱስ ዶሮቴዎስ/

፮፻፺፭. አንተ በሌላው መከራ አታምጣ። ይበድሉህ አንተ አትበድል፤ ይሙህ ይንቀፉህ አንተ ማንንም አትማ ትንቀፍ። /ማርይስሐቅ/

ጀ፻፲፮. ማንኛውም ዜጋ የተቸገረ ወገኑን መርዳት ያለበተ ሲተርፈው ብቻ ሳይሆን ካለው በማፈራል ቁምር መሆን አለበት።
/ቅዱስ እንድርያስ/

ቅዱሳት ሥዕላት

ጀ፻፲፯. ቅዱሳት መጻሕፍት በነባቢ ቃል የተናገሩትን መለኮታዊ ምሥጢር ቅዱሳት ሥዕላት በእርምጥና በተደሞ ሆነው በግልጽ ያሳያሉ። /ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ/

ጀ፻፲፰. ያልሞተ ሰው የሚንቀሳቀስ ራስ ነው፤ የቅዱሳን ሥዕል ግን የማይንቀሳቀስ ሕያው ነው። /አንድሪ ደሳስፍ/

ፍርድ

ጀ፻፲፱. ዘወደቁትና ድቀት ባጋጠማቸው መካከል ልዩነትን አታድርግ። የኩራት ሐሳብም አንተ ፈራጅ እንደሆንክ አያሳ ምንም። /ቅዱስ አባጋሪዮስ/

በሌላው አለመፍረድ

ጀ፻. በጽሙና ያለ የሚመስል፡ በሀሊናው ግን በሌሎች ላይ በመፍረድ የተጠመደ ሰው ይኖራል። ይህ ሰውና እርሱን የሚመስል ሁሉ ዘወትር እየለፋለፉ እንደሆነ ይረዳ።
/ቅዱስ ጴሜን/

ጀ፻፩. ማንንም ክፉ ነው ብለህ በሀሊናህ አታስብ ወይም አትዛዘል፡ ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ "ማንንም ርኩስ አሉ እንዳልል እግዚአብሔር ይህን አሳየኝ ብሏል። /ሐዋ ፲፡ ፳፰/
/ቅዱስ መቃርዮስ/

ጀ፻፪. በእንተም እንደነርሱ እንዳትወድቅ በሌሎች ላይ አትፍረድ በሌሎች ላይ የሚፈርድ እነርሱ በወደቁበት

መንፈሳዊ መርነት ውስጥ ባይሆንም ራሱን ማን ለፈተና አያጋለጠ ነው። ከአፈር እንደተገኘህ አትርሳ፡ ደካማ ሥጋና የራሱ ተፈጥሯዊ ጫና እንደሌሎቹ ሁሉ በእንተም ላይ አለብህ። የእግዚአብ ሔርን አስታዋሽነት ቸል ያለ ሰው ብቻ በወንድሙ ላይ ክፋን ይናገራል። /ማርይሳሔ/

ጀ፻፫. የራሳችንን ጉዳዮች ብንመረምር በሌሎች ላይ ባልፈረድን ነበር፡ ሌሎችን የምንወቅስበትን ድክመት በራሳችን ላይ እናገኘዋለንና። / ማርይሳሔ/

ጀ፻፬. ንጥኡን ንጥአ ነው ብለህ አትንቀፈው ሁላችን ንጥአን ነንና። /ማር ይስሐቅ/

ጀ፻፭. ምንም እንኳ ምክንያቶች ቢኖሩህ ማንንም አትንቀፍ፡ ሕጉን ለመፈጸም አትቆይ ወንድምህን ብታየውም እንኳ አርመው ስሙንም አታጥፋ። /ቅዱስ እንጦንስ/

ጀ፻፲፫ ዓ.ም. አዲስ አበባ፡ ዓለም ማተሚያ ቤት

፳፰. ኃይለ ማርያም ማርማ (አባ)፡ ሥነ ምግባራዊ ጥበብ። 1993 ዓ.ም፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

፳፱. ማርማ ባቱ (ዲ/ን)፡ ጉህ ወደ እግዚአብሔር። 1995ዓ.ም፡ አዲስ አበባ

፴. ዘኤልያስ ወ/ሚካኤል (ዲ/ን)፡ የምስጋና ሕይወት። 2002ዓ.ም፡ አሊን ማተሚያ ድርጅት

፴፩. A spiritual psalter, from the works of our holy father saint Ephraim The Syrian, 1997

መጽሔቶች

፩. ደብረ ገሊላ አማኑኤል ካቴድራል፡ ማየ-ሕይወት። ፲፱፻፺፱ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ፡ ሶፊ ሚህ ማተሚያ ቤት

፪. _____መዝገበ -ጥበብ፡ ዘደብረ አሚ ፡ 1997ዓ.ም፡ ሚጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ

፫. _____ሄኤሚን። 1996ዓ.ም፡ sof.mic printing press

፬. _____ፊለገ ሠላም። 1998ዓ.ም

፭. _____ሥረይ ለ-ሙ። 1998 ዓ.ም

፮. ሰናፍጭ የሰሊዳ መጽሔት በተለያየ ጊዜ የወጡ

ዋቢ መጻሕፍት

፩. በሊቃውንት ጉባኤ፡ ወንጌል ቅዱስ። ፲፱፻፹፲ ዓ.ም፡ ተሰፋ ገብረ ሥላሴ

፪. መዝገቡ ካሣ፡ (ዲ/ን) ክርስቲያናዊ ሕይወት ወደ ትክክለኛ የትዳር ሕይወት እንዴት መድረስ ይቻላል። ፲፱፻፺፪ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ

፫. መጻሕፍተ ሐዲሳት ሠለስቱ። ፲፱፻፹፱ዓ.ም፡ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

፬. ማኅበረ ቅዱሳን፡ ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ። ፲፱፻፹፩ዓ.ም፡ አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

፭. ማኅበረ ቅዱሳን፡ አባ እንየው ውቤ የምዕራቡ ኮከብ። ፲፱፻፺፱ ዓ.ም፡ አዲስ ማተሚያ ቤት

፮. ማለደ ዋስይሁን (ዲ/ን)፡ እትፍረድ። ፳፻፪ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ፡ ሚጋ ማተሚያ

፯. ማር ይስሐቅ። ፲፱፻፹፱ዓ.ም፡ ተሰፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት

፰. ሽታ ብዙዬ፡ ዲያብሎስን የማሸነፍ ኃይል። ፲፱፻፺፯ ዓ.ም፡ አለኒ ማተሚያ ቤት

፱. ታኘው ወልዴ (ዲ/ን)፡ ጸሎት ለመንፈሳዊ ሕይወት። ፲፱፻፺፱ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ ፡ብራና ማተሚያ ድርጅት

፲. በመ/ጸ/ቅ/ሥላሴ/ ካቴድራል፡ መንበረ ጸባኦት፡ ፲፱፻፺፲ ዓ.ም፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት

፲፩. አያሌው ዘኢየሱስ፡ መንፈሳዊ ታሳትና ጥቅማቸው። ፳፻፲ ዓ.ም፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት

፲፪. አያሌው ዘኢየሱስ፡ መንፈሳዊ አገልግሎትና መንፈሳዊ አገልጋይ። ፳፻፲ ዓ.ም፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት

፲፫. አያሌው ዘኢየሱስ፡ ሀብታምና ደሀ። ፲፱፻፺፯ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት

፲፬. አያሌው ዘኢየሱስ ሞነፍስ አርነት። ፲፱፻፺፮ዓ.ም፡ አዲስ አበባ፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት

፲፭. አያሌው ዘኢየሱስ፡ የበረሃ አባቶች ምክሮች። ፳፻፫ዓ.ም፡ አዲስ አበባ፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት

፲፮. አያሌው ዘኢየሱስ፡ ጸሎት ንስሐና ተመስጠ። ፳፻፫ዓ.ም፡ አዲስ አበባ

፲፯. አሰፋ ሽፈራው፡ የዓለም ድንቃ ድንት ምሳሌያዊ አነጋገሮች፡ 1995ዓ.ም

፲፰. አንዱአለም ዳግማዊ፡ (መ/ር) ነቅዐ ሕይወት። 2002ዓ.ም ፡ አዲስ አበባ፡ ኤመርሰን ማተሚያ ድርጅት

፲፱. ኤፍሬታ መጽሔት። 1974ዓ.ም ብራና ማተሚያ ፡ አዲስ አበባ

፳. አንድነት አሸናፊ (ዲ/ን)፡ እግዚአብሔር መልስ አለው። 1997ዓ.ም፡ ባናዊ ማተሚያ ቤት

፳፩. አሸቱ ታደሰ (ዲ/ን)፡ የንስሐ ሕይወት። ፲፱፻፺፫ዓ.ም፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት.

፳፪. እንግዳ መርጊያ (ዲ/ን) ፳፪አባሲያ። መጽሔት፡ 1997ዓ.ም፡ ግብጽ

፳፫. ወንድወሰን ሶርሳ (ዲ/ን)፡ ደቀመዝሙርነት። ፲፱፻፺፭ዓ.ም፡ ዓለም ማተሚያ ቤት

፳፬. ወንድወሰን ሶርሳ (ዲ/ን)፡ የእምነት ሕይወት ክፍል ሁለት። 1998ዓ.ም፡ ላሊበላ አታሚዎች

፳፭. ዘድንግል ኑርበገን (አባ)፡ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ። 1995 ዓ.ም፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት

፳፮. ዳንኤል ክብረት (ዲ/ን)፡ በበረኃው ጉያ ውስጥ። ፲፱፻፺፲ ዓ.ም፡ አዲስ አበባ፡ ኢትዮ ጥቱር ዓባይ አታሚዎች

፳፯. ኃ/ጊዮርጊስ ተፈራ (ዲ/ን)፡ የመንፈሳዊ አድገት ማነቆዎች።